# የአፋር ክልል ሕገ መንግስት

/ነገሪት ጋዜጣ/

QAFAR DOLATIH RAKAKAYA

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር —
ሠመራ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7[th] Year No. —
SEMERA – July 2002

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፺፮ ዓ/ም
"የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፺፬ ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 16/2002
The Establishment of the Office of the Chief of Administration of Afar National Regional State and Definition of Its Powers and Duties Proclamation ............................................... Page 1

## አዋጅ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፺፬ ዓ/ም

## በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የርዕሰ–መስተዳድሩን ጽ/ቤት ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በሕገ – መንግሥቱ የተጣለበትን ከፍተኛ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲያስችለው የራሱ ጽ/ቤት እንደሚኖረው እንደሚገባ በመታመኑ ፣

እንዲሁም የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ እንደሆነ ተሻሽሎ በወጣው ሕገ–መንግሥት አንቀጽ — ንዑስ አንቀጽ — ስር አስቀድሞ የተደነገገ በመሆኑ፣

ከዚሁ በመነሣት ጽ/ቤቱን በሕግ በመመስረት በሰው ኃይልና በቁሳቁስ አደራጅቶ በተሟላ ሁኔታ ሥራውን ለማከናወንና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፫/ሀ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ ፩

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፮ ፲፱፻፺፬ ዓ·ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO 16/2002
## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE OFFICE OF THE CHIEF OF ADMINISTRATION OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE AND DEFINITION OF ITS POWERS AND DUTIES

WHEREAS, it has been provided for in Sub-Article 2 of Article 60 of the revised Constitution that the Chief of Administration of the Region shall have his own Chief office in order to discharge his responsibility as Chairman of the Council of the Administration.

WHEREAS, it has become necessary to staff and furnish the Office with manpower and equipment so as to carry our the activities effectively and provide services efficiently;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 47 (3) (a) of the Revised Constitution of the Council of the Afar National Regional State, it is hereby proclamied as follows:

### PART ONE
### General Provision

Article 1

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the Establishment of the Office of the Chief of Administration of Afar National Regional State and Definition of Its Powers and Duties Proclamation No. 16/2002.

## ክፍል ሁለት

**አንቀጽ ፪**
**ትርጓሜ**

፩· "ርዕሰ መስተዳድር" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት ማለት ነው።

፪· "የክልል መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት በርዕሰ–መስተዳድሩ የሚመራ ከፍተኛ የክልሉ የሕግ አስፈፃሚ አካል ነው።

፫· ጽ/ቤት ማለት የርህሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ነው ።

**የተፈፃሚነት ወሰን፣**

ይህ አዋጅ በክልሉ ርዕሰ – መስተዳድር ጽ/ቤትና እንደ አስፈላጊነቱ በወረዳ አስተዳደርና የክልል መስተዳድሩን ወክለው በሚሰሩ የአስተዳደር ጽ/ቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሦስት

### ስለ ርዕሰ–መስተዳድሩ ጽ/ቤት መቋቋም፣ ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና አመራር፣

**አንቀጽ ፬**
**ስለ ርዕሰ – መስተዳድሩ ጽ/ቤት መቋቋምና ተጠሪነት**

፩· የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ–መስተዳድር ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤቱ" እየተባለ የሚጠራው ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግሥታዊ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ተጠሪነት በክልሉ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።

**አንቀጽ ፭**
**ዓላማ**

የጽ/ቤቱ አላማ የክልሉ ከፍተኛ አስፈፃሚ አካል የተጣለበትን ከባድ ኃላፊነት በብቃትና ስልታዊ በሆነ መንገድ እንዲወጣ የዕለት ከዕለት ድጋፍ መስጠት ነው።

**አንቀጽ ፮**
**የጽ/ቤቱ አቋም**

ጽ/ቤቱ ርዕሰ መስተዳድሩንና ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን በሞያ አገልግሎት የሚያግዙ አማካሪ ተሿሚዎችን ጭምር የያዘ ሲሆን፣ ይህንኑ በማካተት አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል።

**አንቀጽ ፯**
**የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩· ለርዕሰ–መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤቱ አጠቃላይ አስተዳደራዊ አገልግሎት ይሰጣል። ለዚህም የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ተሟልቶና ተደራጅቶ መገኘቱን ያረጋግጣል።

፪· ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተገቢውን የፕሮቶኮል ሽፋን ይሰጣል።

፫· ለክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን የሚያስፈልጉትን የመሰብሰቢያ ቦታዎች ያሰናዳል፣ መሟላት የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁሶች ያቀርባል ተገቢውን የመስተንግዶ አገልግሎት ይሰጣል።

፬· የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ቃለ ጉባኤዎችንና ሌሎች ሠነዶችን ትክክለኝነታቸውን በማረጋገጥ በአግባቡ እንዲያዝና ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቀመጡ ያደርጋል።



## *PART TWO*

**Artice 2**
**Definitions**

In this proclamation

1) ''Head of the Region'' means the president of Afar Naional Regional State;
2) ''Regional Administrative Council'' means the highest executive body of the Region directed by the Chief Administrator.
3) "Office" means office of chief Administration of the Region.

**Article 3**
***Scope of Application***

This proclamation shall apply to the Office of Head of the region and woreda Administration and administrative offices representing the Regional Administration as may be necessary.

## PART THREE

### *Establishment, Objective, Organization, Powers and Leadership of the Office of the Chief of Administration of the Region*

***Article 4***
Establishment and Accountability of the Office of the Chief of Administration of the Region

1. The Office of the Chief of Administration of Afar National Regional State, (herein after referred to as the Office''), is hereby established as an autonomous government organ having juridical personality.
2. The Office shall be accountable to the Chief Administrator and Administrative Council of the Region in accordance with Article 61(2) of the Constitution of the Region.

**Article 5**
**Objectives**

The objective of the Office is to provide assistance for the highest organ of the Region to efficiently discharge its responsibility.

**Article 6**
**Structure**

The Office shall have professional consultants appointed to assist the Chief of Administration of the Region and Vice Chief Administrator. It shall study the organizational structure of the Office and submit to the Council of the Region to realize its objective.

***Article 7***
***Powers and Duties of the Office***

The Office shall have the powers and duties to:

1) provide general administrative services for the Chief of Administration of the Region and the Administrative Council; and ensure the fulfillment of manpower and materials necessary for such purpose;
2) render the necessary protocol to the Chief Administrator and Vice Chief Administrator; particulars shall be determined by a directive;
3) arrange halls required for regular and extraordinary meetings of Regional Administrative Council members; provide for the necessary materials and render service,
4) ensure the authenticity of the minutes and other documents of the Council and make them to be kept properly and safely;

፭· በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚወጡ ደንቦች በወቅቱ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ የሚታተሙበትንና ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት መሠራጨታ ቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።

፮· ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ከአገር ውስጥና ከውጭ ለሚመጡ የክልሉ እንግዶች በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስም ሁለገብ የመስተንግዶ አገልግሎት ይሰጣል።

፯· ለርዕሰ–መስተዳድር ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን ከርዕሰ – መስተዳድሩ ጋር የሚኖራ ቸውን የሥራ ግንኙነት በማቀላጠፍ ያግዛል።

፰· በመደበኛና በካፒታል በጀት ለሚያከናውናቸው የሥራ ፕሮግራሞች የሚያስፈልገውን ዓመታዊ የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

፱· የጽ/ቤቱ መደበኛ ዕቅዶች በመስተዳድሩ ምክር ቤቱ ስም የሚጠሩ አውደ ጥናቶች፣ ኮንፈረንሶችና ሌሎች ስብሰባ ዎችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲከና ወኑና እንዲፈፀም ያደርጋል።

፲· አስተዳደራዊ ፍትህ ጠይቆ ወደ ርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት የሚመጣ ባለጉዳይን ያለውጣ ውረድ ቅሬታውን ለማሰማት ይቻለው ዘንድ አግባብ ካለው የሥራ ኃላፊ ወይም ባለሥልጣን ጋር በወቅቱ የሚገናኝበትን አመች የአሰራር ስልት ቀይሶ በሥራ ላይ ያውላል።

፲፩· የበታች አስተዳደር ጽ/ቤቶችን በሰው ኃይል ስልጠናና በቁሣቁስ አቅርቦት እንደ አስፈላጊነቱ ይደግፋል ያጠና ክራል።

፲፪· በየደረጃው ባሉ አስተዳደራዊ ጽ/ቤቶች ዘንድ እቅድ የማውጣት ተግባራዊ የማድረግና አፈፃፀሙን የመገ ምገም ባህል በሠራተኛው ዘንድ እንዲኖር አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል።

፲፫· የንብረት ባለቤት ይሆናል። ውል ይዋዋላል በስሙ ይከሳል ይከሰሳል።

፲፬· ሌሎች ከጽ/ቤቱ ሥራ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ ፰

ስለጽሕፈት ቤቱ አመራርና ተጠሪነት

፩· ጽሕፈት ቤቱ በርዕሰ–መስተዳድሩ በሚሾም አንድ የበላይ ኃላፊ ይመራል።

፪· የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

አንቀጽ ፱

የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

፩· የጽ/ቤቱ ኃላፊ ከርዕሰ መስተዳድሩ በሚሰጠው አመራር መሠረት የጽ/ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል ጽ/ቤቱን ያስተዳድራል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጽ/ቤቱ ኃላፊ፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ስር የተመለከቱ የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል።

ለ) የጽ/ቤቱን ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በአገሪቱ የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል ያስተዳ ድራል።

ሐ) የጽ/ቤቱን ዓመታዊ በጀት የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለርዕሰ – መስተዳድሩ ያቀርባል። ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።



5) follow up and supervise that the Regulations issued by th Council, and the publication of same in the Regional Negarit Gezeta and their distribution to the concerned government organs is made timely;
6) render all rounded reception services for guests from within and abroad on behalf of the Administrative council; the particulars shall be determined by a directive to be issued;
7) identify the executive office accountable to the Office of the Chief of Administration of the Region and assist to make efficient the work relation ship with the Chief of Administration of the Region;
8) prepare the draft of annual budget it needs for its work plan to be accomplished by recurrent and capital budget and implement same upon approval;
9) cause the accomplishment of the regular plans of the Office and conducting of workshops, conferences and other meetings convended by the council in accordance with the schedule set for them;
10) devise mechanism and implement same to facilitate conditions to enable the clients who come to the Office of the Chief of Administration of the Region seeking justice to lodge their complaints with concerned head or authority without difficulties.
11) support and reinforce lower administrative offices by providing manpower training and material, as may be necessary;
12) make the necessary effort to enable workers at every level of administrative offices to develop the culture of work planning and evaluating its implementaion;
13) own property; make contracts, sue or be sued;
14) carry out such other duties related to the activities of the Office;

*Article 8*

*Leadership and Accountability of the Office*

1) The Office shall be direcçted by a head appointed by the Chief Administrator of the Region;
2) The Head of the Office shall be accountable to the Chief administrator of the Region.

*Article 9*

*Powers and Duties of the Head of the Office*

1. The Head of the Office shall direct over all activities of the Office and administer same in accordance with the order given to him by the Chief Administrator of the Region.
2. Without prejudice to the generality of the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the head of the Office shall:
   (a) carry out powers and duties specified under Article 7 herein; Employ and administer the support giving staff of the Office in accordance with the civil service Law of the country;
   (b) prepare and submit the annual budget and work plan of the Office to the Chief Administrtion of the Region and implement same upon approval;
   (c) prepare and submit the annual budjet and work plan of the Office to the Chief Administrator of the Region and implement same upon approval.

መ) ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል።

ሠ) ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ስር በተሰጠው የስልጣን ክልል ተወስኖ ከሌሎች አካላት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ጽ/ቤቱን ይወክላል።

ረ) የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሒሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል።

ሰ) በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከና ውናል።

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፲**
**የጽ/ቤቱ በጀት**

የጽ/ቤቱ በጀት በክልል መንግሥት የሚመደብ ይሆናል።

**አንቀጽ ፲፩**
**የሒሣብ መዛግብት**

፩· ጽ/ቤቱ ትክክለኛና የተሟሉ የሒሣብ መዛግብት ይይዛል

፪· የጽ/ቤቱ የሒሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየዓመቱ ይመረመራል። ሆኖም ርዕሰ መስተዳድሩ አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነበት ጊዜ ምርመራው በከፊልም ሆነ በሙሉ በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በልዩ ሁኔታ እንዲመረመሩ ሊያዝ ይችላል

**አንቀጽ፲፪**
**የተሻሩ ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**አንቀጽ ፲፫**
**ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ደንቦችና መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

**አንቀጽ ፲፬**
**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ
ሰኔ — ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም
ኢስማኢል አሊ ሲሩ
የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር

(d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work plan of the office;

(e) represent the Office in all its dealings with third parties, within the power given to him in Article 7 of this Proclamation;

(f) prepare and submit the Office's performance and financial report to the Chief Administrator of the Region;

(g) carry out such other activities as are assigned to him by the Chief Administrator of the Region;

## PART THREE
## *Miscellaneous Provisons*

*Article 10*

*The budget of the Office shall be allocated and approved by the Regional Government.*

*Article 11*
*Books of Accounts*

1) The Office shall keep complete and accurate books of accounts.

2. the Office's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor General of the Region. The Chief Administrator of the Region may, however, order partial or complete auditing by the Auditor General at any time if he deems it necessary.

*Article 12*
*Inapplicable Laws*

No any law or customary practices which are inconsistent with this Proclamation shall have effect in respect of matters provided for in this Proclamation.

*Article 13*
*Power to Issue Regultions and Directives*

The Region's Administrative Council may issue regulations and directives necessary for the implementation of this Proclamation.

*Article 14*
*Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Negarit Gazeta of the Afar National Regional State.

Done at Semera, this — day of —/2002

Ismail Alisero

Chief Administrator of Afar National Region State

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር —
ሠመራ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. —
SEMERA – July, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ............................. ገጽ ፩

## CONTENTS

Proclamation No. 17/2002
The Establishment of the Office of Afar National Regional State Council and Definition of its Powers and Duties Proclamation ............................. Page 1

### አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፬ ዓ.ም.
### የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ጽ/ቤትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የክልል ም/ቤት ካስፈፃሚው አካል የአሠራር ተፅዕኖ ተላቆና ራሱን ችሎ እንዲዋቀርም ሆነ የራሱን ነፃ አመራር እንዲኖረው በተሻሻለው የ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ሕገ መንግሥት የተወሰነ በመሆኑ፣

በዚህም የተነሣ የክልል ም/ቤቱ በሕገ-መንግሥቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ፈርጅ የራሱን ጽ/ቤት ፣ ማደራጀትና ሥልጣንና ተግባሩን በህግ መወሰን ተገቢ ሆኖ በመገኘት፣

እንዲሁም በክልሉ ውስጥ የህዝብ አስተዳደርን፣ የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶች የዕለት ከዕለት አሠራርና ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በዚሁ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት አማካኝነት መከታተልና መደገፍ የማይታለፍ ተግባር ሆኖ በመገኘቱ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ተሻሽሎ በወጣው ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፫/ሀ/ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀፅ ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF OFFICE OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE COUNCIL AND DFINITION OF ITS POWERS AND DUTIES

WHIREAS, it has been provided in the Revised Constitution of 2002 that the Afar National Regional Council be reorganized independently of the Executive Organ;

WHEREAS, it has become appropriate to establish, organize and define powers and duties of the Office of the Afar National Regional State Council so that the Council of the Region will be able to efficiently discharge its multi responsibilities entrusted to it by the Constitution,

WHEREAS, it is indispensable to follow up and support public administration in the Region, day-to-day functions and activities of the Woreda and Kebele Councils in,

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 47 sub Article 3/A/ of the Revised Constitution of 2002 of the Council of the Afar National Regional State, it is hereby proclaimed as follows;

### PART ONE
### *GENERAL PROVISION*

*Article 1. Short Title*

This Proclamation may be cited as the establishment of the Office of Afar National Regional State Council and Definition of its Powers and Duties Proclamation No. 17/2002.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 5.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፵
Negarit G.P.O.Box 40

## ክፍል ሁለት

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩· "የክልል ምክር ቤት" ማለት በ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ተሻሽሎ በወጣው የአፋር ብሔራዊ ክልል ሕገ–መንግስት አንቀጽ —— ሥር የተቋቋመውና ዝርዝር ሥልጣንና ተግባሩ የተገለፀው አካል ነው።

፪· "አፈ–ጉባዔ" ማለት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ሕገ–መንግሥት አንቀጽ— ንዑስ አንቀጽ —— መሠረት ከክልሉ ም/ቤት አባላት መካከል ተመርጦ ለም/ቤቱ የሥራ ዘመን እንዲያገለግል የተሰየመ ባለሥልጣን ወይም የሕዝብ ባለአደራ ሲሆን እንደ አግባብነቱ የክልል፣ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች አፈ–ጉባዔዎችንም ይጨምራል።

፫· ጽ/ቤት ማለት የክልል ም/ቤቱ ጽ/ቤት ነው።

## ክፍል ሦስት

## ስለ ክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤት መቋቋም፣ ዓላማ አደረጃጀትና ተልዕኮ

### አንቀጽ ፫· ስለ መቋቋም

፩· የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ "ጽህፈት ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ተጠሪነቱ ለአፈ–ጉባዔው ይሆናል።

### አንቀጽ ፬· ዓላማ

የጽ/ቤቱ ዓላማ ም/ቤቱና አመራሩ በሕገ–መንግሥቱ የተጣለ ባቸውን ሕዝባዊ አደራና ኃላፊነት በብቃትና በታማኝነት ተልዕኳቸውን እንዲወጡ ማስቻልና ማሳካት ነው።

### አንቀጽ ፭· የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩· የክልል ም/ቤት አፈ–ጉባዔ ጽ/ቤት በመሆን ያገለግላል፣

፪· ለክልሉ ም/ቤትና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎቹ ሁለገብ አገልግሎት ይሠጣል፣

፫· ለክልሉ ም/ቤትና ኮሚቴዎቹ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ያሰናዳል፣ ያደራጃል፣ የመገልገያ ቁሳቁሶችን ያሟላል፣

፬· የም/ቤቱና ኮሚቴዎቹ ቃለ ጉባዔዎች፣ ውሣኔዎችና ሰነዶች በሚገባ ተመዝግበው እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣

፭· ለክልሉ ም/ቤት አባላትና አካላቱ የቤተ–መጻህፍት፣ የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ይሠጣል፣

፮· የክልሉ ም/ቤት በየጊዜው የሚያወጣቸው አዋጆችና ደንቦች በቅርጽም ሆነ በይዘት በወቅቱ ተሟልተውና ተስተካክለው በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙና ለሚመለከታቸው አካላትም ሆነ ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዲሰራጩ ያደርጋል፣

፯· በክልሉ ም/ቤት የሚወጡ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና በራሪ ጽሁፎች ዝግጅት ህትመትና ስርጭት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣

፰· ከአፈ–ጉባዔው በሚሰጠው አመራር መሠረት የም/ቤቱን አባላትና ተጋባዥ እንግዶችን ይቀበላል፣ ተፈላጊው የመስተንግዶ አገልግሎት ተሟልቶ የቀረበላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

፱· የክልሉን ም/ቤት ጨምሮ የየደረጃው ም/ቤት አባላት አቅም የሚጐለብትበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ፣ ይደግፋል፣



## PART TWO

2. *Definitions*

Unless the context requires otherwise in this Proclamation:

1) "Regional Council" means a body established under Article... of the Revised Constitution of 2002 of the Sub-Article....Afar National Regional State and whose powers and duties are stated in it;
2) "Speaker" means an official appointed in accordance with Sub-Article... of Article... of the Constitution, from among members of the Regional Council to serve for terms of the Council, and it includes Regional, Woredas and Kebele Council's speakers as may be aproppirate;
3) "Office" means the Afar Regional Council Office.

## PART THREE

## *Establishment, Accountability, Objective, Organization and Mission of the Office of the Regional Council*

*Articl 3. Establishment*

1) The Office of Afar National Regional State Council hereinafter referred to as "the Office" is hereby eatbalished as an autonomous organ that has legal entity.
2) The Office shall be accounable to the Speaker.

Article 4. *Objective*

The fundamental objective of the Office of the Regional Council is to enable the Council and its leadership to discharge, efficiently and loyally, the mandate of the people and legal responsibility entrusted to them by the constitution and materialize thier mission.

Article 5. *Powers and Diuties of the Office*

The Office of the Afar National Regional State Council shall have the powers and duties to:

1) serve as the office of the Speaker of the Regional Council;
2) provide general services to the Regional Council and its various committees
3) arrange and organize meeting halls of the Regional Council and committees; and provide necessary materials;
4) cause minutes, decisions and documents of the Council and committees be recorded and kept properly;
5) provide library, research and information services to bodies of the council and its members;
6) cause the Proclamation and Regulations issued by the Regional Council and their publication in the Region's Gazeta and dissemination to the concerned organ and various social categories done;
7) direct and follow up the preparation, publication and circulation of newspapers, periodicals and brochures that are issued by the Regional Council;
8) give reception to members of the Council and invited guests based on directives of the Speaker and ensure proper service is rendered;
9) create conducive condition to enhance the capacity building of members of the Councils at every level, and support the same;

፲· በተዋረድ ጽ/ቤቶች የሚሠሩ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን አያያዝና አስተዳደር በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፩· ምክር ቤቱ ያሳለፋቸው ውሣኔዎች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፣

፲፪· የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፲፫· የክልሉን ም/ቤት ሥራ ለማሳካት የሚረዱና በአፈ–ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

**አንቀጽ ፮· ስለ ጽ/ቤቱ አደረጃጀት፣ አመራርና ተጠሪነት**

፩· ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶቹን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ በአፈ–ጉባዔው አማካኝነት ያስወስናል፣

፪· ጽ/ቤቱ በክልሉ ም/ቤት አፈ–ጉባዔ በሚሾም አንድ የበላይ ኃላፊ ይመራል፣ ይተዳደራል፣

፫· የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለአፈ–ጉባዔው ይሆናል፣

**አንቀጽ ፯· የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር**

የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ስር ለጽሕፈት ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

፪· ከአፈ–ጉባዔው በሚሰጠው አመራር መሠረት የጽ/ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፫· የጽ/ቤቱን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሕጐችና ደንቦች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

፬· የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለአፈ–ጉባዔው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

፭· የጽ/ቤቱን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣ የተፈቀደውን በጀት መሠረት የፋይናንስ ሕግን መሠረት አድርጐ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

፮· ከአፈ–ጉባዔው በሚሰጠው አመራር መሠረት ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፣

፯· የጽሕፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት ለአፈ–ጉባዔው ያቀርባል፣

፰· በአፈ–ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣

፱· ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል ከተግባሩ ከፊሉን በውክልና ለጽ/ቤቱ የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ለሌሎች ሊያስተላልፍ ይችላል።

**ክፍል አራት**
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**አንቀጽ ፰· በጀት**

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በክልሉ ም/ቤት የሚመደብ ይሆናል።

**አንቀጽ ፱· የሂሣብ መዛግብት**

፩· የጽሕፈት ቤቱን የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣

፪· የጽሕፈት ቤቱን የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር አማካኝነት በየጊዜው ይመረመራሉ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ አፈ–ጉባዔው የጽ/ቤቱ ሂሳብ ወይም ንብረት ነክ መዛግብትና ሠነዶች በልዩ ሁኔታ እንዲመረመሩ ሊያዝ ይችላል።

10) follow up and supervise overall management and administration of the support giving staff at every level;

11) forward the decisions passed by the Council to concerned bodies timely;

12) own property, enter into contracts, sue and be sued in is own name;

13) caryy out such other relevant activities necessary to materialize the functions of the council and other related duties given by the Speaker.

*Article 6. Organization, Management and Accountability of the Office*

1) The Office shall study the organization structure necessary to implement its powers and duties provided under Article (7) of this Proclamation and through the Speaker for approval.

2 The Office shall be directed and administered by a Chief appointed by the Speaker of the Regional Council.

3) The Chief of the Office shall be accountable to the Speaker.

*Article 7. Powers and Duties of Chief of the Office*

The Chief of the Office shall have the powers and duties to:

1) carry out the powers and duties that are given to the Office under Article (7) of this Proclamation;

2) direct, coordinate and supervise overall activities of the Office pursuant to the directives given to him by the Speaker;

3) employ and administer personnel of the Office in accordance with Civil Service Laws and Regulaltions;

4) perpare and submit to the Speaker the annual budget and work plan of the Office, and implement same upon approval;

5) operate accounts of the Office, based on financial laws, effect expenditure in accordance with the approved budget and work plan;

6) represent the Office in all its dealings with third parties in accordance with the directives given to him by the Speaker;

7) prepare and submit activity and finacial report of the Office to the Speaker;

8) implement other duties given by the Speaker;

9) delegate part of his power and duties to subordinate officials of the Office to the extent necessary for the efficiency of the Office's works.

PART FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

*Article 8. Budget*

The budget of the Office shall be allocated by the Regional Council.

*Article 9 Books of Accounts*

1) The Office shall keep complete and accurate books of accounts.

2) The books of accounts and financial documents shall be audited from time to time by the Auditor General of the Region.

3) Without Prejudice to Sub-Article (2) of this Article the Speaker may at any time and conditions order the auditing of the books and documents of accounts and property be conducted in a special condition,

**አንቀጽ ፲· የተፈጻሚነት ወሰን**

፩· አግባብነት ያላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በተዋረድ ም/ቤቶች ጽ/ቤቶች ኃላፊዎችና አሠራር ላይ እንዳስፈላጊነቱ ተፈፃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

፪· የየደረጃው ም/ቤቶች ሕገ–መንግሥታዊ አቋምና የአሠራር ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ የም/ቤት ጽሕፈት ቤታቸውን ለዚህ አዋጅ አላማና አፈፃፃም የክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ቅርንጫፎች ናቸው።

**አንቀጽ ፲፩· ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉትን ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**አንቀጽ ፲፪· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ — ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም·

ኢስማኤል አሊ ሲሩ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ርዕሰ መስተዳድር

***Articl 10. Scope of Applicability***

1) Appropirate provisions of this Proclamation may apply to the head of the offices of the subordinate councils and their activities, as may be necessary.
2) Without prejudice to the Constitutional structure and independency of the councils at hierarchical level, the offices of councils shall be branches of the Office of the Regional Council for the purpose of the objectives and implementation of this Proclamation.

***Article 11. Power to Issue Regulation***

The Regional Council may Issue Regulation necessary for the Implementation of this Proclamation

**Article 12. *Effective Date***

This Proclamation shall enter into force as of the date of June Done at Semera, this.....day of..../2002

Done at Semera, this — day of June /2002

Ismal Ali Sero

Chief Administrator of

Afar National Regional State

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
# AFAR REGION NEGARIT GAZETA
## OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር
ሠመራ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No.
SEMERA –7th July, 2004

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
"የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፬ ዓ.ም." ........................ ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 15/2002
Reorganization of the Executive Organ of Afar National Regional Stat and Definition of Their Powers and Duties Proclamation No.15/2002 Page 1

አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፬

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣

የአርብቶ አደሩን ኑሮ በተሻለና ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመምራትና ለውጥ ለማምጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡ የክልሉን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲን በተቀናጀ መልኩ በመምራት ቀልጣፋ የመንግሥት አገልግሎት ለክልሉ ኅብረተሰብ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

የቀድሞው የክልል አስፈጻሚ አካል አደረጃጀት ለሥራ ጥራትና ቅልጥፍና አመች የነበረ ባለመሆኑ ፤

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፫/ሀ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀፅ ፩

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፬ ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

ክፍል ሁለት

አንቀፅ ፪

ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩· "ሕገ–መንግሥት" ማለት የ፲፱፻፺፬ የተሻሻለው የአፋር ክልል ሕገ–መንግሥት ነው ።
፪· "ማስተባበሪያ ቢሮ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተለያዩ ቢሮዎችንና ሌሎች መሥሪያ ቤቶችን በበላይነት የሚመራ ማለት ነው ።

Proclamation No, 15/2002

*PROCLAMATION TO REORGANIZE THE EXECUTIVE ORGANS OF AFAR NATIONAL REGIONAL STATE AND TO DEFINE THIER POWERS AND DUTIES*

WHEREAS, it is found necessary to lead the life of pastoralists in a better and sustainable way and provide the people of the region with improved public service through integrated social and economic development policy;

WHEREAS, the preceding organization of the executive organ is not conducive to improve the quality and effectiveness of activities;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 47 (3) (a) of the Revised Constitution of the Afar National Regional State, it is hereby proclaimed as follows.

*PART ONE*
*General Provision*

Article 1

*Short tiltle*

This Proclamation may be cited as the "Reorganization of the Executive Organ of Afar National Regional Stat and Definition of Their Powers and Duties Proclamation No.15/2002.

*PART TWO*

Article 2

*Definitions*

In this proclamaion:

(a) "Constitution" means the 2002 Revised Constitution of Afar National Regional State;
(b) "Coordinating Bureau" means, in accordance with this Proclamation, a body that is a chief supervisor of various bureaux and other offices,

ያንዱ ዋጋ 21.75
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፵
Negarit Gazeta P.O.Box 40

## ክፍል ሦስት
## ስለክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባለተ

አንቀፅ ፫

የክልል መስተዳድር ምክር ቤት

፩· የክልል መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ።
   ሀ) ርዕሰ መስተዳድር
   ለ) ምክትል ርዕሰ መስተዳድር
   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተመለከቱት የቢሮዎች ኃላፊዎች
   መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ሥር ከተመለከቱት ውጭ ርዕሰ መስተዳድሩ ምክር ቤት አባላት እንዲሆኑ በተለይ የሚመርጣቸው ሌሎች የቢሮ ኃላፊዎችና ባለሥልጣናት ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሐ/ ሥር የተመለከተው ማንኛውም ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችል በት ጊዜ ምክትል የቢሮ ኃላፊው ወይም በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ወኪል በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በምክትል አባልነት ይሳተፋል ።

አንቀፅ ፬

ስለቢሮዎች መቋቋም

የሚከተሉት ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል ።

፩· የአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ
፪· የአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ
፫· የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ
፬· የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ
፭· የአስተዳደርና ፍትሕ ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ
፮· የማስታወቂያና የሕዝብ አደረጃጀት ማስተባበሪያ ቢሮ
፯· የእንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ቢሮ
፰· የትምህርት ቢሮ
፱· የጤና ጥበቃ ቢሮ
፲· የፍትሕ ቢሮ
፲፩ ·የባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ
፲፪ የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ

አንቀፅ ፭

የቢሮዎች ተጠያቂነት

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ሥር የተዘረዘሩት ቢሮዎች መስተዳድሩ ም/ቤት ለሚያሳልፈው ውሣኔ የጋራ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት አለባቸው ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ቢሮ የተቋቋመ በትን ዓላማ መሠረት በማድረግ በዚህ አዋጅ ተለይተው የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች የመወጣት ግዴታ አለበት።

አንቀፅ ፮

የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተጠያቂነት፣

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ/ እና /ሐ/ መሠረት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን ጨምሮ የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት የሆኑ ቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ሥር የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሐ/ መሠረት የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሆነው የሚመሯቸው ቢሮዎች ተጠሪነት ለማስተባበሪያ ቢሮዎች ጭምር የሆነ የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነት ለማስተባበሪያው ቢሮ ኃላፊ /ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ሥር ከተመለከቱት ውጭ ያሉና በዚህ አዋጅ መሠረት የክልል መስተዳድር ም/ቤት አባላት ያልሆኑ የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለሚመለከተው ማስተባበሪያ ቢሮና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል ።

## *PART THREE*
## *REGIONAL ADMINISTRATIVE COUNCIL*

*Article 3*

*Reginal Administrative Council Members*

1) The Regional Administrative Council shall have the following members:
   (a) Chief Administarator;
   (b) Vice Chief Administrator;
   (c) heads of bureau specified under Article 4 of this Proclamation;
   (d) heads of bureau and authorities other than those specified under Article 4 of this Proclamation to be assigned by the chief administrator.
2) Where any head of bureau referred to in Sub-Article 1(c) of this Article is unable to attend the meetings of the council, his deputy or representative specifically delegated shall take part in the meetings of the council.

Article 4

*Establishment of Bureau*

The following Bureau are established by this Proclamation:

1) Pastoralist Rural Development Coordination Bureau;
2) Capacity Building Coordination Bureau;
3) Trade, Industry and Urban Development Coordination Bureau;
4) Finance and Economic Development Coordination Bureau;
5) Administration and Justice Affairs Coordination Bureau;
6) Information and Public Organization Coordination Bureau;
7) Livestock and Natural Resource Development Conservation Bureau;
8) Education Bureau;
9) Health Bureau;
10) Justice Bureau;
11) Culture, Tourism and Information Bureau;
12) Water, Mines and Energy Resource Development Bureau.

Article 5

*Responsibility of Bureau*

1) The Bureau specified under Article 4 of this Proclamation shall have common responsibility and accountability for a decision passed by the council.
2) Without prejudice to Sub-Article 1 of this Article, each Bureau based on the objectives it is established, has the obligation to carry out the duties and responsibilities specifically vested to it by this Proclamation.

Article 6

*Accountability and Responsibility of Heads of Bureau*

1) In accordance with Article 3 Sub-Article 1(a) and (c) of this Proclamation, heads of bureau who are members of the council, including the Vice Chief Administrator, shall be accountable to the Chief Administrator and the Administrative Council of the Region.
2) Notwithstanding the provision under Sub-Article 1 of this Article heads of bureau who are members of the council in accordance with Article 3 Sub-Article (c) of this Proclamation and the bureau under their leadership are also accountable to coordinating bureau, shall be accountable to the Head of Coordinating Bureau, the Chief Administrator of the Region and the council.
3) heads of bureau who are not members of the council and are not included in the specifications under Sub-Article 1 and 2 of this Article, shall be accountable to the concerned coordinating bureau and the Chief Administrator.

፬. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፫ ከተመለከቱት ውጭ ያሉ ኮሚሽኖች የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች ፣ ጽ/ቤቶች ፣ የልማት ተቋማትና ድርጅቶች ኃላፊዎች ተጠሪነት እንደአግባብነቱ ለሚመለከተው ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ወይም ለርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ይሆናል ።

አንቀፅ ፯

<u>የአስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት፣</u>

፩. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ።
  - ሀ) የእንስሳትና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ቢሮ
  - ለ) የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ቢሮ
  - ሐ) የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ምግብ ዋስትና ቢሮ
  - መ) የገጠር መንገድ ባለሥልጣን
  - ሠ) የመስኖ ልማትና የውሃ ኮንስትራሽን ባለሥልጣን
  - ረ) የግብርና ምርምር ማዕከል
  - ሰ) የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን

፪. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ።
  - ሀ) የትምህርት ቢሮ
  - ለ) የጤና ጥበቃ ቢሮ
  - ሐ) የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ
  - መ) የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ጽ/ቤት
  - ሠ) የሥራ አመራር ማሠልጠኛ ተቋም
  - ረ) የአፋርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ማዕከል

፫. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ።
  - ሀ) የንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ
  - ለ) የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ
  - ሐ) የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

፬. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ።
  - ሀ) የሥነ-ሕዝብ ጽ/ቤት
  - ለ) የገቢዎች ጽ/ቤት

፭. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአስተዳደርና ፍትሕ ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ።
  - ሀ) ፍትሕ ቢሮ
  - ለ) የፖሊስ ኮሚሽን
  - ሐ) የሚሊሺያ ጽ/ቤት
  - መ) የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት
  - ሠ) ወሰን ጉዳይ ጽ/ቤት

፮. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለማስታወቂያና የሕዝብ አደረጃጀት ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ።
  - ሀ) የባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ
  - ለ) የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ
  - ሐ) የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት
  - መ) የሕዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት ጽ/ቤት
  - ሠ) የሠፈራ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
  - ረ) የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት

፯. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ይሆናል ።
  - ሀ) የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ
  - ለ) የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት



4) Heads of commissions, authorities, offices, development institutions and organizations that are not included in the specifications under Sub-Article 1 to 3 of this Article shall be accountable, as shall be proper, to the head of concerned coordinating office or to the office of Chief Administrator.

Article 7

*Accountability of Executive Bodies*

1) The following executive bodies shall be accountable to Prastoralist Rural Development Coordination Bureau:
   - (a) Livestock and Natural Resource Development Conservation Bureau;
   - (b) Cooperative Associations Extension Bureau;
   - (c) Disaster Prevention and Preparedness Food Security Bureau;
   - (d) Rural Roads Authority;
   - (e) Irrigations Development and Water Construction Authority;
   - (f) Agricultural Research Center;
   - (g) Environmental Protection Authority;

2) The following executive bodies shall be accountable to Capacity Building Coordination Bureau:
   - (a) Education Bureau;
   - (b) Health Burea;
   - c) Civil Service Bureau;
   - d) Civil Service Reform Program Office;
   - e) Management Training Institute;
   - f) Afar Language Promotion Center.

3) The following executive bodies shall be accountable to Trade, Industry and Urban Developmnt Coordination Bureau:
   - (a) Trade, Industry and Transport Bureau;
   - (b) Work and Urban Development Bureau;
   - (c) Investment office.

4) The following executive bodies shall be accountable to Finance and economic development Coordination Bureau:
   - (a) Population Office;
   - (b) Revenues Office;

5) The following executive bodies shall be accountable to Administration and Justice Affairs Coordination Burea:
   - (a) Justice Bureau;
   - (b) PoliceCommission;
   - (c) Militia Office;
   - (d) Prisons Administration Office;
   - (e) Boundary Affairs Office.

6. The following execuutive bodies shall be accountable to Information and Public Organization Affairs Coordination Bureau.
   - (a) Culture, Tourism and Information Bureau;
   - (b) Labour and Social Affairs Bureau;
   - (c) Youth and Sports Affairs Office;
   - (d) Public Participation and Organization Office;
   - (e) Resettlement Program Coordination Office;
   - (f) Women's Affairs Office.

7. The following executive bodies shall be accountable to the Office of Chief Administrator.
   - (a) Water, Mines and Energy Resource Development Bureau;
   - (b) HIV/AIDS Pevention and Cntrol Secretariat Office.

## ክፍል አራት
## የቢሮዎች ሥልጣንና ተግባር

**አንቀፅ ፰**

**የአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ**

የአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡፡

፩· የክልሉን አርብቶ አደር የኑሮ ሁኔታ የተሻለ ለማድረግ ፖሊሲዎችን ያመነጫል ፣ የሥራ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል ፡፡

፪· በክልሉ ውስጥ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ የሚሆኑበት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ፡፡

፫· የገጠር ልማትን ሊያፋጥኑ የሚችሉ ፖሊሲዎችን ያመነጫል ፣ የሥራ ፕሮግራሞችና በጀት ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድለትም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ፡፡

፬· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯/፩/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላትና የልማት ተቋማትን በበላይነት ይመራል ፣ ያስተባብራል ፣ ይቆጣጠራል ፡፡

፭· የአርብቶ አደሩን ልማት ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

**አንቀፅ ፱**

**የአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ፣**

የአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፡፡

፩· የክልሉን የአቅም ግንባታ ፖሊሲዎች ያመነጫል ፣ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል ፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ፡፡

፪· ለክልሉ አቅም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን እንዲ መሠረቱና እንዲደራጁ ይደረጋል ፡፡

፫· በቢሮዎችና መሥሪያ ቤቶች ለሚከናወኑ የአቅም ግንባታ ተግባሮች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ፡፡

፬· የክልሉ ቋንቋ እንዲዳብር አስፈላጊውን የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል ፡፡

፭· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯/፪/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላትና የልማት ተቋማት በበላይነት ይመራል ፣ ያስተባብራል ፣ ይቆጣጠራል ፡፡

፮· የአቅም ግንባታ ለማጠናከር የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል ፡፡

**አንቀፅ ፲**

**የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ**

የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡፡

፩· የአገሪቱን የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ፖሊሲ ዎችን ያመነጫል ፣

፪· የክልሉን ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ደረጃ በደረጃ የሚለወጥበትን ፖሊሲ ያመነጫል ፣ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፡፡

፫· ለአነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ሥራዎች መስፋፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ፤

፬· የግል ባለሀብቶችን በክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ተገቢውን ሚና መጫወት የሚያስችላቸው ፕሮግራሞች መነደፋቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል ፡፡

፭· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯/፫/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ፣ ያስተባብራል ፣ ይቆጣጠራል ፡፡

፮· ለንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ማደግ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ያከናውናል ፤

**አንቀፅ ፲፩**

**የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ**

ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡፡

፩· የክልሉ መንግሥት አካላት የአገሪቱን የፋይናንስ ፖሊሲዎች ፣ ሕጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል ፡፡



## *PART FOUR*
## *POWERS AND DUTIES OF BUREAU*

Article 8

The Pastoralist Rural Development Coordination Bureau

The Pastoralist Rrural Development Coordination Bureau shall have the powers and duties to:

1) initiate policies, prepare work programs and execute them to make better the living condition of pastoralists;
2) facilitate conducive condition for implementation of food security programs in the region;
3) initiate policies that can speed up rural development, prepare work programs and budget, implement upon approval;
4) direct, coordinate and supervise executive bodies and development institutions specified under Article 7(1) of this Proclamation;
5) perform such other duties that would help to extend the development of pastoralists.

Article 9

*Capacity Building Coordination Bureau*

The Capacity Building Coordination Bureau shall have the powers and duties to:

1) Initiate the region's capacity building policies prepare programs and budget, and implement same upon approval;
2) ensure that the necessary institutions are established and organized for the regions capacity building;
3) render the necessary support for capacity building functions performed in bureaux and offices;
4) make necessary capacity building activities to promote the region's language;
5) supervise, direct and coordinate the executive bodies and development institutions specified under Article 7(2) of this proclamation;
6. Perform such other duties that help strengthen capacity building.

Article 10

*Trade, Industry and Urban Development Coordination Bureau*

Trade, Industry and Urban Development Coordination Bureau shall have the powers and duties to:

1) initiat and execute the region's trade, industry and urban development policies;
2. Initiate a policy to change the region's economy into industrial economic sector setp by step prepare program and budget and implement same upon approval;
3) Facilitate conducive environment for expansion of small and micro trading activities;
4) ensure that programs that enable investors play proper role in the region's economy are provided and implemented;
5) direct, supervise and coordinate executive bodies specified under Article 7(3) of this Proclamation.
6) perform such other duties necessary for enhancement of trade, industry and urban development.

Article 11

*Finance and Economic Development Coordination Bureau*

The Finance and Economic Development Coordination Bureau shall have the powers and duties to:

1) supervise whether the region's government bodies perform their functions in accordance with policies, laws, regulations and directives of the region;

፪· በክልሉ መንግሥት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ጥያቄዎች መርምሮ የክልሉን የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ከአስተያየቱ ጋር ለክልሉ መንግሥት ምክር ቤት ያቀርባል ፤ የተፈቀደውን በጀት ያስተዳድራል ።

፫· የክልል መንግሥቱን የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታ የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለክልል መንግሥት ምክር ቤት ያቀርባል ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ።

፬· የክልሉ መንግሥት ከሀገር ውስጥ የብድር ምንጮች የሚያገኛቸውን ብድሮች በክልል መንግሥት ስም ይፈራረማል ፤ ብድሮችንም እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል ።

፭· የክልለ መንግሥቱን የዕቃና የአገልግሎት ግዥና አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል ፤ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል ።

፮· በአገሪቱ የልማት ስትራቴጂ ላይ የተመሠረተና በክልሉ መንግሥት የሚፈጸም የረጅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል ።

፯· ከፌዴራል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በተገባው ውል መሠረት በክልሉ የሚካሄዱትን የልማት ትብብር ሥራዎችን ያስተባብራል ፤ በልማት ትብብር ፕሮጀክቶች ዝግጅት ሥራ ይሳተፋል ።

፰· በክልሉ መንግሥት እንዲሠሩ የሚያስችል ፈቃድ ያላቸውን መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ሥራ ያስተባብራል ፤ ስለሥራቸው አፈጻጸም ብቃታቸውን ይቆጣጠራል ።

፱· የክልል መንግሥቱን ሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይዘረጋል ።

፲· የማናቸውንም የክልሉ መንግሥት አካላት የሂሣብ መዛግብቶች ፤ ሠነዶችና ማስረጃዎችን ይመረምራል ።

፲፩· ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር በክልሉ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ተሣትፎ እንዲበረታታ ድጋፍ ሰጪ የሆኑ አመልካች ዕቅድ ያዘጋጃል ።

፲፪· የክልሉን የረጅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት ዕቅድ ለማዘጋጀትና ይህንኑ የሚረዳ የኢኮኖሚ ጥረትና ምርምር ያካሂዳል ፤ የፕላን ሜቶዶሎጂና አጠቃላይ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታ መለኪያዎችንና መመዘኛዎችን ያዘጋጃል ።

፲፫· የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት ፤ የምርት ፤ የሕዝብ ፤ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ሥርጭት የአገልግሎት መረጃዎችን ያሰባስባል ፤ ያጠናክራል ፤ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል ።

፲፬· የየሴክተሩን ዕቅድ አፈጻጸም እየገመገመ የተቀነባበረ ሪፖርት በየሦስት ወሩ ለክልል መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል ።

፲፭· በክልሉ የሥነ–ሕዝብ ፖሊሲ በተግባር ላይ እንዲውል ሥርዓቶችን ይዘረጋል ።

፲፮· የሥነ–ሕዝብን ሣይንሳዊ ግንዛቤ ለማዳበር የሚያግዙ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል ።

፲፯· የክልል መንግሥት ገቢዎችን በተቀላጠፈ መንገድ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓቶች ይዘረጋል ።

፲፰· የክልል ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እንዲሄድ የሚያስችል ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ያመነጫል ።

፲፱· የክልሉ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት እያደገ እንዲሄድ ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮች ያከናውናል ።

፳· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯/፬/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ፤ ያስተባብራል ።

2) prepare the region's annual budget by examining the capital and recurrent budget request that is prepared and submitted to it by the region's government bodies, and submit it together with its suggestions to the region's council and administer the approved budget:

3) submit regularly, a general explanation that shows financial performance of the region and its cash belonging to the Region's State Council, prepare and submit additional budget whenever deemed necessary;

4) sign in the name of the regional state, loans that the regional state obtains from domestic loan sources, supervise and administer the loans;

5) prepare directives for purchase and utilization of goods and services for the regional state, check implementation of same;

6) prepare long, medium and short term development plans that are based on the country's development strategy and executed by the state of the region; supervise implementation of same upon approval;

7) In accordance with the contract entered into with Federal Finance and Economic Development Ministry, coordinate development cooperation works undertaken by the region, participate in preparation of development cooperation projects;

8) Coordinate licensed non-governmental philanthropic organizations activities in the regional state, supervise their efficiency;

9) Establish accounting procedures of the regional state;

10) Examine books of accounts, documents and evidences of any organ of region's government body;

11) In relation with economic policy of the country, prepare supportive indicating plans to encourage the private economic sector participation in the region.

12) Exert economic effort and conduct research that may help prepare long, medium and short term development plan of the region, prepare plan methodology and measurements or the general economic and social conditions;

13) Collect, organize and transfer to relevant bodies evidences on dissemination and services of natural resources, production, population and science and technology in the region;

14) Evaluate plan performance of each sector and submit an organized report to the regional state council quarterly;

15) Arrange procedure to implement population policy of the region;

16. Ensure that research that help to raise the scientific awareness of the people about population are conducted;

17) Arrange follow up and supervision procedure that enable to collect the region's revenue promptly;

18. Initiate policies and strategies that enable to promote the region's revenue from time to time;

19) Perform such other duties necessary to enhance the finance and economic development of the region;

20) Direct, supervise and coordinate executive bodies specified under Article 7(4) of this Proclamation.

አንቀፅ ፲፪

የአስተዳደርና የፍትሕ ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ

የአስተዳደርና የፍትሕ ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

፩· በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የኅብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል ፤ ያረጋግጣል ።

፪· በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላት ዲሞክራሲያዊ አመለካከታቸው እንዲዳብር ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል ።

፫· ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚዋሰኑ አካባቢዎች የሚነሱ አለመግባባቶችን ሠላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ያደርጋል ።

፬· በአስተዳደር ፣ በሕዝብ ደህንነትና በፀጥታ ሥራ ጉዳዮች አግባብነት ያላቸው የፌዴራል መንግሥትና የሌሎች ክልሎች አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል ።

፭· የፍትሕ አካላትን በማጠናከር ኅብረተሰቡ የተሻለ የፍትሕ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል ።

፮· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯/፭/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ።

፯· ለፍትሕ መስፈንና ለፀጥታ መከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ።

አንቀፅ ፲፫

፲፫· የማስታወቂያና የሕዝብ አደረጃጀት ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ

የማስታወቂያና የሕዝብ አደረጃጀት ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· ኅብረተሰቡ ራሱን በልዩ ልዩ ማኅበራት እያደራጀ በልማት ሥራው ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ ያመቻቻል ፤ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ በሥርዓት የሚመራበትን ስልት ይቀይሳል ።

፪· ማኅበራት የዕርስ በርስ ተሞክሮ ልውውጥና መደጋገፍ እንዲያደርጉና በቅንጂት እንዲቀሳቀሱ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል ።

፫· ሥራ አጥነትንና ሌሎች የማኅበራዊ ዕድገት ጠንቆች ተወግደው ዜጎች አምራች ኃይል እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ።

፬· ለኅብረተሰቡ መድረስ የሚገባቸው መረጃዎች ወቅቱን ጠብቀው የሚደርሱበትንና የመረጃ አውታሮች የሚዘረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤ ሥልቶችን ይቀይሳል ።

፭· የክልሉን የባህል እና የቱሪዝም ዕድገት ለማፋጠን የሚረዱ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል ፤ ሥርዓቶችም እንዲዘረጉ ያደርጋል ።

፮· የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራጅተው መብታቸውን እንዲያስከብሩ የሚችሉበትን ፖሊሲ ያመነጫል ፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል ።

፯· ሴቶች ተደራጅተው ለመብታቸው የሚታገሉበትንና የፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥ ያለሰለሰ ጥረት ያደርጋል።

፰· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯/፮/ የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ፤ ያስተባብራል ።

አንቀፅ ፲፬

፲፬· የጤና ጥበቃ ቢሮ

የጤና ጥበቃ ቢሮ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· የአገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የክልሉ ሕዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ።

፪· በክልሉ ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል ።

፫· ስለ ሕዝብ ጤና አጠባበቅ የወጡ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል ።

፬· በየደረጃ የሚገኙ የጤና ተቋማትን የጥናትና የምርምር ማዕከላትንና የማሠልጠኛ ተቋማትን ያደራጃል ፤ ያስተዳድራል ።

Article 12

Administration and Justice Affairs Coordination Bureau

The Administration and Justice Affairs Coordination Bureau shall have the powers and duties to:

1) follow up and ensure law and order is respected and security and well-being of the society prevails in the region;
2) exert intensive effort to raise the democratic attitude of law enforcing bodies in the region;
3) make effort to settle disputes peacefully that arise in areas that border with neighboring regions;
4) deal with relevant federal government and other region's bodies with regard to administration, social welfare and people's security;
5) make the people benefit from a better justice service by strengthening justice organs;
6) direct and supervise executive bodies specified under Article 7(5) of this Proclamation;
7) perform such other duties necessary for prevalence of justice and governance of security.

Article 13

*Information and Public Organization Affairs Coordination Bureau*

The Information and Public Organization Affairs Coordination Bureau shall have the powers and duties to:

1) facilitate a way in which the society organizes itself into various associations and participate in the development works; formulate a strategy by which the public participation shall be guided;
2) exert the necessary effort to make associations exchange experiences, support each other and operate integrity;
3) facilitate conducive conditions to eradicate unemployment and other impediments of social development thereby creating productive citizens;
4) facilitate conditions and formulate strategies through which up-to-date information that has to reach the public shall be disseminated and put in place information sources;
5) see to the undertaking of researches that help prompt the development of culture and tourism of the region and set up the systems;
6) initiate a policy through which various sectors of the society organize themselves and assert their rights, implement same upon approval;
7) exert effort to enable women organize and struggle for their rights and that gender equality is ensured;
8) direct supervise and coordinate executive bodies specified under Article 7(6) of this Proclamation.

Article 14

*Health Bureau*

The Health Bureau shall have the powers and duties to:

1) prepare plans and program by which the health of people of the region shall be treated, cause the expansion of health service in the region, based on the country's health policy and implement same upon approval;
2) expand health service in the region;
3) ensure that laws, regulations and directives provided about health are respected;
4) organize and administer health institutions; research and study center, and training institutes at every level;

፭· በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶችንና የሕክምና መሣሪያዎችን ይመዘግባል ።

፮· በሀገር ውስጥ ባለሃብቶችና ድርጅቶች ለሚቋቋሙ ጤና ጣቢያዎች ፣ ክሊኒኮች ፣ የምርመራ ድርጅቶችና መድኃኒት ቤቶች ፈቃድ ይሰጣል ። በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን መስፈርት ጠብቀው መሰራታቸውን ይቆጣጠራል ።

፯· በክልሉ ውስጥ በሕዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎችን የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል ።

፰· ዝቅተኛና መካከለኛ የጤና ባለሙያዎችን ያሰለጥናል ።

፱· ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድኃኒቶችና የሕክምና ዘዴዎች ከዘመናዊ ሕክምና ጋር ተዋህደው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፤ ባለሙያዎችን ያደራጃል፤ ያበረታታል ።

፲· የጤና ፖሊሲውን መሠረት አድርጐ ሕዝቡ በሽታን በመከላከል ላይ በስፋት የሚሳተፍበትን ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችሉ ሥልቶች ይቀይሳል ፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል ።

፲፩· ለጤና አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ሥራዎች ያቅዳል ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል ።

፲፪· የሕዝብን ጤና ለመጠበቅ በሚደረግ ኳራንቲ ቁጥጥር ይሳተፋል ።

፲፫· የምግቦችንና መጠጦችን ንጽሕና ይቆጣጠራል ፤ ለጤና ተስማሚነታቸውንም ያረጋግጣል ።

አንቀፅ ፲፭

ፍትሕ ቢሮ

የፍትሕ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩· በሕግ ጉዳይ የክልል መንግሥቱን ይወክላል፤ የሕግ አማካሪ ሆኖም ይሠራል።

፪· በክልሉ መንግሥት ውስጥ በሚገኙ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ክልል ሥር በመውደቁ የወንጀል ጉዳዮች የክልሉን መንግሥት በመወከል ይከራከራል።

፫· የሕዝቡን እንዲሁም የክልሉን መንግሥት መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በማንኛውም የዳኝነት ሰጭ አካል ወይም በሽምግልና ጉባኤ ክስ ይመሰርታል። ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፤ እንደነገሩ ሁኔታም ተከላካይ በመሆን ይቀርባል።

፬· በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የመንግሥት ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን እንደዚሁም በክልሉ መንግሥት ወይም በክልሉ መንግሥት አካላት ላይ የሚቀርቡትን የፍትሐ ብሔር ክሶችና ጥያቄዎች በአግባቡ መያዛቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሪፖርት እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል።

፭· በክልሉ መንግሥት አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት የሕግ ረቂቆችን በማዘጋጀትና የሕግ አስተያየት በመስጠት ይረዳል።

፮· በማረሚያ ቤትና በማረፊያ ቤት የተያዙ ወይም የታሠሩ ሰዎች የእስርና የአያያዛቸውን ሕጋዊነት ይከታተላል፤ የሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበር ያደርጋል፤ ካለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዙ ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ያደርጋል።

፯· የወንጀል ድርጊት ምስክሮች እንደአስፈላጊነቱ ተገቢውን የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል።

፰· እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ይሰርዛል።

፱· ከሰብዓዊ መብት አጠባበቅ አንፃር የሕዝቡን ንቃተ ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴ የሕግ ትምህርት ይሰጣል። የሕግ ትምህርት ሥልጠናን በሚመለከት በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ዳኞችና ዓቃቢያን ሕግ እንዲሁም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት ለነገረ ፈጆች የሥልጠና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ የሙያ ሰርቲፊኬት ይሰጣል።



5) register medicines and medical equipments used in the region;

6) give license for health centers, clinics, examination agencies and pharmacies that are established by domestic investors and organizations;

7) ensure that professionals engaged on health sector in the region have fulfilled the required criteria;

8) train junior and medium health professionals;

9) implements traditional medicines and health treatments that their effectiveness is proved by combining them with modern medicine, encourages and organizes professionals;

10/ based on the health policy, formulate strategies that enable the people massively participate on prevention and prevention of communicable diseases, follow up its implementation;

11/ plan construction works necessary for health service, supervises implementation of same upon approval;

12/ participate in quarantine controls that are effected for protecting the public health;

13/ supervise sanitation of foods and drinks, ensure their fitness for health.

Article 15

*Justice Bureau*

The Justice Bureau shall have the powers and duties to:

1/ represent the regional state on legal affairs;

2/ represent the regional state in criminal cases falling under the jurisdiction of the regional courts;

3/ institute, cause to be instituted or intervene in proceedings and defend as the case may be before the regional courts; any judicial body or arbitration tribunal where the rights and interests of the public and of the Regional Government so requirs;

4/ follow up whether government regulations and directives are respected in offices of the regional state; and whether civil cases and claims against the regional state or bodies of the regional state are properly handled; cause rep-orts submitted to it on same as may be necessary;

5/ when requested by the regional state bodies, assist by preparing legal drafts and giving professional comments;

6/ follow up the legality of treatment of prisioners in prisons and see that their human right is respected; ensure that persons arrested without court order shall appear at court;

7/ make witnesses of crime shall get proper legal protection as may be found necessary;

8/ give license for attorneys that can practice up to the supreme court of the region, supervise and cancel their license when found necessary;

9/ in relation to human rights protection, give legal education by way of different means to raise the awareness of the people. Aranges training programs, direct and award professional certificate with regard to legal education and training for judges and prosecutors of the region and for attorneys of government offices in accordance with requests from such offices;

፲· በክልሉ ውስጥ የውል፣ የውክልና የማስረጃ ምዝገባዎችን ይሠራል፣ አላማቸው ለትርፍ ያልሆኑ በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ ማኅበራት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል።

፲፩· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የወንጀል መንስዔዎችን ያጠናል፣ ለወንጀል መከላከል የሚረዱ ጥናቶች ያካሂዳል፣ ወንጀል የሚቀነስበትን ሥልት ይቀይሳል።

፲፪· በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በክልሉ ፍርድ ቤቶች ክስ ለመመሥረትና ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበርና ካሣ እንዲያገኙ በፍትሐብሔር ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ይከራከራል።

፲፫· የክልሉ ሕጎች ከፌዴራል ሕጎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ በየጊዜው አዲስ የሚወጡትን የክልሉንም ሆነ የፌዴራል ሕጎችን እንዲሁም ማሻሻያዎችን እየተከታተለ ያሰባስባል ያስጠርዛል፣ ሕጎችን የማጠቃለል የኮዲፊኬሽን ሥራ ይሰራል።

አንቀፅ ፲፮

ትምህርት ቢሮ

የትምህርት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩· በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት የክልሉን የትምህርት ሥልጠና ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፪· ትምህርትን በክልል አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋት የሚያስችሉ ሥልቶችን ይቀይሳል። ለተግባራዊነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

፫· በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሁሉ የመማር ዕድል የሚያገኙበትን ሥልት ይቀይሳል፣ መሠረተ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል።

፬· የክልሉ የትምህርት ጥራት በአገር አቀፍ የተወሰነውን እስታንዳርድ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል።

፭· የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና እስታንዳርድ ተከትሎና የክልሉንና የአካባቢ ሁኔታዎችን በማገናዘብ የክልሉን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና እንደአስፈላጊነቱ የአፀደ ሕፃናት ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ ያጠናል፣ ይገመግማል በሥራ ላይ ያውላል።

፮· በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ መምህራናን የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑም ያደርጋል።

፯· በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ፈተናዎችን ተከትሎ ያስፈጽማል፣ በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡትን ፈተናዎችና የምስክር ወረቀቶች ብቃት ያረጋግጣል።

፰· ለትምህርቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ መጽሐፍትና ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል።

፱· የክልሉን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በክልል ደረጃ የሚቋቋሙ መለስተኛ ኮሌጆች ያደራጃል፣ ያስተዳድራል።

፲· ለትምህርቱ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፲፩· የክልሉ ትምህርት ፕሮግራሞች በሬዲዮና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች እንዲደገፉ ያደርጋል።

፲፪· የትምህርትን ሥራ ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችና ግምገማዎች ያካሂዳል፣ በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ጥናቶች ይሳተፋል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፲፫· የትምህርት መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያስተላልፋል።

፲፬· ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል ኅብረተሰቡን ያስተባብራል።

አንቀፅ ፲፯

የእንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ቢሮ

የእንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩· የክልሉን የእንስሳት እርሻ የተፈጥሮ ሀብት ልማትን በተመለከተ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያዘጋጃል፣ ቅደም ተከተልና አፈጻጸም ስትራቴጂዎችን ያወጣል፣ ሲፈቀድ በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

10/ perform registration of contracts; acts and documents in the region, give license for non?profit associations operate in the region and cancel the license it renders;

11/ study causes for crime in collaboration with concerned bodies, conduct researches that help prevent crime, formulate a strategy by which crime could be minimized;

12/ intervene in civil proceedings before the regional courts to assit victims of crimes for the recovery of damages resulting from grave injury where such victims are unable to institute such proceedings;

13/ ensure laws of the region are consistent with those of the federal, collect and binds newly issued laws and amendments of the region as well as the federal perform consolidation of laws.

Article 16

*Education Bureau*

The Education Bureau shall have the powers and duties to:

1/ prepare plan and programs for educational traning of the region in accordance with educational policy of the country, implement same upon approval;

2/ design strategies to extend education at regional level, and facilitate conditions for implementation of same;

3/ design strategy to reach out education opportunity for all children at school age; ensure all get basic education;

4/ ensure that educational quality of the region fits the educational standard of the country;

5/ based on the country's education policy and standard and taking into consideration of conditions of the region and local areas, prepare, study, evaluate, and implement primary schools and as may be necessay kindergartens of the region;

6/ supervise critera required to teach at every level are fulfilled, train teachers and education professionals, effect training of same;

7/ follow up and execute examinations prepared by the country to be given to schools in the region, check the adequacy of examinations and certificates prepared and given at the region's level;

8/ cause the fulfillment of books and other materials necessary for the educational works;

9/ organize and administer primary and secondary schools as well as junior colleges established at regional level;

10/ prepare projects for execution of the education program, implement same upon approval;

11/ cause that educational programs of the region are supported by radio and other medias;

12/ conduct researches and examinations that enable promote education works; participate on researches that are conducted federally, render the necessary support;

13/ collect and organize educational information; transfer same to relevant bodies;

14/ coordinate the public in order to get the support necessary for educational work.

Article 17

17. *Livestock and Natural Resources Development Conservation Bureau*

The Livestock and Natural Resources Development Conservation Bureau shall have the powers and duties to:

1/ prepare policy ideas with regard to livestock, agricultrue, and natural resource developments of the region, design strategies for priority setting and implementation; implement same upon approval;

፪· በክልሉ ውስጥ የእንስሳት የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል።

፫· በአገሪቱ ፖሊሲና ሕጎች መሠረት የክልሉን የመሬት አጠቃቀም የዱር አራዊት እና የብዝሃ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም ደንቦችን ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

፬· በክልሉ ውስጥ ለአርብቶ አደሩ የሚሰጡ የእንስሳትና የእርሻ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲስፋፋ ያበረታታል፤ ድጋፍ ይሰጣል።

፭· የክልሉን የደን ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ያበረታታል።

፮· ወደ ክልሉ በሚገቡትም ሆነ ከክልሉ በሚወጡ ዕፅዋት፣ አዝርዕት እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ላይ ተገቢው የኳራንቲን ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል።

፯· በክልሉ ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውሉ የእንስሳት መድኃኒትና ፀረ ሰብል ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል፤ በተገቢው መንገድ ስለመያዛቸው ይቆጣጠራል።

፰· በክልሉ ውስጥ ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳት ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያበረታታል።

፱· የግብርና ልማትን ለማፋጠንና ለማሻሻል የሚረዱ የምርምርና የማሠልጠኛ ተቋሞችና ማዕከሎች ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፤ ድጋፍ ይሰጣል።

፲· የግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ያበረታታል፤ በግብርና ዘርፍ ለሚሰማሩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የግብርና ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል።

፲፩· ተዛማች የእንስሳትና የሰብል በሽታ እንዲሁም ነባር የፀረ–ሰብል ተባይ ሲነሣ አስቸኳይ የመከላከል ዕቅድ በማውጣት በክልሉ የሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋሞችን እንዲሁም የህብረተሰቡን አቅም በማስተባበር በባህላዊና ዘመናዊ መንገድ አደጋውን ይከላከላል፤ በቁጥጥር ሥር እንዲውል ያደርጋል።

፲፪· የተፈጥሮ ሀብት መጨፍጨፍ በክልሉ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቆጣጠር እንዲቻል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውኃ የአፈርና የአየር ንብረትን ለመከላከል የሚረዱ መመሪያዎችን እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመጣል፤ የሚወጡ ሕጎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል።

፲፫· በክልሉ የሚገኙ ለአደን የተከለከሉ ቦታዎችና ደኖችን በማስተዳደር የክልሉ ደንና ዱር አራዊት ሀብት እንዲጠበቅና እንዲለሙ ያደርጋል።

፲፬· በክልሉ የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማሣደግ የተመረጡ ዝርያዎችን ለአርብቶ አደሩ እንዲተዋወቁ ያደርጋል።

አንቀፅ ፲፰

የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ

የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩· የውሃ ሀብት ልማት ፖሊሲዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፪· ስለውኃ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል። የውሃ ሀብትን ልዩ ልዩ የግልጋሎት ዓይነቶች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና ጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል።

፫· የውሃ ማዕድንና ኢነርጂን በሚመለከት ጥናቶችን ያካሂዳል እንዲጠና ያደርጋል፤ መረጃዎችን ያሰባስባል።

፬· በጥናት የተረጋገጠ የውኃ፤ የንፋስ፤ የፀሐይ ሐይል የተሻሻሉ የባዮ ማስና የሌሎች ኢነርጂ አጠቃቀሞች እንዲለሙና እንዲያድጉ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

፭· የውሃ ሀብትን በልዩ ልዩ የግልጋሎት ዓይነቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና ጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል።

፮· የውኃ ሀብትን በሚመለከት ግድቦችንና የውኃ ሥራዎችን ለማሠራትና ጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል።

2/ effect expansion of livestock; agriculture and natural resource developments in the region;

3/ prepare regulations for protection and utilization of land in the region, wild animals and biodiversity of the region in accordance with polices and laws of the region, implement same upon approval;

4/ encourage and assist promotion of livestock and agriculture extension services given to the pastoralist in the region;

5/ encourage expansion of forest resource development of the region;

6/ effect proper quarantine control on plants, crops, livestock and diary products that go in or out of the region;

7/ register animal medicine and pesticide chemicals that are used in the region, supervise their being handled properly;

8/ encourage and support promotion of quality livestock resource development in the region;

9/ works in collaboration with and support research and training institution and centers that help to improve and speed up agricultural development;

10/ encourage promotion of agricultrual investment, give agriculture license for and supervise domestic investors engaged on the agricultural sector;

11/ when communicable animal and livestock disease as well as familirar pests are created, prevent and contol the disaster by means of modern as well as traditional methods through coordinating governmental and non-governmental organizations found in the region and the society, by designing prevention plans;

12/ in order to control problems that may be created in the region as a result of natural resource damage, initiate ideas for preparation of directives that help water, soil and weather conservation in collaboration with relevant bodies, and make its effort to implement laws;

13/ effect protection and development of forest and wild animals resources of the region by administering forests and areas that are prohibited for hunting in the region;

14/ introduce special breeds to the pastoralist in order to promote livestock resource development in the region

Article 18

*Water, Mines and Energy Resources Development Bureau*

The Water, Mines and Energy Resources Development Bureau shall have the powers and duties to:

1/ implement policies of water resource;

2/ ensure that laws, regulations and directives provided for protection and utilization of water resource are respected; supervise the fair distribution and utilization of the various services of water resource;

3/ conduct researches with regard to water, mines and energy, cause research of same and collect information;

4/ make effort to promote and develop the use of water, wind solar powers and improved bio mass and other energies that are proved by research;

5/ supervise the fair distribution and utilization of water resource through various types of services;

6/ give license and supervise for the construction and implementation of dams and water works with regard to water resource;

፯· በተፈቀደ የውሃ ታሪፍና ፖሊሲ መሠረት የውኃ ጅምላ ክፍያ ያስከፍላል።

፰· የውሃ የማዕድንና ኢነርጂ ሀብትን በመጠበቅ ረገድ ከሚመለከታቸው የፌዴራል የሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በክልሉ ለሚካሄዱ የውኃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፱· ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራዎችን ያበረታታል፤ የማዕድን ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ይመዘግባል፤ የኮንስትራክሽን ማዕድናት የማምረት የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይመዘግባል፤ ይቆጣጠራል።

፲· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ የሚያስፈልገው ጋዝ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፲፩· የውሃ፤ የማዕድንና ኢነርጂ ሀብትን የሚመለከቱ ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲጠና ያደርጋል፤ መረጃዎች ይሰበስባል ያደራጃል።

፲፪· የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሥራዎችን በሚመለከት ዓላማውን ለማስፈጸም ሌሎች ተግባሮችንም ያከናውናል።

አንቀፅ ፲፱

የባሕልና ቱሪዝም ማስታወቂያ ቢሮ

የባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩· የክልሉ ሕዝብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች እንደዚሁም በክልሉ የሚደረጉ አበይት እንቅስቃሴዎችን በዜና ማሠራጫዎች ያሰራጫል፤ በአጠቃላይ የክልሉ መንግሥት ቃል አቀባይ በመሆን ይሠራል።

፪· በክልሉ መንግሥት የሚቋቋሙ መገናኛ ብዙኃንን ያደራጃል፤ ይመራል፤

፫· ባህል፤ ኪነ ጥበብ፤ ሥነ ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል።

፬· ፌዴራል መንግሥት የሚያወጣውን መመሪያ ተከትሎ በክልሉ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶች ተፈልገው እንዲገኙ፤ እንዲጠበቁ፤ እንዲጠኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል።

፭· በክልሉ ውስጥ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍትና ሙዚየሞች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል።

፮· የክልሉ ብሔረሰብ ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ቋንቋውም እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል።

፯· የአገሪቱን የቱሪዝም ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የቱሪስት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል።

፰· የክልሉን የቱሪዝም ዕድገት ለማፋጠን የሚረዱ ጥናቶች ያካሂዳል።

፱· በክልሉ በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለሚካሄዱና ከሆቴሎች አገልግሎት ውጭ ላሉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል።

፲· ለክልሉ ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ሥራዎች እድገት ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮችን ያከናውናል።

አንቀፅ ፳

የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ

የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩· የኮንስትራክሽን የከተማ ልማትና ቢሮ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

፪· የሕንፃ ኮድ፤ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል።

፫· በክልሉ መንግሥት በጀት ለሚሠሩ የመንግሥት ኮንስትራክሽኖች ሥራ ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል።

፬· በክልሉ መንግሥት በጀት የሚከናወን የመንግሥት ኮንስትራክሽን በተገባለት ውል መሠረት የጥራቱ ደረጃው፤ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል፤ በበላይነትም ይቆጣጠራል።

፭· በከተሞች ውስጥ ለሚካሄድ ኢንቨስትመንት በከተማ ቦታና የኮንስትራክሽን ሥራዎች ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

7/ effect payment of whole price in accordance with approved water tariff and policy;

8/ render the necessary support together with concerned federal ministries for water, mines and energy resources development works to be carried out in the region with regard to protecting water mines and energy sources;

9/ encourage traditional mine production works; registers cooperative works association of mines, give license for registers and supervise mine production construction;

10/ facilitate ways in which gas; fuel and fuel products necessary for the region are supplied, in collaboration with concerned bodies;

11/ conduct researches concerning water, mines and energy resources, cause researches to be conducted, collect information and organize it;

12/ perform such other duties to effect the objectives pertinent to water, mines and energy works.

Article 19

*Culture and Tourism Information Bureau*

The Culture and Tourism Information Bureau shall have the powers and duties to:

1/ release news on medias about political, economic and social affairs of the people of the region as well as major performances. In general it is to serve as information source of the regional state.

2/ organize and direct mass medias established by the regional state;

3/ effect promotion and expansion of culture, art and creative talent;

4/ in collaboration with relevant bodies, effect discovery conservation, study and utilization of historical antiquities found in the region, inline with the directives issued by the Federal Government;

5/ effect establishment and expansion of public libraries in the region;

6/ effect registration of history and culture of the people of the region, and promotion and expansion of its language;

7/ encourage expansion of tourism services in the region in accordance with the country's tourism policy;

8/ conduct researches that help to speed up tourism development of the region;

9/ give license for and supervise tourist service rendering institutions other than hotels and are undertaken by domestic investors in the region;

10/ perform such other duties necessary for development of the region's culture, tourism and information works.

Article 20

*Work and Urban Development Bureau*

The Work and Urban Development Bureau shall have the powers and duties to:

1/ prepare policies and strategies of construction, urban development, and house, implement same upon approval;

2/ check building code, design and standards of construction works are respected in the region;

3/ effect preparation of contract for government's construction works carried out by budget of the regional state;

4/ effect supervision and check up on government owned construction works carried out by the regional state's budget to ensure their performance in accordance with the quality standard; time and price limits, set in the contract;

5/ facilitate condition and render the necessary support for investment undertaken in towns and activities made with regard to urban land and construction works;

፮· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተሞች ውስጥ ለሚካሄድ የግል ኪራይ ቤቶች ግንባታ የኢንቨስትመንት የሥራ ፈቃድ ይሰጣል።

፯· በክልል መንግሥቱ ባለቤትነት ሥር የሚገኙ የከተማ ቤቶችን በሚመለከት ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል።

፰· ለከተሞች ፕላን ዝግጅት የሚረዳ ጥናቶች ያካሂዳል ፤ ከሚመለከታቸው የማዕከላዊ መንግሥት አካላት ጋር አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤ የከተሞችን ፕላን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ፕላኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ የከተሞችን ደረጃ በየጊዜው እያጠና ይወስናል።

፱· የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ ቤቶችን ሠርቶ እንዲጠቀም ሁኔታዎችን እንዲመቻቹ ያደርጋል።

፲· የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል።

፲፩· በክልል ከተሞች ውስጥ የመኖሪያ ቤት ችግርን ለማቃለል የቁጠባ ቤቶች እንዲሰሩና እንዲከራዩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ያበረታታል።

፲፪· በክልሉ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶችን በበጀት በዕቅድና በከተማ ፕላንና አዘገጃጀትና አፈጻጸም በሰው ኃይል ስምሪት በአስተዳደርና ገቢ አሰባሰብ ረገድ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ የቴክኒክ ሙያ ድጋፍ ይሰጣል።

<u>አንቀጽ ፳፩</u>

<u>የንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ</u>

የንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፩· የክልሉን የንግድ የኢንዱስትሪና የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ የሚመራበት ፖሊሲና ስትራቴጂ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፪· በክልሉ ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይመራል፤ ይቆጣጠራል የኢንዱስትሪና የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል፤ እንዲጎለብት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፫· የንግድ የኢንዱስትሪና የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚው የሚመራበትን ደንቦችን ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅለትም በሥራ ላይ ያውላል። የወጡ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎችንም በክልሉ መተግበራቸውን ያረጋግጣል።

፬· ለሌሎች አግባብ ላላቸው አካላት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን መንግሥት የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎቶችን እንዲሰሩ፣ እንዲሻሻሉና እንዲጠገኑ ያደርጋል።

፭· በክልሉ መንግሥት ውስጥ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለሚካሄድ የንግድ ሥራዎች የኢንዱስትሪ ዕደ ጥበባት በሕዝብ ማመላለሻና መገናኛ አገልግሎቶችን እንዲሠሩ እንዲሻሻሉና እንዲጠገኑ ያደርጋል።

፮· የሕዝብና የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማኅበሮችን ይመዘግባል። በማኅበራዊ የሚቀርብለትን የስምሪት ፕሮግራም ያጸድቃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፯· በክልሉ መንግሥት ውስጥ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል፤ በነዚሁ ላይ የቴክኒክ ምርመራ ያደርጋል፤ መንጃ ፈቃድ ይሰጣል።

፰· በክልል መንግሥት ውስጥ የትራንስፖርትና የመገናኛ ዓይነቶች ተደጋግፈው የሚሄዱበትንና በተቀነባበረ ሁኔታና በሚገባ በጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፱· በክልሉ መንግሥት ውስጥ የመሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሥርጭት አግባብ ባለው አካል የተወሰነው የዋጋ ተመን መከበሩን ይቆጣጠራል።

፲· የክልል መንግሥት የእንዱስትሪና የአርብቶ አደር የልማት ውጤቶች እንዲታወቁ ኢግዚቢሽን እንዲዘጋጅ ያደርጋል።

፲፩· የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን እያመነጨ በማዕከላዊ መንግሥት ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን ለሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ያስተላልፋል፤ ሌሎችም በክልል ደረጃ እንዲጠኑና በሥራ ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

6/ in collaboration with concerned bodies, give investment license for construction of private rent houses to be carried out in urban;

7/ render technical suppoert concerning urban houses owned by the regional state;

8/ conduct researches that help preparation of urban plan, make the necessary collaboration with concerned federal government bodies, effect preparation of detailed plans necessary for execution of urban plans, follow up and supervise their implementation; study and decide standard of urban from time to time;

9/ facilitate conditions so that urban dwellers construct houses as their financial capacity allows and benefit therby;

10/ encourage organization of residence house construction cooperative works associations, designs ways in which they shall get support;

11/ facilitate conditions and encourage construction and rent of saving houses, in order to alleviate residence house problems in towns of the region;

12/ follow up and supervise municipalities found in the region with regard to budget, plan, preparation and execution of urban plan, manpower assignment, administration and revenue collection; render technical support to same.

Article 21

*Trade, Industry and Transport Bureau*

The Trade, Industry and Transport Bureau shall have the powers and duties to:

1/ prepare policy and strategy by which the region's trade transport and industry economic sector shall be directed, implement same upon approval;

2/ direct and supervise trade activities in the region, encourage promotion of industry and transport services; render the necessary support for its development;

3/ prepare regulations by which the trade, industry and transport economic sector shall be directed, implement same upon approval by concerned body ensure issued laws, regulations and directives are implemented in the region;

4/ without limiting the power given to other relevant bodies, effect establishment, upgrading amendment of transport and communication services of the regional state;

5/ effect establishment, upgrading and amendment of public transport and communication services for trade, industry and handicraft activities carried out in the region by domestic investors;

6/ register trasport associations, approve work assignment program presented to it by the association and supervise its implementation;

7/ register vehicles found in the region, effect technical examination on same and give driving license;

8/ facilitate conditions in which various kinds of transport and communication in the region work in collaboration and utilized in an organized and proper way;

9/ supervise distribution of basic commodities and services in the region is in accordance with the tariff fixed by relevant body;

10/ cause exhibitions prepared so that industry and pastoralist development products of the region are introduced;

11/ initiate industry projects and transfer those which shall be implemented by the federal government to the relevant ministry, facilitate conditions so that others shall be studied and implemented at regional level;

፲፪· ለዕደ ጥበባትና ለጎጆ እንዱስትሪዎችና ለአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል። እንደአስፈላጊነቱ የዕደ ጥበባትን የጎጆ ኢንዱስትሪዎችን የሙያ ማሻሻያ ማሰልጠኛ ማዕከላትን የሕዝብና የንግድ የመንገድ ፣ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፤ መናኸሪያዎችን እንዲቋቋሙ ያደርጋል።

፲፫· በክልል መንግሥት ውስጥ ለሚቋቋሙ መካከለኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የተሽከርካሪ መጠገኛ ማደሻ፣ ጋራዦችና ባለሞተሮች ተሽከርካሪዎች መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ የዕደ ጥበባት ባለሙያዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ይመዘግባል።

፲፬· በክልሉ የሚቋቋሙት የንግድ ኢንዱስትሪ መ/ቤቶችን ያበረታታል፤ ያቋቁማል።

፲፭· የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት መገናኛ ዕደ ጥበባት ልማት የሚመለከት መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያጠናቅራል፤ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል።

፲፮· በክልሉ የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል።

<u>አንቀፅ ፳፪</u>

<u>የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ</u>

የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩· የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደርን በተመለከተ የወጡ ሕጎችን ፣ ፖሊሲዎችን፤ ደንቦችን መመሪያዎችን በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል።

፪· ለመንግሥት ሠራተኞች የተፈቀደው የደመወዝ ስኬል የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎች የመንግሥት ሠራተኞችን በሚመለከት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

፫· የመንግሥት ሠራተኞች አቀጣጠር አመዳደብና የደረጃ ዕድገት የደመወዝ ጭማሪ ዝውውር ሥልጠናና የዲስፕሊን አጠባበቅ ከመንግሥት ሠራተኞች ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ሠራተኞች ሕጎችን፤ ደንቦችን መመሪያዎች ጋር በማገናዘብ ይፈጽማል።

፬· የመንግሥት ሠራተኞችን ዝርዝር ሁኔታ መዝገቦ ይይዛል፤ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ያጠናክራል።

፭· የመንግሥት ሠራተኞች ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ አገልግሎታቸውን እንዲራዘም በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

፮· የመንግሥት ሠራተኞች በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ለመሰናበት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል።

፯· የመንግሥት ሠራተኞች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በሚቀርቡት ይግባኝ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል።

፰· ለመንግሥት ሠራተኞች የሥራ ውጤት መመዘኛ የወጣው መመሪያ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል።

፱· መሥሪያ ቤቶች በሚፈጸሙ የጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥር በተመለከተ የወጣውን መመሪያ ተከትለው መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል።

፲· የመንግሥት ሠራተኞች ሕጎችን፤ ደንቦችንና መመሪያዎችን በመተርጎም ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለክልሉ መንግሥት ምክር ቤት ያቀርባል፤ ለፌዴራል መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንም ያስተላልፋል።

፲፩· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አደረጃጀት የሰው ኃይል አወቃቀር በመገምገም የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራና ሠራተኛ መገናኘቱን ያረጋግጣል።

<u>አንቀፅ ፳፫</u>

<u>የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ</u>

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል።

፩· የፌዴራል መንግሥቱ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎችን በክልል መንግሥቱ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፪· አሠሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ ሕጎችን፤ ደንቦችንና መመሪያዎችን በክልሉ መንግሥት ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል።



12/ render extension service for handicrafts, micro and small industries; effect establishment of training centers for skill upgrading of handicraft and small industries as well as stations for public and freight road transport;

13/ give license for and supervise medium and small industries, garages, and persons and organizations who teach driving; register cooperative works associations of handicraft professionals;

14/ establish and encourage trade industry offices to be established in the region;

15/ collect, organize and transfer to concerned bodies information with regard to trade, industry, transport comunication and handicraft development;

16/ establish and administer trade book of the region.

Article 22

*Civil Service Bureau*

The Civil Service Bureau shall have the powers and duties to:

1/ supervise implementation of laws, policies, regulations and directives issued with regard to government employees administration;

2/ effect implementation of salary scale, various allowances and other working conditions permitted for government employees;

3/ execute employment, assignment, promotion, salary increment, transfer, training and disciplinary issues of government employees in accordance with laws, regulations and directives of government employees (civil servants);

4/ register and keep detailed conditions of government employees, organize statistical data;

5/ give final decision on requests for extension of services of government employees beyond their retirement age;

6/ give final decision on cases of firing government employees due to incompetence;

7/ give final decision on appels that government employees present in accordance with what is allowed by the law;

8/ supervise implementation of directive issued for efficiency evaluation of government employees;

9/ supervise whether offices perform employment of contract workers in accordance with the directive issued;

10/ present to the region's council problems faced with regards to interpretation of laws, regulations and directives of government employees; transfers same to Civil Service Commission of the Federal Government;

11/ present amendment ideas by evaluating organization of government offices, manpower structure in collaboration with relevant bodies, check the relevant worker is assigned for a particular work.

Article 23

*Labour and Social Affairs Bureau*

The Labour and Social Affairs Bureau shall have powers and duties to:

1/ effect implementation of policies of the federal labour and social affairs in the regional state;

2/ check laws, regulations and directives issued with regard to employer and employee are respected in the regional state;

፫· የሠራተኞችን ደህንነት ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና እና የመከላከያ ዘዴዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል።

፬· በየድርጅቱና በክልሉ ደረጃ የሚቋቋሙትን የሠራተኛና የአሠሪ ማኅበራት ይመዘግባል፤ ድጋፍ ይሰጣል።

፭· የኅብረት ስምምነት ድርጅቶችና የሥራ ክርክሮች በሕግ የተዘረዘረው ሥርዓት ተከትለው ፍጻሜ እንዲያገኙ በተቀላጠፈ ሁኔታ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፤ የኅብረት ስምነቶችን ይመዘግባል።

፮· በክልሉ መንግሥት ውስጥ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ባለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል።

፯· በክልሉ መንግሥት ውስጥ ሥራ ፈላጊዎችና ክፍት የሥራ መደቦች እንዲመዘገቡና ሥራና ሠራተኛ እንዲገናኙ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል።

፰· ስለክልሉ የሰው ኃይልና የሥራ ስምሪት ስለሠራተኞች ደህንነትና ጤና እንዲሁም አሠሪና ሠራተኞች ስለሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል፤ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል።

፱· በዘለቄታ ጡረታና የማኅበራዊ ዋስትና ዕቅድ የሚሸፈኑ የክልሉ ሠራተኞች በመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል።

፲· ሴቶች በፖለቲካ፤ በኢኮኖሚ፤ በማኅበራዊና ባህል መስኮች ያላቸውን ተሳትፎ ለማጎልበት የወጡ ፖሊሲዎች በክልሉ ኅብረተሰብ ትብብር ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፲፩· አግባብ ያላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልል ውስጥ የሚገኙ አረጋዊያንና የአካል ጉዳቶኞችን ለመርዳት እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፲፪· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሕፃናትንና ወጣቶች መልካም አስተዳደግ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎች በክልሉ እንዲዘረጉ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል።

፲፫· የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች እንዲወገዱ የክልሉን ኅብረተሰብ ያስተባብራል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፲፬· የቤተሰብ ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግና የጋብቻ ሥርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

<u>አንቀፅ ፳፬</u>

<u>የአደጋ መከላከል ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ቢሮ፤</u>

የአደጋ መከላከል ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ቢሮ ከዚህ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል ።

፩· በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ምክንያት የሚደርስ አደጋ ለመከላከል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና ሥልቶችን ያቅዳል ፣ ሲፈቀደም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል ።

፪· አግባብ ካላቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር አደጋ ለመከላከል የተቀየሱ ፖሊሲዎችና ሥልቶችን በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ።

፫· ከክልል መንግሥት በሚሰጥ መመሪያ መሠረት ከአገር ውስጥ ማንኛውም ዓይነት ድጋፍ ይጠይቃል ፣ የዕርዳታ ግኝትና አስተዳደርን በሚመለከት በፌዴራልና በክልል መንግሥት በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ከዕርዳታ ሰጪዎች አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል ።

፬· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋ ሊመጣ የሚችልበትን ምክንያት አስቀድሞ ያጠናል ፣ ያሳውቃል፣ አደጋው እንዳይደርስ ጊዜያዊና ዘላቂ የመከላከል እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል ።

፭· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋ በሚደርስበት ጊዜ የአደጋው ዓይነት መጠንና ስፋት እያጠና ሊወሰድ የሚገባውን ዕርምጃ ጭምር ለክልሉ መንግሥት ያሳውቃል ፣ ዕርዳታ የሚደረግበትን ቅደም ተከተል ይወስናል ።

፮· ማንኛውም ዓይነት ዕርዳታ ይመዘግባል ፣ ለተረጂው በወቅቱ በትክክል እንዲዳረስ ያደርጋል ።

3/ supervise standards of working conditions and safety measures issued for safety of workers are implemented;

4/ register and support employees' and employers' associations established at organizations and regional level;

5/ make the necessary prompt effort so that cooperative agreement companies and labour debates are settled in accordance with the procedure stated by law; registers cooperative agreements;

6/ conduct research about assignment of professionals and manpower engaged in the regional state;

7/ take measures that would enable the availablility of work for worker by registering the unemployed and vacancies in the region;

8/ collect, organize and transfer to concerned bodies information with regard to manpower and assignment, workers safety and health as well as employers and employee in the region;

9/ take mesures that would enable workers of the region, who are to be covered by long lasting pension and social security program, benefit from their rights;

10/ effect implementation of policies issued to promote the participation of women in political, economic, social and cultural sectors, with the cooperation of the region's society;

11/ prepare programs that would enable to help elders and the disabled in the region as well as rehabilitate the disabled, in collaboration with relevant bodies, implement same;

12/ in collaboration with relevant bodies, make the necessary effort to provide methods that would enable effect a good up brining of children and youth in the region;

13) coordinate society of the region to eradicate implements of social living, render the necessary support for same;

14) implement policies issued for protecting family well-being and taking care of marriage conducts.

Article 24

*Disaster Prevention and Preparedness and Food Security Bureau*

The Disaster Prevention and Preparedness and Food Security Bureau shall have the powers and duties to:

1) plan policies and strategies that would enable prevent disasters caused nature and human activities; implement same, in collaboration with relevant bodies, upon approval;

2) implement policies and strategies designed to prevent disaster, in collaboration with relevant government bodies of the region;

3) ask for any assistance from domestic authority in accordance with directive to obtain from the regional state and in accordance with directives issued by the federal and the regional governments, contacts with philanthropic organizations concerning relief resource and its administration;

4) study before hand and inform in collaboration with concerned bodies, anticipated causes of disaster, effect or cause to be effected temporary and permanent measures to prevent the disaster;

5) study in collaboration with concerned bodies, the kind, degree and amount of the disaster happened, and inform the regional state together with resolving measures to be taken; decide sequence for relief delivery;

6) register any kind of assistance, effect its delivery to the needy in a timely and proper ways;

፯. የዕርዳታ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ልማት ነክ ፕሮጀክቶችን ዝግጅትና አፈጻጸም ያስተባብራል ።

፰. በክልሉ መንግሥት እንዲሰሩ የሚያስችል ፈቃድ ያላቸውን መንግሥታዊ ያልሆኑ የግል የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ሥራ ያስተባብራል ፤ ስለሥራቸው አፈጻጸምና ብቃታቸውን ይቆጣጠራል ።

፱. በክልሉ ረጅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ውስጥ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚካሄዱ ሥራዎች እንዲካተቱ ያደርጋል ፤ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል ።

፲. የምግብ ዋስትና የተለያዩ ጥናቶች ያካሂዳል ፤ የፖሊሲ ሃሳብ ያመነጫል ።

፲፩. በምግብ አጠር አካባቢዎች የኅብረተሰቡ የምግብ ዋስትና ሁኔታ ለማሻሻል እንዲቻል የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞች እንዲጠኑ ያደርጋል ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል።

፲፪. በምግብ ዋስትና በኩል የሚካሄዱ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ያስተባብራል ።

፲፫. ለተቀናጀ የምግብ ዋስትና ፕሮጀክቶች ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል ፈንድ /ሌላ ሀብት/ ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከኅብረተሰቡ እንዲገኙ ያስተባብራል ፤ የተገኘው ፈንድና ሀብት በክልሉ መንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና ለሕዝባዊ ተቋማት ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

፲፬. ዓላማውን ለማስፈጸም ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል ።

፲፭. ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል ።

ክፍል አምስት

ስለጽሕፈት ቤቶች የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ፤

አንቀፅ ፳፭

መቋቋም ፤

የሚከተሉት ጽሕፈት ቤቶች የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል ።

፩. የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት
፪. የገቢዎች ጽ/ቤት
፫. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ጽ/ቤት
፬. የሥነ–ሕዝብ ጽ/ቤት
፭. የሕዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት ጽ/ቤት
፮. የሠፈራ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
፯. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት
፰. የሚሊሻ ጽ/ቤት
፱. የወሰን ጉዳይ ጽ/ቤት
፲. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት
፲፩. የመስኖ ልማትና የውኃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን
፲፪. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን

አንቀፅ ፳፮

የጽ/ቤቶች የባለሥልጣን መ/ቤቶችና ተቋማት የወል ሥልጣንና ተግባር ፤

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ላይ ስለቢሮዎች ተጠያቂነት የተደነገጉት ድንጋጌዎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

አንቀፅ ፳፯

የጽ/ቤት የባለሥልጣን መ/ቤቶችና ተቋማት ኃላፊዎች የወል ሥልጣንና ተግባር፤

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተደነገገው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል ።

አንቀፅ ፳፰

የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት

የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩. በወጣቶች ላይ የሚያተኩሩ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎችን ያስፈጽማል ፤ ይህን መሠረት በማድረግ በክልል ደረጃ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል ።

፪. በክልል አቀፍ ደረጃ ጤናማና ኃላፊነት የሚሰማው የወጣት ኃይል ለማፍራት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይቀይሳል ፤ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ።

፫. የክልሉ ወጣት ሕገመንግሥታዊ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ግንባታ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ።

7) coordinate preparation and execution of development oriented projects necessary for execution of relief programmes;
8) coordinate the works of non-governmental relief organizations that are licensed to operate in the region; supervise their competence and efficiency;
9) cause works undertaken to ensure food security to be included in long, medium and short term plans of the region, follow up their implementation, in collaboration with relevant bodies upon approval;
10) conduct various researches of food security, initiate policy idea;
11) in order to improve food security of the community in food insecure areas, cause projects and programmes studied, in collaboration with relevant bodies to create various income generating employment opportunities, immplement same upon approval;
12) coordinate various development works carried out in relation to food security;
13) coordinate to get fund (other resource) from government and non-governmental organizations as well as from the society for execution of coordinated food security projects programmes; effect utilization of the obtained fund (resource) for public institutions through the regional state or non-governmental organizations;
14) deal with different bodies to executive its objects;
15) submit report to concerned bodies regularly.

*PART FIVE*

*OFFICES, AUTHORITIES AND INSTITUTION*

Article 25

*Establishment*

The following offices, authorities and institutions are established by this proclamation.

1) Youth and Sport Affairs Office
2) Revenue Office
3) Civil Service Reform Progamme Office
4) Population Office
5) Public Participation and Organization Office
6) Resettlement Programme Coordination Office
7) Women's Affairs Office
8) Militia Office
9) Boundary Affairs Office
10) Prisons Administration Office
11) Irrigation Development annd Water Construction Authority
12/ Environmental Protection Authority

Article 26

*Common Powers and Duties of Offices, Authorities and Institution*

The provision provided under Article 5 of this Proclamation about accountability of bureau shall be applied similarly.

Article 27

*Common Powers and Duties of Heads of Offices, Authorities and Institutions*

The provision provided under Article 6 Sub-Article 4 of this Proclamation shall be applied similarly.

Article 28

*Youth and Sports Affairs Office*

The Youth and Sports Affairs Office shall have the powers and duties to:

1) cause executed national policies that focus on youth; based on this, initiate policies and laws at regional level;
2) facilitate conducive environment and design methods that would enable, to produce a healthy and responsible youth at regional level;
3) render the necessary support so that the region's youth shall actively participate in the democratic regime, based on the constitutional principles;

፬· የክልሉ ወጣት የክልሉንና የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህል እንዲያከብር፣እንዲጠብቅ፣እንዲንከባከብና እንዲያዳብር ያበረታታል ፡፡

፭· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን ወጣትና ሁለንተናዊ ስብእናን ለማዳበር የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

፮· አካል ማሰልጠኛና ስፖርት በክልሉ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል ፡፡

፯· በክልሉ ለሚቋቋሙ የስፖርት ማኅበሮች ፈቃድ ይሰጣል፣ ፕሮግራሞቻቸውን ያስተባብራል ፣ ይቆጣጠራል ፡፡

፰· ክልላዊ ስፖርት ውድድሮችን ያዘጋጃል ፣ እንዲዘጋጁም ፈቃድ ይሰጣል ፡፡

፱· ክልላዊ ስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት የስፖርት ማኅበሮች መካከል የሚነሳውን ክርክር ይዳኛል ፡፡

፲· የክልሉን ስፖርት ም/ቤት ያቋቁማል ፡፡

፲፩· ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቅና መሣሪያዎች ተሟልተው እንዲገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፡፡

፲፪· የክልሉን ባህላዊ ስኬቶች የበለጠ እንዲታወቁ ፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያደርጋል ፡፡

፲፫· የክልሉ ስፖርት ማኅበራት ገቢ ለዓላማቸው ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ሂሳባቸውን ይመረምራል ፡፡

፲፬· በክልሉ ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ያዘጋጃል ፣ እንዲዘጋጁ ያበረታታል ፣ የቴክኒክ ድጋፍም ይሰጣል ፡፡

፲፭· ከጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ ሕክምናን ያዘጋጃል ፣ በልዩ ወረዳዎች ለሚደረጉ ዝግጅቶችም ድጋፍ ይሰጣል ፡፡

አንቀጽ ፳፱

የገቢዎች ጽ/ቤት

የገቢዎች ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡፡

፩· አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከማናቸውም የገቢ ምንጭ የሚገኘው የክልሉ መንግሥት ገቢ በሚገባ ይወስናል ፣ ይሰበስባል ፡፡

፪· የክልሉ የገቢ መሠረት የሚስፋፋበትን ፍትሃዊ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት የሚኖርበትን ያጠናል ፣ ያመቻቻል ፣ ይተገብራል ፡፡

፫· ኅብረተሰቡ ስለግብር ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር በማናቸውም ዘዴ ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል ፡፡

፬· የክልሉን ገቢ በተመለከተ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተጋገዝ ሥራዎች ይሰራል ፡፡

፭· ገቢን በተመለከተ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

አንቀጽ ፴

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፡፡

፩· በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሙን ልዩ ልዩ ጥናቶች ፣ የማስፈጸሚያ ሕጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች በተዋሀደና በተቀናጀ መንገድ የሚተገበሩትን ማቀድ ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል ፣ ማስተባበር ፣ መቆጣጠር ፤

፪· አዲስ ጥናቶችን ማመንጨት በሌሎች አካሎች የሚቀርቡለትን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ የጥናት ሃሳቦችን መመርመርና ማጥናት እንደአስፈላጊነቱም በሚመለከታቸው አካሎች እንዲጠኑ ማድረግ ፤

፫· የጥናት ውጤቶችን መርምሮ ለውሣኔ ማቅረብ ፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ፤

፬· መሥሪያ ቤቶች ስትራቴጂያዊ አመራር የሚከተሉበትን ሥርዓት መቀየስ ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተል ፡፡

፭· ለመ/ቤቶች የቴክኒክና የምክር አገልግሎት ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት የሚያገኙትን ድጋፍ በአግባቡ መጠቀማቸውን መከታተል ፣ መቆጣጠር ፤

፮· የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጥናቶችንና አፈጻጸም የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችን ተገልጋዩ ሕዝብ በስፋት እንዲያውቃቸው ማድረግ ፣ በየወቅቱ መከታተልና መገምገም ፣ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ ፤



4) encourage youth of the region to respect, preserve, take care of and promote culture of the region as well as that of the country's nations and nationalities;
5) perform in collaboration with concerned bodies, and other such functions that help to promote the comprehensive character of the youth of the region;
6) effect promotion and extension of physical exercise and sport in the region;
7) give license for sport associations established in the region, supervise and coordinate their programmes;
8) prepare regional sport tournaments; permit preparation of same;
9) arbitrate debate that arise between sport associations concerning regional sport tournaments;
10) establish sport council of the region;
11) facilitate conditions in collaboration with government bodies of the region, for fulfillment of sport wears and materials;
12) make cultural values of the region known, improved and promoted better;
13) audit and check whether revenue of sport associations of the region is utilization for the intended purpose;
14) prepare sport centers in the region, encourage their preparation; render technical support;
15) prepare sport medical treatment in collaboration with Health Bureau, render support for preparation at special woredas;

Article 29

*Revenues Office*

The Revenues Office shall be accountable to Finance and Economic Development Coordination Bureau and shall have the powers and duties to :

1) decide properly and collect revenue of the regional state to be obtained from any revenue source in accordance with pertinent law;
2) study, facilitate and implement fair revenue collecting procedures to promote the region's revenue basis;
3) effect educating the society by any method to raise their awareness about tax paying;
4) perform functions with regard to revenue of the region in collaboration with relevant government bodies;
5) perform other duties concerned with revenue.

Article 29

*Civil Service Reform Office*

The Civil Reform Office shall have the powers and duties to:

1) plan ways in which executive bodies in the region implement, in an organized and combined way of the various studies, executing laws, regulations and directives of the reform programme, follow up their implementation, coordinate and supervise;
2) initiate new researches, studies and examine research ideas of civil service reform presented to it by other bodies;
3) examine research findings and submit them for decision, implement same upon approval;
4) design procedures by which offices follow strategic leadership, follow up implementation of same;
5) facilitate conditions by which technical and guidance support shall be rendered to offices, follow up and supervise whether they properly use the support they have obtained;
6) make that the public know widely the civil service reform researches and their execution, and good results obtained; follow up and evaluate same from time to time, prepare and submit report to concerned bodies;

፯· በተለያዩ ደረጃዎች የማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥልጠናዎች በስፋት የሚሰጡበትን ዕቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ ውጤቱንም መገምገም ፤

፰· በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ረገድ የክልሎችን ተሞክሮዎች በማጥናት ጠቃሚ ልምዶች በክልሉ ሁኔታ ተስተካክለው እንዲተገበሩ ማድረግ ፤

አንቀፅ ፴፩

የሥነ–ሕዝብ ጽ/ቤት

የሥነ–ሕዝብ ጽ/ቤት ከዚህ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· በክልሉ የሥነ–ሕዝብ ፖሊሲ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል ።

፪· ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በሥነ–ሕዝብ ፖሊሲ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ይመራል ፣ ይቆጣጠራል ።

፫· በክልሉ የሥነ–ሕዝብ ፖሊሲን በሚመለከት ምርምርና ጥናት ያደርጋል ።

፬· በክልሉ ውስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥነ–ሕዝብን የሚመለከቱ በዓላትና ሲምፖዚየሞችን ያዘጋጃል ፣ ያካሂዳል ።

፭· በክልሉ ውስጥ ልማትና የሕዝብ ዕድገት ተቀናጅተውና ተዋህደው የሚራመዱበትን ሥልት ያጠናል ፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል ።

አንቀፅ ፴፪

የሕዝብ ተሣትፎና አደረጃጀት ጽ/ቤት

የሕዝብ ተሣትፎና አደረጃጀት ጽ/ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· የክልሉ ሕዝብ ራሱን በተለያዩ ማኅበራት በማደራጀት ፈጣን የልማት እድገት እንዲመጣ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ያደርጋል ።

፪· የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራጅተው መብታቸውን እንዲያስከብሩና ለአገር ዕድገት አስተውጽኦ እንዲያደርጉ አስፈላውን ጥረት ያደርጋል ።

፫· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ማኅበራት የዕርስ በርስ የተሞክሮ ልውውጥ እንዲኖር መድረኮች ያዘጋጃል ።

፬· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት ሥራዎችን በጋራ ይሰራል ።

፭· ዓላማውን ለማስፈጸም ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል ።

አንቀፅ ፴፫

የሠፈራ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ፤

የሠፈራ ፕጀሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· ለግጦሽና ለእርሻ አመች ባልሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ አርብቶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሠፈራ ፕሮግራም ጥናቶችን ያካሂዳል ፣ ሲፈቀድለትም በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሠፈራ ፕሮግራም ያመቻቻል ።

፪· ለሠፋሪ አርብቶ አደሮች ስለሰፈራ ፕሮግራም አስፈላጊነት ሰፋ ያለ ግንዛቤ ያስጨብጣል ።

፫· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለሠፈራ ፕሮግራም አመች የሆኑ የክልሉ አካባቢዎችን ይመርጣል ።

፬· አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተባበር ለሠፋሪዎች የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች እንዲሟሉ ያደርጋል ።

፭· የሚመለከታቸው አካላት ለሠፋሪዎች ማቅረብ ያለባቸውን ነገሮች ስለማቅረባቸው ይከታተላል ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት በማድረግ ሁኔታዎች እንዲስተካከል ያደርጋል ።

፮· የሠፈራ ፕሮግራምን አላማ ተግባራዊ ለማድረግ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ።

አንቀፅ ፴፬

የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት

የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል ።

፩· የሴቶች ጉዳይ በተመለከተ በክልል ደረጃ ያስተባብራል፣ ያቀናጃል ይከታተላል።

7) prepare training plan that would enable to promote executing capacity at various levels, check implementation of same, evaluate its results;
8) study valuable experiences from other regions with regard to civil service reform and adopt them to the condition of the region.

Article 31

*Population Office*

The Population Office shall have the powers and duties to:

1) effect implementation of population policy in the region;
2) direct and supervise, in collaboration with concerned governmental and non-governmental organizations, activities undertaken on population policy;
3) conduct research and study concerning population policy of the region;
4) prepare and undertake, in collaboration with concerned bodies festivals and symposiums concerning population in the region;
5) study a strategy through which development and population growth go proportionally with each other in the region; follow up its implementation.

Article 32

*Public Participation and Organization Office*

The Public Participation and Organization Office shall have the powers and duties to :

1) cause the people of the region to organize itself into various associations and contribute their part to bring about fast development;
2) make the necessary effort to cause various sectors of the society organized and assert their rights as well as contribute for development of the country;
3) provide floor, in collaboration with, concerned bodies, for exchange of experience among associations to happen;
4) perform public participation and organization tasks in collaboration with concerned bodies;
5) perform such other duties to effect its objectives.

Article 33

*Resettlement Program Coordination Office shall have the powers and duties to:*

1) conduct resettlement program studies to improve the living condition of pastorlist residing around areas that are not convenient for pasture and agriculture; facilitate voluntary resettlement program up on approval;
2) give awareness raising explanations about importance of resettlement program, for resettling pastoralists;
3) select, in collaboration with concerned bodies, areas in the region convenient for resttlement program;
4) cause, in collaboration with concerned bodies, the fulfillment of basic materials necessary for the resetters;
5) follow upo supply of necessary facilities by concerned bodies for resettles; when need arises, effect correction measures by submitting report to concerned body;
6) perform such other duties to effect resettlement program objectives.

Article 34

*Women's affairs office*

The Women's Affairs Office shall have the powers and duties to:

1) coordinate, organize and follow up affairs concerning women at regional level;
2) supervise implementation of policies, laws and directives issued by the Federal and the Regional Government concerning women's affairs in the region;

፫· የሴቶች ጉዳይ በሚመለከት በፌዴራል መንግሥት በክልሉ መንግሥት የወጡ ፖሊሲዎችን ፣ ሕጎችንና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ በትክክል መተግባራ ቸውን ይከታተላል ።

፬· የክልሉ ሴቶች የሚገኙበትን ሁኔታ በተመለከተ ጥናቶች ያካሂዳል ፣ እንዲጠኑ ያደርጋል ፣ መረጃዎች ይሰበስባል ፣ ያጠናቅራል ፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ ያመቻቻል ።

፭· በተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሴቶችን ተሣትፎ ለማጎል በትና ኅብረተሰቡን በሴቶች ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማዋቀር የሚረዱ ሥልጠናዎች ዓውደ ጥናቶች ያካሂዳል፣ ውጤቱንም ይገመግማል ።

፮· በሕገ–መንግሥቱ ለሴቶች የተከበሩ መብቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል ።

፯· መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚወጡ ዕቅዶችና የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ሴቶችን በሚጠቅም መንገድ የሚተገበሩበትን ሁኔታ በማጥናት ሃሳብ ያቀርባል ፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል ።

፰· ሴቶችን ለሚያግዙና ለክልሉ ልማት አስተውጽኦ ለሚያ ደርጉ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ዕርዳታ ያስፈልጋል። ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የክልሉን ሴቶች ሕይወት ለማሻሻል ዕርዳታው መዋሉንና ውጤታማነቱን ይከታተላል ።

፱· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሴቶች ማኅበራት የሚደራጁበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፣ ድጋፍ ይሰጣል ።

፲· የጽ/ቤቱን ዕቅድ ከሌሎች አካላት ጋር የተቀናጀና የክልሉን ችግርና የልማት ቅደም ተከተል ያገናዘበ መሆኑን ይከታተላል ።

**<u>አንቀፅ ፴፭</u>**

**<u>የሚሊሽያ ጽ/ቤት</u>**

የሚሊሻ ጽ/ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል ።

፩· የሕዝቦችን የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ መብቶች ከየትኛውም አቅጣጫ ከሚሰነዘር ጥቃት የመከላከልና የመጠበቅ ግዴታ ፣ ሕገ–መንግሥታዊ መብት እንዳይ ደፈር መጠበቅና መከላከል እንዲሁም እነዚህን መብቶችና ጥቅሞች ለመድፈር የሚሞክሩትን በቁጥጥር ሥር አውሎ ለሕግ ማቅረብ ፤

፪· አገራችን የምትመራበት ሕገ–መንግሥትና የክልሉን ሕገ–መንግሥት በስሙ መሠረት የተቋቋመውን በሕዝብ የተመረጠ መስተዳድር /መንግሥት/ በኃይልና በኃይል ተፅዕኖ በማፍረስ ወይም አቅጣጫ ለማሳየት የሚደረጉ ጥረቶችን በሙሉ የመከላከል የሀገሪቱን የክልሉ ሕጎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ጥረት የማድረግ ፣ ሕዝቡ ያለስጋት ተንቀሳቅሶ በተናጠልና በኅብረት ክልሉን እያለማ የሚ ጠቀምበትን ሰላማዊ ሁኔታ ማመቻቸት በሕዝቡና በክልሉ መንግስት ጥረት የሚዘረጉ የልማት አውታሮች ጉዳት እንዳይደርስባቸው መከላከል ፤

፫· በየደረጃው የሚገኘው የመስተዳድር አካላት የሚያወጣ ቸውን መመሪያዎች ነፃ ፍ/ቤቶች የሚወስናቸው ውሳኔዎች ጉዳይ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን መፈጸምና ማስፈጸም ፤

፬· ከክልሉ የፖሊስ ኃይልና የመከላከያ ሠራዊት ጋር ተቀናጅቶ መንቀሳቀስና ወንጀልን በመከላከል ረገድ የመረጃ ምንጭ ሆኖ መሥራት ፤

፭· ከሚሊሽያ ዓላማ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን ፤

**<u>አንቀፅ ፴፮</u>**

**<u>የወሰን ጉዳይ ጽ/ቤት</u>**

የድንበር ጉዳይ ጽ/ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

፩· ከክልሉ ጋር አዋሣኝ ከሆኑ ሌሎች ክልሎች ጋር በወሰን ጉዳይ በጋራ ተባብሮ ይሰራል ።

፪· በኢ·ፌ·ዴ·ሪ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፹፮ ንዑስ አንቀጽ ፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሉን ከሚያዋስኑ አገሮች ጋር ባለው የድንበር ጉዳይ ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር በመሆን በጋራ ይሰራል ።



3) conduct researches about the existing condition of women in the region, cause researches to be conducted, collect information, oroganize them and facilitate ways in which they can be utilized;
4) conduct workshops and trainings, which help to promote women's participation in various activities and raise the awareness of the people about women;
5) check implementation of rights respected for women in the Constitution;
6) initiate ideas by studying conditions in which plans provided and projects undertaken by governmental and non-governmental organizations are implemented in such a way that they shall benefit women;
7) seek assistance for execution of projects which help women and contribute to the development of the region; in collaboration with concerned bodies, supervise implementation of the assistance obtained to improve the lives of women in the region and its fruitfulness;
8) facilitate condition and render support, in collaboration with relevant bodies, for organization of women's associations;
9) check that the Office's plan is consistent with that of other bodies and considered problems and development order of the region.

Article 35

*Militia Office*

The Militia Office shall have the powers and duties to:

1) defend and protect political, economic and social rights of the people from attack that can be made from any direction, protect and defend constitutional rights from trespasses as well as arrest and bring to court those who try to violate these rights and benefits.
2) defend the administration (government) elected by the people and established in accordance with the regional and federal constitution from attempts made to overthrow it by force or divert it; make effort to cause the country's as well as regions laws executed; facilitate a peaceful situation through which the people can jointly or privately engage in developing the region and benefit from it; defend development sectors established through effort of the regional state and the people from getting harmed;
3) execute and cause to be executed, in collaboration with concerned bodies, directives issued by administrative bodies at every level, and decisions passed by independent courts;
4) function as a source of information with regard to working in collaboration with the region's police force and federal defense force;
5) perform such other duties related to objectives of militia.

Article 36

*Boundary Affairs Office*

The Boundary Affairs Office shall have the powers and duties to:

1) works in collaboration with other regions bordering with the region with regard to boundary affairs;
2) without limiting the provision under Article 86, Sub Article 6 of the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia, work in collaboration with the federal government concerning boundary affairs with countries bordering with the region;

፫· በወሰን አካባቢ የሚፈጠሩ የግጭቶችን ምክንያት ምን እንደ ሆነና መፍትሄዎቹ ምን መሆን እንዳለባቸው ያጠናል ፣ ለሚመለከተው አካል በማቅረብም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ።
፬· በወሰን አካባቢ የሚፈጠሩ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል ።
፭· ከወሰን ጉዳይ ጋር የተያያዘ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

<u>አንቀጽ ፴፯</u>

<u>የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት</u>

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· ታራሚዎች የሚገባቸውን እንክብካቤ እንዲያገኙና ሰብዓዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩ ያደርጋል ።
፪· አመክሮ የሚጠየቅላቸው የሕግ ታሪሚዎች ጉዳይ እየተ ከታተለ በመመሪያው መሠረት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ።
፫· የሕግ ታራሚዎችን መብትና ማኅበራዊ ችግሮች በማጥናት ማኅበራዊ ኑሮአቸው እንዲሻሻልና ፍትሃዊ እንዲሆን ያደርጋል ።
፬· የሕግ ታራሚዎችን ወደ ማኅበራዊ ኑሮ ለመመለስና ብቁ ዜጎች ለማድረግ የሚያስችል የሥራ ተግባራቶችን ያከና ውናል ።
፭· የሕግ ታራሚዎችንና የማረሚያ ቤት አስተዳደርን በሚ መለከት ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል ።

<u>አንቀፅ ፴፰</u>

<u>የመስኖ ልማትና የውኃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ፤</u>

የመስኖ ልማትና የውኃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ከዚህ የሚከ ተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· የግድቦችንና የመስኖ ልማት ሥራዎችን /አውታሮችን/ ዲዛይን ይሰራል ።
፪· በሕዝብና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካሎች ሊሰሩ የታቀዱ የእርሻ ግድቦች ዲዛይንና ግንባታ እስታንዳርድ ይቆጣ ጠራል ።
፫· የአርብቶ አደሩን ምርታማነት እንዲጨምር ግድቦችና የመስኖ አውታሮች እንዲታደሱና በአካባቢው ሊደርስ የሚችል ጉዳይ ለመቆጣጠር ከተለያዩ መንግሥታዊ አካሎች ጋር በመተባበር ይሰራል ።
፬· ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሕዝቡ ስለግድብና መስኖ በእድሳትና ግንባታ የተጠቃሚዎች ሚና እንዲሁም የውኃ ፣ የእርሻና የግጦሽና የመስኖ አጠቃቀም እንዲ ያውቅ ያደርጋል ።
፭· አቅም ለመፍጠር የሚያስችሉ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚዛመድ የሌሎች አገሮች ልምድና ቴክኖሎጂ ያጠናል ።
፮· የሥልጠና ፕሮግራሞች ለኅብረተሰቡ በማዘጋጀት መሠረታዊ የኅብረተሰቡን አቅም ያጎለብታል ።
፯· የክልሉን የውኃ ኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚያከናውኑ የኮንስትራክሽን ብርጌዶችና ግብረ—ኃይሎች እንዲ ቋቋሙ ፣ እንዲስፋፉና ቅንጅት እንዲኖራቸው ያደርጋል።
፰· የውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽንን በሚመለከት የምክር አገልግሎት ይሰጣል ።
፱· በክልሉ የውኃ ሀብት ለማልማት የውሀ ጉድጓድና የኩሬ ቁፋሮ የምንጭ ውኃ ማሻሻል የውኃ ማከፋፈያና የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮችን መዘርጋት የውኃ ፓምፖችንና ጀኔሬተሮችን መትከል ፣ የውኃ ጋኖችንና ማጣሪያዎችን፣ ግንባታ ያካሂዳል ።
፲· ለውኃ ሥራዎች የሚያስፈልገውን መሬትና ድንጋይ ነክ የመሳሰሉ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም የሚችል ይሆናል ።
፲፩· የንብረት ባለቤት ይሆናል ፣ ውል ይዋዋላል ፣ በስሙ ይከሳል ፣ ይከሰሳል ።
፲፪· የመስኖና የውኃ ኮንስትራክሽን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራቶችን ያከናውናል ።



3) study cause of conflicts that arise around border areas, and what their solutions should be; cause implementation of same by submitting to the concerned body;
4) make intenseive effort to resolve boundary conflicts peacefully;
5) perform such other duties related to boundary affairs.

Article 37

*Prisons Administration Office*

The Prisons Administration Office shall have the powers and duties to:

1) make that prisonsers shall get due care and that their human rights are respected;
2) follow up and submit to concerned body, cases of prisoners who shall be released on condition;
3) study social problems and rights of prisoners and improve and make fair their social life;
4) perform functions that would enable to return prisonsers into social life and make them efficient citizens;
5) perform other duties concerned with prisoners and prisons administration.

Article 38

*Irrigation Development and Water Construction Authority*

The Irrigation Development and Water Construction Authority shall have the powers and duties to:

1) make designs of dams and irrigation networks;
2) supervise designs and construction standards of agriculture dams planned to be undertaken by the people and non-governmental organizations;
3) work in collaboration with different governmental bodies to renew irrigation sectors and dams to increase productivity of the pastoralist and contain the disaster that may happen in the region;
4) in collaboration with concerned governmantal and non-governmental organizations make the people learn about users role in construction and renewal of irrigation and dams, and utilization of water, pasture, agriculture and irrigation;
5) Study experience and technology of other countries that would enable to create capacity and related to the existing condition of the region;
6) Promote basic capacity of the society by preparing training programs;
7) Effect establishment, promotion and collaboration of construcion units and task forces that perform water construction works of the region;
8) Render consultation service concerning water works construction;
9) Undertake excavation of water wells and ponds, spring development, construction of drainage and water distribution pipes, water pumps and implantation of generators, reservoirs and distillers in order to develop water resource of the region;
10) Use resources such as land and stone necessary for water works free of charge;
11) Own property, enter into contracts; sue and be sued in its own name;
12) Perform such other duties necessary to effect objectives of irrigation and water construction.

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ፤

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩· የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ሕጎች ያዘጋጃል ፤ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ።

፪· አፈርን ውኃንና አየርን እንዲሁም ሕልውናቸውን በእነዚህ ሀብቶች ላይ የተመሠረተውን ሥነ-ሕይወታዊ ሥርዓቶች ለመጠበቅ የሚያስችሉ ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል ።

፫· በርሃማነትን ለመከላከል የሚያስፈልጉ ጥናቶችን ያካሂዳል ፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ።

፬· በተሻለ ሁኔታ አካባቢን ለመጠበቅ እንዲቻል ልዩ ልዩ የማበረታቻና የቁጥጥር ዘዴዎች ሥራ ላይ ስለሚውሉበት ሁኔታ ሃሳብ ያቀርባል ።

፭· የአካባቢ ጥበቃ አስፈላጊነት ግንዛቤ እንዲዳብር አስፈላጊውን ትምህርት ይሰጣል ።

፮· የአካባቢውን ጥበቃ በተመለከተ በክልሉ ባሉ ወረዳዎች የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል ።

፯· የንብረት ባለቤት ይሆናል ፤ ውል ይዋዋላል ፤ በራሱ ስም ይከሳል ፤ ይከሰሳል ።

፰· ዓላማውን ለማስፈጸም ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል ።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀፅ ፵

ስለሌሎች አስፈጻሚ አካላት ፤

፩· በዚህ አዋጅ ውስጥ ሥልጣንና ኃላፊነታቸው ያልተገለጹ የክልሉ አስፈጻሚ አካላትና ሌሎች ተቋማት ሥልጣንና ተግባር በተቋቋሙበት ሕግ በተደነገገው መሠረት የተገለጸው ይሆናል ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ሥር የሠፈሩት ሌሎች ሥልጣንና ተግባራቸውን የሚወስን ሕግ ያልወጣላቸው የአስፈጻሚ አካላትና ተቋሞች ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው የየተቋማቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ይወሰናል ።

አንቀፅ ፵፩

የአስፈጻሚ አካላት ቅርንጫፎች በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለመሆኑ ፤

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አካላት በክልሉ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ በዞን በወረዳ ወይም በሁሉም እርከኖች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖራቸው ይችላል ።

፪· በየትኛውም እርከን የሚገኝ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቅርንጫፍ ሥልጣንና ተግባር በዋናነት በክልል ደረጃ ለማስተባበሪያ ቢሮዎች የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ማዋል ይሆናል ።

፫· የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ ተጠሪነት በደረጃው የሚገኝ የመስተዳድር ጽ/ቤት እና ለማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ።

Article 39

Environmental Protection Authority

The Environmental Protection Authority shall have the powers and duties to:

1) Prepare policy laws of environmental protection, implement same upon approval;
2) Prepare standards that enable protect soil, water and air as well as biological procedures which their existence is based on these resources; follow up implementation of same;
3) Conduct researches necesary to prevent desertification; facilitate, in collaboration with concerned bodies, conditions through which they can be implemented;
4) Initiate ideas on ways in which incentives and supervision methods could be implemented in order to protect environment in a better way;
5) Give the necessary education to raise awareness of importance of environmental protection;
6) Render technical and guidance support with regard to environmental protection at woredas in the region;
7) Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;
8) Perform such other duties to execute its objectives.

## *PART SIX*
## *Miscellaneous Provisions*

Article 40

*Other Executive Organs*

1) The region's executive organs and other institutions whose powers and duties are not mentioned herein shall be what it explained in accordance with provisions in the law for their establishment.
2) Without prejudice the provision in sub-Article 1 of this Article executive bodies and institutions specified under Article 7 of this Proclamation, but no provision for the definition of their powers and duties shall be decided in proclamation for establishment of each institution.

Article 41

*Establishment of Branches of Executive Bodies at Every Level*

1) Organs established in accordance with this Proclamation shall have branches at zone, woreda or at all levels in the region as may be required.
2) The powers and duties of branch office found at any level shall mainly be implementing powers and duties given to coordinating bureau at regional level.
3) The branch office shall be accountable to administrative level at same level and to coordinating bureau.

አንቀፅ ፵፪
የተሻሩ ሕጎች ፤

፩· የአፋር ክልል አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፺፩/ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።
፪· ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

አንቀፅ ፵፫
አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ ፤

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

ሠመራ
ኢስማኢል አሊሲሮ
የአፋር ብ/ክ/መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

Article 42
*Repealed Laws*

1) Proclamaion No. 6/1999 for Establishment of Afar Region Executive Organs is hereby repealed.
2) No law, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

Article 43
*Effective Date*

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Afar Region Negarit Gazeta.

5 July 2002

Semera
Ismail Alisero
Chief Administrator of
Afar National R.State

(4)


QAFAR XOLETIH RAKAKAYA

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

| ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፯<br>አይሳኢታ – ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ | በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 2nd Year No. 7<br>AYSAITA – 8th July, 2001 |
|---|---|---|


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
“የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ —” ...................... ገጽ ፩


## CONTENTS


Proclamation No. 11/2001
''Afar Regional State Cooperatives Promotion Bureau Establishment Proclamation ...'' .......................................... Page 1


### አዋጅ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
### የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ቢሮን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአፋር ብሔራዊ ክልል ተመሣሣይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ኅብረተሰብ በመፍጠር ገንዘብን፣ እውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ቁጠባንና እርስ በርስ መደጋገፍን የሚፈጥሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋምና ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ፣

አባላት በማኅበራቸው አማካይነት ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶችንና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙና በነጻ ገበያ ተወዳድረው ምርታቸውን ወይም አገልግሎታቸውን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የሚያስችላቸውን ሁኔታ በማመቻቸት ለክልሉ ልማት ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣው የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ መሠረት ለተቋቋመውና ወደፊትም በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቋቋሙ ማኅበራት ድጋፍ የሚሰጥ የህብረት ሥራ ማኅበራትን የሚያስፋፋና የሚያስተባብር አንድ የመንግሥት አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፱/፫/፫–10 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

### Proclamation No. 11/2001
### A Proclamation that Provides for the Establishment of Cooperatives Promotion Bureau of The Afar National Regional State

WHEREAS, it has become necessary to establish cooperative among individuals having similar needs on voluntary bases by pooling their finance, knowledge and property which bring saving and mutual assistance in the Afar National Regional State to enable and solve their social and economic problems;

WHEREAS, it has become essential to facilitate condition. by which through their cooperatives the members can get modern agricultural technologies, industrial products and credit service that enable to develop productions and competing in the free market economy, sell their production or services with a better price and play the appropriate role for the development of the Region;

WHEREAS, it has been found essential to establish government organ which can support, promote and coordinate agricultural cooperatives which have been established pursuant to cooperative establishment Proclamation No. 147/1998 that has been proclaimed by Democratic Republic of Ethiopia and cooperatives to be established in accordance with the Proclamation;

NOW– THEREFORE, the Council of the Afar National Regional State pursuant to sub–article 3/3-10 of Article 49 of the Constitution of the Region, is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር····/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩· "ማኅበር" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ነው። በተለይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል።
- ሀ) የከብት አርቢዎችንና የከብት አርቢ ገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
- ለ) የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
- ሐ) የኢንዱስትሪና የዕደ ጥበብ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
- መ) የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማኅበር፤
- ሠ) የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር፤
- ረ) የዓሣ አሥጋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር፤
- ሰ) የማዕድን የህብረት ሥራ ማኅበራትና ሌሎች።

፪· "ክልል" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልል ማለት ነው።

፫· "ቢሮ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የህብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ቢሮ ነው።

## ክፍል ሁለት

፫· **ስለቢሮው መቋቋምና ተጠሪነት**

፩· የአፋር ብሔራዊ ክልል የህብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ቢሮ (ከዚህ በኋላ "ቢሮው" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው የመን ግሥት መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ቢሮው ተጠሪነቱ ለአፋር ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

፬· **የቢሮው መዋቅራዊ አደረጃጀት**

፩· ቢሮው በክልሉ መንግሥት የሚሾም የቢሮ ኃላፊና ለሥራ የሚያስፈልጉ የቴክኒክና ድጋፍ ሰጭ በባለሙ ያዎች የታገዘ መዋቅር ይኖረዋል።

፪· የቢሮው ዋና መ/ቤት በክልሉ ርዕሰ ከተማ ሠመራ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በዞንና በወረዳ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይኖረዋል።

፭· **የቢሮው ዓላማዎች**

፩· ለክልሉ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙ በአባላቱ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የተለያዩ ዓይነት የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

፪· የህብረት ሥራ ማኅበራት አባላት የምርት ማሣደጊያ ዎችን ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን የገበያና ብድር አገልግሎቶችንና የመሳሰሉትን በማግኘት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉበት ሁኔታዎች ማመቻቸት፤

፫· የህብረት ሥራ ማህበራት የምርት ውጤቶች ከአባላት በመግዛትና ለገበያ በማቅረብ የአባሎቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤

፬· ማኅበራት በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው የራሳቸውን ችግር ከመፍታት ባሻገር ለክልሉ ልማት ጉልህ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማኅበራቱን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ተከታታይ ሥልጠናዎች ሌሎች ሁለንተናዊ ድጋፎች ማድረግ።



## PART ONE
## *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as "Afar National Regional State Cooperatives Promotion Bureau Establishment Proclamation No....../20001"

2. *Definition*

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1. "Society" means any cooperatives which are established and registered in accordance with Proclamation No. 147/98; and it shall particularly include the following:-
   - (a) Pastoral and Agro-pastoral cooperative societies,
   - (b) Housing Cooperative Societies,
   - (c) Industrial and Artisans producers,
   - (d) Consumers Cooperatives Societies,
   - (e) Saving and Credit Cooperatives Societies,
   - (f) Fishery Cooperatives Socieities,
   - (g) Mining Cooperatives Societies and others.
2) "Region" means The Afar National Region;
3) "State" means The Afar National Regional State;
4) "Bureau" means Cooperative Promotion Bureau established in accordance with this Proclamation.

## PART TWO

3. *Establishment and Accountability*
   1) The Afar National Regional Cooperative Promotion Bureau (hereinafter referred to as the "bureau") is hereby established as an autonomous body having its own legal personality pursuant to this the Proclamation.
   2) The Bureau is accountable to the Regional Executive Committee and the Head of the Regional State.
4. *Organizational Structure*
   1) The bureau shall have the head to be assigned by the Region and other staffs.
   2) The head office of the bureau shall be in Semera and may establish branch offices in different zones and woredas as may be necessary.

5. *Objective of the Bureau*

1/ Facilitate conditions for the organization of different kinds of cooperatives based on the interest of their members which may bring socio-economic benefit for the peoples of the Region.

2/ Create suitable condition for members of cooperative societies to get the necessary inputs, loan and market service, raw material support in order to increase production and productivity.

3/ Render the appropriate support for cooperatives in their effort to secure the benefit of their members by buying and marketing their products.

4/ Provide continuing training and other all round support which enable cooperatives solve their problems and be formable competitor in the free market economy and strengthen their participation in the development of the Region.

Bureau;

## ክፍል ሦስት

፮. የቢሮው ሥልጣንና ተግባር

፩. የህብረት ሥራ ማህበራትን በሚመለከት የፖሊሲ ሃሣቦችን ያመነጫል፡ የጥናትና የምርምር ተግባራትን ያከናውናል። በህብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚጠቅሙና በአባላት ተሳትፎ የሚሠሩ የልማት ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል። የአፈጻጸም ስትራቴጂና ቅደም ተከተል ያወጣል፡ ሲፀድቅም በተግባር ያውላል።

፪. በአባላት ፍላጎት መሠረት ማህበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል።

፫. ማህበራት አስፈላጊና ወቅታዊ የገበያ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ በነጻ ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው ተጠቃሚ የሚሆኑ ለክልሉ የኢኮኖሚ እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፬. አባላት በህብረት ሥራ ማህበራቸው በኩል የምርት ማሣደጊያ ግብዓቶችን የምርት ውጤቶችን አገልግሎቶችን በጥናት ላይ የተመሠረተ ብድር እንዲያገኙና ምርትና አገልግሎትን በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፭. በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

፮. የህብረት ሥራ በገጠሩና በከተማ ለማስፋፋትና ለማዳበር የሚያስችሉ ተከታታይ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለህብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ ለማህበራት ቅጥር ሠራተኞችና ለህብረት ሥራ ባለሙያዎች ይሰጣል።

፯. ዓለም አቀፍ የህብረት ሥራ መርሆዎችን መሠረት በማድረግና የክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በአዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ መሠረት የተደራጀ ማህበራትን ይመዘግባል። የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣ ይሰርዛል።

፰. የህብረት ሥራ ማህበራት በሚዋሀዱበት በሚለያዩበት ወይም በሚፈርሱበት ጊዜ በፌዴራል መንግሥት በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ መሠረት እንዲፈጸም አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

፱. የህብረት ሥራ ማህበራት የሂሣብ አያያዝና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እንዲጠናከር የሙያ እገዛ በመስጠት ገንዘብና ንብረታቸውን እንዳይባክን ጥረት ያደርጋል። ወቅታዊ የሂሣብ ምርመራ በማድረግ ያግዛል።

፲. በተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራት የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን በማዘጋጀት በየማህበራቱ ያከፋፍላል።

፲፩. የህብረት ሥራ ማህበራትን የሚመለከቱ ሕጎችና ደንቦችን መመሪያዎችን በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡ ይቆጣጠራል።

፲፪. ህብረተሰቡ ስለህብረት ሥራ ጽንሰ ሃሣብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ በመገናኛ ብዙሀንና በሌሎች ዘዴዎች የትምህርትና የቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል።

፲፫. የቢሮውን እቅድና በጀት ያዘጋጃል። ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፲፬. የንብረት ባለቤት ይሆናል፡ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፡ ይከሰሳል።

፲፭. ቢሮውን በሚመለከት ረቂቅ ሕጎችና ደንቦች ለአፋር ብሔራዊ ክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያፀድቃል፡ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፲፮. ሴቶችን በህብረት ሥራ ማህበር በማሳተፍ ያነቃቃል፡ ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል።

፲፯. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።



## *PART THREE*

6. *Powers and Duties of the Bureau*

The Bureau shall:

1/ initiate policy proposal regarding with Cooperatives. and carry out study and research; prepare development projects useful for the development of the Cooperatives and to be carried out by the participation of the members; and formulate accomplishment strategies and orders and implement same upon approval.

2/ render necessary support to organize different type of cooperatives based on the interest of their members.

3/ facilitate condition for cooperative to compete in the free market economy by making available timely market information so that they can be benefited and thereby contribute in the economic developing of the Region.

4/ facilitate condition by which members through their cooperatives modern technologies that are necessary for the improvement of their productions, industrial products; study based credit and benefit by selling their productions with a better price.

5/ facilitate condition for the establishment of high level cooperative in the Region.

6/ prepare and render continuing education and training programmes for members of cooperatives; employees and experts of cooperatives, which enable to promote and strengthen cooperative in the rural and urban areas.

7/ register and issue certificate of legality to cooperatives organized based on the international cooperative priniciples, taking into account objective conditions of the region and in line with the Federal Proclamation No.....147/1998.

8/ render the necessary support and follow up the amalgamation division or dissolution of cooperatives to be in line with the Federal State Cooperative Proclamation No. 147/1998.

9/ exert effort to control the misuse of finance and property of cooperative societies by giving professional support for the strengthening of their accounting and inspection system and support auditing their accounts timely.

10/ prepare and distribute model cooperative laws, regulations and directives which serve for different cooperatives.

11/ follow up and supervise the proper execution of laws, regulations and directives concerning cooperatives.

12/ educate and spread propaganda through mass media and other means with a view to creating and enhancing public awareness of the concept of cooperatives.

13/ prepare plan and budget of the Bureau and implement same upon approval.

14/ own property, enter into contract, sue and be sued in its own name.

15/ prepare and submit for approval draft legislation and regulations concerning the Bureau to the Executive Committee of the Afar National Regional State, and implement same upon approval.

16/ initiate, educate and train women to participate in cooperative work.

17/ perform such other activities necessary for the execution of its objectives.

፯· የቢሮ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

የቢሮ ኃላፊው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ላይ ለቢሮው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩· የቢሮውን ሥራዎች ይመራል፡ ያስተዳድራል፡ ይቆጣጠራል፡

፪· የቢሮውን ያጭር፡ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፡ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፫· በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፡ ያስተዳድራል፡ ያሰናብታል።

፬· ለቢሮው በተፈቀደው በጀት ሥራና እቅድ መሠረት የገንዘብ ክፍያ ይፈጽማል።

፭· በሕጉ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቢሮው ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፡ ያንቀሳቅሳል።

፮· እንደአስፈላጊነቱ፡ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለቢሮው ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል።

፯· የቢሮውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፰· ስለስራው አፈጻጸም በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል።

፱· ቢሮው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ቢሮውን ይወክላል።

፲· በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሣሣይ ሥራዎች ይፈጸማል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፰· ስለበጀትና የሂሣብ መዛግብት

፩· የቢሮው የገንዘብ ምንጭ መንግሥትና ሌሎች ይሆናሉ።

፪· ቢሮው የተሟላና ህጋዊ የሆነ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፫· የቢሮው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፱· የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩· በተመሣሣይ ከዚህ በፊት የተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀትና ለመመዝገብ ለሌሎች ቢሮዎች ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፺፩ እና በዚህ አዋጅ መሠረት ለህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ተላልፎአል።

፲· የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ሁሉ ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የመተባበር ግዴታ አለበት።

፲፩· ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፲፪· ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፲፫· አዋጁን የማሻሻል ሥልጣን

ይህ አዋጅ ሊሻሻል የሚችለው በክልሉ ምክር ቤት ብቻ ነው።

፲፬· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*ሠመራ ታህሣሥ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.*

እስማኤል አሊ ሴሮ
የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ምክር ቤት
ርዕሰ መስተዳድር

7/ *Powers and Duties of the Head of the Bureau*

The Bureau Head shall,in addition to the powers and duties given to the Bureau under Article 6 of this Proclamation have the powers and duties to:

1/ direct, administer and supervise the activities of the Bureau;

2/ prepare and submit short, medium and long term plan, annual action plan and budget of the Bureau, and implement same upon approval;

3/ employ, administer and dismiss the employees in accordance with Civil Service Regulations;

4/ effect payments based on the approved work plan and budget of the Bureau.

5/ open and operate bank accounts with other partners in the name of the Bureau in line with laws;

6/ delegate his power and duty to employees as necessary,

7/ study and submit, organizational structure of the Bureau to the Regional Executive Committee, and implement same upon approval;

8/ submit periodic reports to the concerned body;

9/ represent the Bureau in its dealings with other third parties;

10/ perform such other activities as assigned to it by the Executive Committee and Head of the Regional State.

## *PART FOUR*
## *MISCELLANEOUS PROVISIONS*

8. *Budget and Books of Accounts*

1/ The source of income of the Bureau shall be the Government and other sources.

2/ The Bureau shall keep approriate and complete books of accounts.

3/ The books of accounts and financial documents of the Bureau shall be audited annually by the Auditor General or other auditors to be assigned by it.

9. *Transitory Provision*

1/ All powers and responsibilities which were previously vested to other Bureau to organize and register different cooperatives societies, are thereby similarly transferred to Cooperatives Promotion Bureau pursuant to Proclamation No. 147/1998 of this Proclamation.

10. *Duty to Cooperate*

Any concerned organ shall have a duty to cooperate in the execution of the Provision of this Proclamation.

11. *Inapplicable Laws*

Any law that is inconsistent with this Proclamation shall not apply with respect to matters provided for herein.

12. *Powers to Issue Directives*

The Bureau may issue directives for the proper implementation of this Proclamation.

13. *Power to Amend the Proclamation*

This Proclamation can only be amended by the Regional Council.

14. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force from the date of its publication in the Afar Regional State Negarit Gazeta.

*Done at Semera, this —— day of December, 2001*

*Ismael Ali Sero*
*President of the Afar National Regional State*

QAFAR DOLAƗIH RAKARAYA

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አይሳኢታ – ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

AYSAITA No 13 July 7 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የአፋር ብ/ክ/ መንግስት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፬ ........................................ ገጽ

## CONTENTS

Proclamation No. 13/2002
''Establishment of the Office of the HIV/AIDS Prevention and Control Secretariat of the Afar National Regional State Proclamation NO.13/2002.'' Page

የኤች.አይ.ቪ/ወረርሽኝ በመላው አለም ላይ በተለይም በታዳጊ አገሮች በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቶ በመታየቱ፣

አገራችን ኢትዮጵያ የኤድስ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ ከሚገኝባቸው ታዳጊ አገሮች አንዷ ሆና በመገኘቷና በክልላችንም ውስጥ ባሉ ከተሞች ከሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ባላነሰ ሁኔታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት ተስፋፍቶ በመታየቱ፣

እስከ አሁን ድረስ ሥርጭቱን ለመከላከልና ለመግታት በክልሉ ደረጃ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ቢሆንም ቅንጅታዊ አሰራርን በማጐልበት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያሳተፈ ከክልል እስከ ቀበሌ የሚወርድ የፀረ ኤድስ አስተባባሪና ቴክኒክ ኮሚቴ አዋቅሮ የተበታተነና ግልፅነት የሌለው አሰራርን በማስቀረት በቅንጅታዊ አሰራር አመርቂ ውጤት ማስገኘት እንደሚቻል በመታመኑ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በክልሉ ህገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ ንዑስ አንቀፅ ፫ (ሐ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### አንቀጽ ፩

### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብ/ክ/ መንግስት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፫ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 13/2002
## PROCLAMATION TO ESTABLISH THE OFFICE OF THE HIV/AIDS PREVENTION AND CONTROL SECRETARIAT OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

WHEREAS, there has been an epidemic of HIV/AIDS all- over the world in general, and in developing countries in particular;

WHEREAS, Ethiopia is one of developing countries with widespread of the HIV/AIDS, and that there has also been found that there is widespread of such disease in the towns of our Region;

WHEREAS, Various activities have been carried out so far at Regional level to prevent and arrest the spread of HIV/AIDS, it is believed that satisfactory results can be achieved by promoting integrated and transparent performance and setting up Anti-AIDS Coordinating and Technical Committee which involves all sections of the society at all levels, from region up to kebele;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-Article 3(c) of Article 47 of the Constitution of the Council of the Afar National Regional State, it is hereby proclaimed as follows.

### SECTION ONE

### Article 1

### Short Title

This Proclamation may be cited as the ''Establishment of the Office of the HIV/AIDS Prevention and Control Secretariat of the Afar National Regional State . Proclamation NO.13/2002.''

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 12.75

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

64 16 55

## አንቀጽ ፪
## ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡–

፩· "ክልል ማለት፡–" የአፋር ብ/ክ መንግስት የመስተዳድር ክልል ማለት ነው።

፪· "ምክር ቤት ማለት"፡– የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት ወይም የም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ነው።

፫· "ጽ/ቤት ማለት" ፡– የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መቆጣጠሪያና መከላከያ ሴክሬታሪያት ማለት ነው፣

፬· "ኮሚቴ ማለት"፡– በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋም አስተባባሪ ኮሚቴ ማለት ነው፣

## አንቀጽ ፫
## መቋቋም

፩· የኤች·አይ·ቪ/ኤድስከላከያና መቆጣጠሪያ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ ሴክሬታሪያት እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· የሀገሪቱንና የክልሉን የኤድስ ፖሊሲ ዕቅድ ፣ ስትራቴጂና መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ክልል አቀፍ የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፫· ሴክሬታሪያት ተጠሪነቱ ለክልሉ ኤች·አይ·ቪ/ኤድስመከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤትና ሰብሳቢ ለሆነው የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

## አንቀጽ ፬
## ዓላማ

የሴክሬታሪያቱ/ የጽ/ቤቱ/ አላማዎች ከዚህ የሚከተሉት ይሆናሉ።

፩· ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴን በተቀናጀና በተባበረ መልክ በማጐልበት ህብረተሰቡ ራሱን ከወረርሺኙ እንዲጠብቅና በኤድስ እንዳይጠቃ በማድረግ ለቀጣይ የዕድገት ጉዞው አስተማማኝ መሠረት መጣል፣

፪· በኤድስ ሳቢያ በክልሉ ውስጥ እየደረሠ ያለውን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ–ልቦናዊ ተፅዕኖዎችን ለመቅረፍና ለማስቀረት መንቀሳቀስ፣

፫· የሀገር ተረካቢ የሆነውን ትውልድ ከኤድስ ወረርሽኝ ሊታደግና በዚህም የልማት ጉዞአችን ጠንካራ መሠረት ይዞ የሚራመድበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

፬· ህብረተሰባዊ የሆነ የፀረ–ኤድስ ባህሪያዊ ለውጥ ለማምጣትና ቀጣይነት ያለው ጥረት ማድረግ፣

፭· የበሽታው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተጠቂዎችን/ የሥነ ልቦና፣ የጤናና የማቴሪያል እገዛና እንክብካቤ እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ፣

፮· ሀገራዊና ክልላዊ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ በሽታ የመከላከልና የመቆጣጠር ፖሊሲና ዓላማ ስትራቴጂ መተግበር፣

፯· ባለብዙ ዘርፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮጀክት ማስፈፀም።

## አንቀጽ ፭

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፤

ሀ/ በአንድ የበላይ ኃላፊ ይመራል፣

ለ/ በተዋረድ በዞንና በወረዳ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፣

ሐ/ ለጽ/ቤቶቹም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፣

## Artilce 2
## Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. '' Region'' means Afar National Regional State.
2. '' Council'' means HIV/AIDS Prevention and Control Council or General Assembly of the Council.
3. '' Office'' means HIV/AIDS Prevention and Control Secretariat.
4. '' Committee'' means a Coordinating Committee set up at kebele level.

## Article 3
## Establishment

1. The Office of the HIV/AIDS Prevention and Control Secretariat (hereinafter referred to as the ''Secretariat'') is hereby established having its own juridical personality.
2. There is hereby established HIV/AIDS Prevention and Control Council at Regional level to implement the plans, strategies and directives of the country and the Region.
3. The Secretariat shall be accountable to the Head of the Regional Government, the Chairperson of the HIV/AIDS Prevention and Control Council.

## Article 4
## Objectives

The Secretariat shall have the objectives to:

1. lay reliable foundation for the development of the society by enhancing HIV/AIDS prevention activities through integrated co-ordination so as to enable the society to protect itself against the attacks of HIV/AIDS epidemic;
2. take initiative to alleviate and avoid social, economic and psychological impacts of HIV/AIDS in the Region;
3. facilitate condition for the strong foundation of development by saving the coming generation from HIV/AIDS epidemic;
4. make continual efforts to bring Anti-AIDS behavioral change in the society;
5. make efforts to provide psychological, health and material assistance and care to the individuals directly or indirectly affected by the disease;
6. implement national and Regional policies, objectives and strategies of HIV/AIDS prevention and control;
7. Carry out multi-sectoral projects of HIV/AIDS prevention and control.

## Article 5

The Office shall have the following organs:

(a) a Head of the Office;

(b) Offices at zonal and woreda levels;

(c) The necessary professionals and other staff.

## ክፍል ፪

## አንቀጽ ፮

## የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩· በም/ቤቱ ውሣኔዎችና የሥራ ፕሮግራሞች ላይ በመመስረት የኤድስ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ የሚደረጉትን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤ ለተግባራዊነታቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

፪· ምክር ቤቱ የተቋቋመባቸውን ዓላማዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል።

፫· የኤች·አይ·ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል ፤ በመከላከሉም የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ያደርጋል።

፬· የክልሉ ኅብረተሰብ ስለ ኤድስና መዘዙ ግንዛቤ እንዲኖረው አገር አቀፍና አለም አቀፍ ስብሰባዎችንና አውደ ጥናቶች ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፭· ምክር ቤቱን በመወከል ኤች·አይ·ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ አገር አቀፍ አሕጉራዊ አለም አቀፍ ስብሰባዎች ይሳተፋል።

፮· የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ጥረት ያስተባብራል የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፯· በክልሉ ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ገፅታ መረጃዎችን ያሰባስባል ያጠናቅራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያስተላልፋል፤

፰· የሚመለከታቸውን አስተባባሪ ኮሚቴዎችን ተግባር በበላይነት ይመራል ፤ ያስተባብራል።

፱· በሥልጣኑ ሥር የተቋቋሙትን ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ተግባር በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤

፲· የአጭር ፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ እቅድና በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ በእነሱም አማካይነት ለም/ቤቱ ያቀርባል ሲያጸድቅም በተግባር ላይ ያውላል።

፲፩· የምክር ቤቱንና የቦርዱን ውሣኔዎች ለክልል መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ያስተላልፋል በወቅቱ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፪· በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የምክር ቤት አካላት መንግሥታዊ ያልሆኑ ደርጅቶችና ግለሰቦች ሥራ የተቀናጀ እንዲሆን በቅርቡ ይከታተላል።

፲፫· ከተለያዩ አጐራባች ክልሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ልምድ የሚገኝበትን መንገድ ይፈጥራል፤

፲፬· በለጋሾች የተገኘውን ገንዘብና ከመንግስት የሚመደብላቸው በጀት በአግባብ ሥራ ላይ ይውላል።

፲፭· የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ ወርሐዊና የ፫ ወር የሥራ ሪፖርት ለቦርዱና ለም/ቤቱ ስብሰባዎች ያቀርባል፤

፲፮· በም/ቤቱና በሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፤

፲፯· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፖሊሲ ያስፈጽማል።

፲፰· የገምጋሚ ቦርዱ ያደራጃል ፤ ያዋቅራል፤

፲፱· ለሥራ ቅልጥፍና ተስማሚ የሆኑ ከፖሊሲና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተቃራኒ ያልሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል።



## Section Two

## Article 6

## The Powers and Duties of the Office

The Office shall:

1. co-ordinate the daily activities carried out in the Region to prevent and control the HIV/AIDS disease based on the decisions and work programmes of the Council; and facilitate conditions for their implementation;
2. devise ways and means to effectively implement the objectives of the Council;
3. co-ordinate the activities of the governmental organizations engaged in prevention and control of HIV/AIDS in the Region, and create integrated activities for the prevention of it;
4. prepare and facilitate conditions for the preparation of national and international meetings and workshops with a view to creating public awareness in the Region about HIV/AIDS and its effects;
5. representing the Council participate in national, continental and international meetings on the prevention and control of HIV/AIDS;
6. co-ordinate the efforts of the non-governmental organizations and renowned individuals engaged in prevention and control of HIV/AIDS in the Region; and facilitate conditions to create integrated co-ordination between such organizations and individuals;
7. collect and analyze data relating to the situation of HIV/AIDS in the Region; and forward the same to the concerned sectors as may be necessary;
8. direct and co-ordinate the activities of the concerned coordination committees;
9. direct and co-ordinate the activities of various committees set up under its jurisidction;
10. prepare short, medium, and long-term work plans, and draw up draft budget, and submit the same to the council through the Management board; and implement the same upon approval;
11. forward the decisions passed by the Council and the Board to the Executive of the Regional Government; and supervise the implementation thereof;
12. follow up closely that integrated activities be maintained between organs of the Council, non-governmental organizations and private sectors engaged in prevention of HIV/AIDS;
13. establish relationship with neighbouring regions so as to facilitate a way and means to gain experience from the same;
14. properly use the fund from donors, and the budget allocated by the Government;
15. present monthly and quarterly reports on its performance to the meetings of the Board and the Council;
16. discharge other duties entrusted to it by the Council and the Management Board;
17. implement the HIV/AIDS policy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
18. establish and organize an evaluation, board;
19. prepare and implement regulations and directives which are appropriate for the efficiency of the activities, and consistent with the policy and objective situation of the Region.

### አንቀጽ ፯
### የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል

፩· የጽ/ቤቱን ሥራ ይመራል ያስተዳድራል ይቆጣጠራል፣
፪· የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከል ለመቆጣጠር የሥራ አመራር ቦርድ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣
፫· የጽ/ቤቱን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ያቀርባል። ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣
፬· የም/ቤት የቦርዱ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለም/ቤት /ለቦርድ እያቀረበ ያስወስናል፣
፭· ከሦስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት ቢያስፈልግ ጽ/ቤቱን ወክሎ ይቀርባል፣
፮· በየደረጃው ያሉ በጽ/ቤቶችና ኮሚቴዎች የሥራ አፈፃፀማቸውን አጠቃሎ ለም/ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣
፯· መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል፣
፰· በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች ድርጅቶች ፣ ማኅበራት ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር እንደ አስፈላጊነቱ ግንኙነት ያደርጋል፣
፱· የበጐ ፈቃድ ተሳታፊዎች እንዲበራከቱ ያበረታታል፣
፲· በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ አመርቂ ተግባራት ላስመዘገቡ ተቋማትና ግለሰቦች ለምክር ቤቱ በማቅረብ የማበረታቻ ሽልማት ያሰጣል/ያሸልማል/፣
፲፩· በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ አገር አቀፍ ስብሰባዎች ይሳተፋል
፲፪· የጽ/ቤቶቹን ሥራ ለማፋጠን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ባለሙያዎችንና ሌሎች የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በቋሚነትና በኮንትራት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል።
፲፫· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲተገበር ያደርጋል።
፲፬· የክልል ገምጋሚ ቦርድ አባላትን መርጦ ለም/ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፣

### አንቀጽ ፰
### ስለ ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት መቋቋም

፩· የሚከተሉት ክፍሎች በአባልነት የሚገኙበት የክልል ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት አባላት፣
 ፩· የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድር ........................................ ሰብሳቢ
 ፪· የክልሉ መስተዳድር የካቢኔ አባላት ................ አባል
 ፫· የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማለትም፦
  • ጤና ጥበቃ ቢሮ ........................................ አባል
  • ትምህርት ቢሮ ........................................ አባል
  • እንስሳትና እርሻ ሃብት ቢሮ ........................ አባል
  • ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ................ አባል
  • አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ ................. አባል
  • ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ .................. አባል
  • የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ................................ አባል
  • ፖሊስ መምሪያ ........................................... አባል
  • እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች ........................................ አባል
 ፬· በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሕዝባዊ ማኅበራትና ድርጅቶች አባል
 ፭· በበጐ አድራጐት ተግባር ላይ በክልል የተሠማሩ ድርጅቶች ...... አባል

### Article 7
### The Powers and Duties of the Head of the Office

The Head of the Office shall:

1. direct, administer and supervise the activities of the Office;
2. serve as a secretary of the Management Board in prevention and control of HIV/AIDS;
3. prepare work plan and the budget of the Office and submit them to the Council; follow up and supervise their implementation upon approval;
4. submit matters to the Council or to the Board for decision - making;
5. represent the Office, as is necessary, in its dealings with third party;
6. consolidate and submit to the council reports of the offices and committees at all levels on their work accomplishment;
7. call on governmental and non-governmental organizations to provide a necessary assistance for the Office;
8. establish relationship, as is necessary, with individuals, associatons, non-governmental institutions engaged in HIV/AIDS Prevention activities;
9. encourage that the number of voluntary participants be increased;
10. recommend the institutions and individuals that have achieved satisfactory results in prevention of HIV/AIDS to the Council for award of incentive;
11. participate in national meetings on the prevention of HIV/AIDS;
12. where it finds it necessary for the efficiency of the activities, employ professionals and other support-giving staff on permanent and contract-basis; and dismiss them;
13. cause the execution of HIV/AIDS policy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
14. select and submit members of the Board of Evaluation of the Region to the Council for approval.

### Article 8
### Establishment of the HIV/AIDS Prevention and Control Council

1. There is hereby established the Regional HIV/AIDS Prevention and Control Council which consists of the following members:
   1. The Head of the Regional Government Chairperson
   2. The Members of the Cabinet of the Regional Government ........................................ members
   3. The organs of the Regional State:
      • Health Bureau........................................ member
      • Education Bureau .................................. member
      • Animals and Agriculture Development Bureau........................................ members
      • Culture, Tourism and Information Bureau ........... member
      • Disaster Prevention and Prepardness Bureau ... member
      • Labour and Social Affairs Bureau ........... member
      • Women's Affairs Office.......................... member
      • Police Department .................................. member
      • Other government orogans as may be nenecessary........................................ member
   4. Civic societies and organizations in the Regonn........................................ member
   5. Charitable Organizations operating in the Region........................................ member

፮· በክልሉ የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት ............. አባል
፯· ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች ያቋቋሙት ማኅበር አባል
፰· ታዋቂ ግለሰቦችና የሀገር ሽማግሌዎች እንደአስፈላጊነቱ ............................................. አባል
፱· የዞን ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤቶች ሰብሳቢዎች ................................ አባል
፲· የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ኃላፊ ......................... ፀሐፊ

ስለ ምክር ቤቱ አደረጃጀት

፩· ተጠሪነቱ ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የሆነው የክልሉ ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት በክልል ደረጃ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦
ሀ/ ጠቅላላ ጉባኤ
ለ/ የሥራ አመራር ቦርድ
ሐ/ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት
መ/ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ
ሠ/ ገምጋሚ ቦርድ
ረ/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች፣

አንቀጽ ፱

የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር፣

፩· የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፖሊስ እቅዶችን ፣ ስትራቴጂያዊ መመሪያዎችን በክልል ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍ ይሠጣል። በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣
፪· በቦርዱ የሚቀርቡለትን ዓመታዊ ሥራ ዕቅዶችና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣
፫· ለሥራ አመራር ቦርዱ አስፈላጊውን አጠቃላይ የሥራ መመሪያ ይሰጣል ተፈፃሚነቱን ይከታተላል።
፬· በቦርዱ ተዘጋጅቶ የሚቀርቡለትን ልዩ ልዩ ረቂቅ መመሪያዎች የማስፈፀሚያ ስልቶች እየመረመረ ያፀድቃል፣
፭· የሴክሬታሪያቱን የሥራ እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል ወቅታዊ የሥራ ሪፖርቱን ያዳምጣል ውሳኔዎችን ይሰጣል፣
፮· የገቢ ምንጮች የሚገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፣ ለአስፈፃሚው የሥራ አመራር ቦርዱ ክትትል እንዲያደርግ ተገቢውን መመሪያ ይሰጣል፣
፯· ከሥራ አመራር ቦርዱ በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት የአባልነት ጥያቄዎችን ተቀብሎ ይመረምራል፣ ያፀድቃል እንደ አስፈላጊነቱ ከአባልነት ይሰርዛል።
፰· የሥራ አመራር ቦርዱ አባላትን ይመርጣል ያፀድቃል፣
፱· የኦዲት ቁጥጥር ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል ይሽራል፣
፲· ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ለመከላከል ለሚደረጉ አገር አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስብሰባዎች ይካፈላል፣
፲፩· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ ለክልሉ በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚንቀሳቀሱ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር የተጠናከረ ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር ያደርጋል፣
፲፪· ዓላማዎችን ሊያሳኩ የሚችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።
፲፫· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፖሊሲ መተግበሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፦

6. Religious institutions in the Region .......... member
7. Association set up by the people living with HIV virus in the Region........................................ meber
8. Renowned individuals and local elders, as may be necessary.................................. member
9. Chairpersons of the zones' HIV/AIDS Prevention and Control Councils .............................. member
10. The Head of the Secretariat Office........... member

2. Organization

The HIV/AIDS Prevention and Control Council, which is accountable to the Council of Reigonal Government, shall comprise the following organs at Regional level;
(a) General Assembly
(b) Management Board
(c) Office of the Secretariat
(d) Audit and Control Committee
(e) Board of Evaluation
(f) Other Sub-committees necessary for the activities.

Article 9

Powers and Duties of the Council

The Council shall have the following powers and duties:
1. It shall provide support to implement HIV/AIDS policy, plans, and strategic directives in the Region; and sahll examine and approve the budget.
2. The Council shall examine and approve the annual work plans and budget submitted to it by the Board.
3. It shall give a general work directives to the Management Board; and follow up its implementation.
4. It shall examine and approve various draft directives and implementation mechanisms prepared and submitted to it by the Board.
5. The Council shall closely follow up the activities of the Secretariat; it shall hear periodic reports on work accomplishment and pass decisions.
6. It shall devise a way and means for getting incomes; and give proper instruction to the Executive of the Management Board to follow up it.
7. It shall examine and approve the applications of a membership on the basis of recommendations submitted to it by the Management Board; it shall dismiss member, as may be necessary.
8. The Council shall select and approve members for the Management Board.
9. The Council shall select and dismiss the members of the Audit and Contnrol Committee.
10. It shall participate in national, continental and international meetings on prevention of HIV/AIDS.
11. The Council shall, in cooperation withthe concerned organs establish strong relationship and cooperation with continental and international organizations working around the prevention of HIV/AIDS at national level;
12. The Council shall carry out other duties that enable it to achieve its objectives.
13. It shall follow up and supervise the execution of HIV/AIDS policy of the country.

## አንቀጽ ፲

### የም/ቤቱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

፩. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ፣ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይመራል፣
፪. የሥራ አመራር ቦርዱን እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል መመሪያዎችን ይሰጣል፣
፫. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድርነቱና በዚህ ም/ቤት ሰብሳቢነቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በም/ቤቱ አማካኝነት ከሚፈቀደው ገንዘብ ውጭ ለኤድስ ህሙማን፣ ተዛማች ጉዳተኞች እንዲሁም በኤድስ መከላከል ዙሪያ ለሚንቀሳቀሱ ተግባራት የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግ ሁኔታዎች ያመቻቻል፣
፬. የጽ/ቤቱን ኃላፊ ለሹመት አቅርቦ ያሾማል።
፭. በምክር ቤቱና በጽ/ቤቱ ጥረት የተገኙ የገቢ ምንጮች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል፣
፮. የጽ/ቤቱን የሂሳብ መዛግብት በታወቁ የሂሳብ ባለሙያዎች እንዲመረመር ያደርጋል።

## አንቀጽ ፲፩

### የምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ አመራር

፩. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል/ይሠራል/፣
፪. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየ3 ወሩ የሚካሄድ ሆኖ አስቸኳይ ጉዳይ ካጋጠመ ልዩ ስብሰባዎች ሊደረጉ ይችላሉ፤
፫. ምክር ቤቱ የራሱ የሆነ ስብሰባና የአሠራር ሥርዓት በሚመለከት ዝርዝር ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ፫

### የሥራ አመራር ቦርዱ

## አንቀጽ ፲፪

### መቋቋም

፩. አግባብነት ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ የም/ቤት ሥራ አመራር ቦርዱ ይቋቋማል።
፪. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለም/ቤቱ ይሆናል፤
፫. የቦርዱ አባላት በም/ቤቱ ይሰየማሉ /ይመረጣሉ/

## አንቀጽ ፲፫

### የቦርዱ አመራርና የስብሰባ ጊዜ

፩. ቦርዱ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጥ ሰብሳቢ ይኖረዋል የሴክሬታሪያቱም ኃላፊ በፀሐፊነት ለቦርዱ ያገለግላል፤
፪. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ስለ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ለቦርዱም ሰብሳቢ በተመሳሳይ ያገለግላል፣
፫. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል እንደ አስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

## አንቀጽ ፲፬

### የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣
፩. ለምክር ቤቱ የሥራ አስፈጻሚ አካል በመሆን ያገለግላል፣
፪. ከለጋሽ ግለሠቦች ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ የሃይማኖትና አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የቅርብና የጠበቀ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል።

## Article 10

### The Powers and Duties of the Chairperson

1. He shall preside over General Assembly, ordinary and extraordinary meetings.
2. He shall closely follow up the activities of, and give directives to, the Management Board.
3. In his capacity as the Head of the Regional Government and Chairperson of the council, shall, if he finds it necessary, facilitate conditoins to get financial support other than that allocated by the Council for the people infected with AIDS and affected by the disease indirectly as well as for the prevention activities launched around HIV/AIDS.
4. The Chairperson shall recoommend the Head of the Office for appointment.
5. He shall follow up and supervise that the funds got by the efforts of the Council and the Office are properly used.
6. He shall cause the auditing of the books of accounts be carried out by processional accounts.

## Article 11

### Procedure of Meetings

1. The Head of the Regional Government shall be a Chairperson of the Council
2. The ordinary meetings of the Council shall be held every three month, and extra-ordinary meetings may be held at any time in case of urgency.
3. The Council may issue detailed regulations regarding its meetings and rules of procedure.

## SECTION THREE
## THE MANAGEMENT BOARD

## Article 12

### Establishment

1. There shall be established a management board of the Council comprising members from the appropriate governmental and non-governmental organizations.
2. The Board shall be accountable to the Council.
3. Members of the Board shall be designate by the Council.

## *Article 13*

### *The Executive and Meetings*

1. The Chairperson of the Board shall be elected from among the members of the Council; and the Head of the Secretariat shall serve as a secretary of the Board.
2. The provisions regarding the Chairperson of the Council in Article 9 herein shall be also applicable to the Chairperson of the Board.
3. The Board shall, at least once in a month, hold an ordinary meeting. It may, as may be necessary, call an extra-ordinary meeting.

## *Article 14*

### *Powers and Duties of the Board*

The Board shall:
1. serve as being an executive organ of the Council;
2. establish close and strong relationship with donors, non-governmental, religious and international organizations;

፫. የኤች. አይ.ቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ የሚንቀሳቀሱትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ታዋቂ ግለሰቦች እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ በመካከላቸውም የሥራ ቅንጅት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
፬. የምክር ቤቱ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል
፭. ለምክር ቤቱ አባልነት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ወይም በዚሁ ምክር ቤቱ ውስጥ በአባልነት ሊመዘገቡ የሚገባቸውን ተቋማት እና ማኅበራት በሚመለከት የሚነሱ ጉዳዮችን በመገምገም ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ ያቀርባል፣
፮. ለሥራው መቃናት የሚያግዙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ያደራጃል፤ ሥራዎቻቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
፯. በሥልጣኑ ሥር የተቋቋሙትን ኮሚቴዎች ሰብሳቢና ፀሐፊ ይሰይማል፣
፰. በምክር ቤቱ የሚተላለፉትን ውሣኔዎችና የሚሰጡትን መመ ሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣
፱. በክልሉ የአስተዳደር እርከኖች እንደ አስፈላጊነቱ የፀረ–ኤድስ አስተባባሪና የቴክኒክ ኮሚቴዎች የሚቋቋሙበትን፣ የሚደራጁበትንና ሥራቸውን የሚያከናውኑበትን ዝርዝር መመሪያ ያዘጋጃል፣

## አንቀጽ ፲፭

## ስለ ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ

፩. ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት ገቢና ወጪውን የሚከታተልና የሚቆጣጠር የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል።
፪. የኮሚቴው ተጠሪነት ለምክር ቤቱ ይሆናል፣
፫. የኮሚቴው አባላት በምክር ቤቱ ይሰየማሉ

## አንቀጽ ፲፮

## ስለ ኦዲት ቁጥጥር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃለፊነቶች ይኖሩታል፣
ሀ) የጽሕፈት ቤቱንና የምክር ቤቱን ሂሣብ ጊዜውን ጠብቆ ይመረምራል፣
ለ) የጸሕፈት ቤቱ፣ የምክር ቤት ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ በአግባቡ መያዛቸውንና ለተፈቀደው አገል ግሎት ብቻ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
ሐ) በምክር ቤቱ ሰብሳቢ መመሪያ ሲሰጠው ድንገተኛ የሃሳብ ምርመራ ያደርጋል፣
መ) የራሱን የውስጥ አሠራር መመሪያ በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ስብሰባ አስቀርቦ ያስፀድቃል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ይውላል፣
ሠ) ከምክር ቤቱ እና ከስብሰባው የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፣

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ እና ፲፮.፩ ከሀ–ሠ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በማናቸውም ጊዜ የሴክሬታሪያቱን የሂሣብ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል።

## አንቀጽ ፲፯

## ስለ ሌሎች ኮሚቴዎች መቋቋም፤

እንደ አስፈላጊነቱ ተጠሪነታቸው ለሥራ አመራር ቦርድ የሆነና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፣
በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚቋቋሙት ንዑሳን ኮሚቴዎች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት የሥራ አመራር ቦርዱ በሚያወጣው ሕግ መሠረት ይወሰናል።



3. coordinate the activities of non-governmental organizations and renowned individuals engaged in prevention and control of HIV/AIDS in the Region; and facilitate conditions for integrated activities between them;
4. prepare annual work plan and supporting budget of the Council and submit it to the same; and follow up and supervise their implementation upon approval;
5. examine and present to the Chairperson the applications for the membership of the Council, and issues relating to membership of institutions and associations;
6. organize, as may be necessary, various committees necessary for the efficient execution of its activities; follow up and supervise their activities closely;
7. assign chairpersons and secretaries to the committees set up under its authority;
8. implement decisions adopted, and directives given by, the Council;
9. prepare detailed directives as may be necessary, for setting up and organizing Anti-AIDS Coordinating and Technical Committees at Regional administrative levels.

## *Article 15*

## *Audit and Control Committee*

1. The Council shall have Audit and Control Committee that follows up and inspects its income and expense in accordance with provisions herein.
2. The Committee shall be accountable to the Council.
3. Members of the Committee shall be designated by the Council.

## *Article 16*

## *Powers and Duties of the Committee*

1. The Audit and Control Committee shall:
   (a) audit the accounts of the Office and the Council;
   (b) follow up and supervise that the movable and immovables, of the Office and the Council are properly managed, and used only for the purpose they are intended to;
   (c) carry out a sudden audits when instructed by the Chairperson to do so;
   (d) prepare its internal rules of procedure and submit them to the council for approval; and implement the same upon approval;
   (e) discharge other duties entrusted to it by the Council.
2. Without prejudice of Article 15 and Sub-Articles (a)-(e) of Article 16 herein, the Regional Office of the Auditor General may at any time carry out audits of the Secretariat accounts.

## *Article 17*

## *Establishment of Sub-Committees*

1. There shall be established various committees which are accountable to the Management Board, and necessary for the activities.
2. The Management Board shall determine by law the powers and duties of the sub-committees to be established pursuant to Sub-Article 1 of this Article.

## አንቀጽ ፲፰

### ስለ ዞኑ ኤች·አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት ማቋቋም፤

፩· ተጠሪነቱ ለክልል አቀፍ ምክር ቤት የሆነ ፀረ–ኤድስ አስተ ባባሪ ም/ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት በዞን ደረጃ ተቋቁሟል።

፪· የአስተባባሪ ም/ቤት ሰብሳቢ የዞን መስተዳድር ሊቀመንበር ይሆናል፤

፫· የም/ቤቱ ፀሐፊ የዞኑ ኤች· አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣ ጠሪያ ጽ/ቤት አስተባባሪ /ፎካል ፐርሰን/ ይሆናል፤

፬· የም/ቤት አባላት አስተዋፆኦና ስብጥር በእያንዳንዱ ዞን ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ ይወሰናል፤ የዞን መስተዳድር ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ኃላፊዎችና የሕዝባዊ ማኅበራት ተወካዮች ይሆናሉ ሆኖም ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ተግባር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ተቋማትና ግለሰቦች የአባልነት ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል፤

፭· የም/ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይሆናል እንደ አስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባዎች ሊጠሩ ይችላሉ፤

## አንቀጽ ፲፱

### የዞን ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር፤

፩· ምክር ቤቱ የተቋቋመባቸው አላማዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ በዞኑ ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል።

፪· በዞኑ ውስጥ በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ግለሰ ቦችና ድርጅቶች አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ተገቢው ጥሪ ያደርጋል፤

፫· መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጥረት ያስተባብራል፤ በመካከላቸው የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታ ዎችን ያመቻቻል፤

፬· በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ በሚደረጉ ክልል አቀፍ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት የዞኑን ችግር ይገልፃል ለችግሩም መፍትሔውን በጋራ ይፈልጋል።

፭· ለዞኑ የሚያስፈልገውን በጀት ያፈላልጋል፤ ይመድባል፤ በትክክል በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

፮· የዞኑ ህብረተሰብ ስለ ኤች· አይ·ቪ/ኤድስና ስለሚያስከትለው ጉዳት ግንዛቤ እንዲኖረው የተለያዩ ስብሰባዎችና አውደ ጥናቶች እንዲዘጋጁ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፯· የዞኑን የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ገጽታ መረጃዎች ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል እንደ አስፈላጊነቱም ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያስተላልፋል፤

፰· በሥሩ ላሉ ንዑስ አስተባባሪ ኮሚቴዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፱· በሥሩ ባሉ ወረዳዎች የሚገኙ የፀረ–ኤድስ አስተባባሪ ም/ ቤቶች እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲· የሥራ እንቅስቃሴን በተመለከተ ለም/ቤቱ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፩· ከሥራ ባህሪው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## አንቀጽ ፳

### ስለ ወረዳ ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት መቋቋም፤

ተጠሪነቱ ለታቀፈበት ዞን ም/ቤት የሆነ የፀረ–ኤድስ አስተ ባባሪ ም/ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት በወረዳ ደረጃ ተቋቁሟል፤

የም/ቤቱ ሰብሳቢ የወረዳ ምክር ቤት ሊቀመንበር ይሆናል፤

የም/ቤቱ ፀሐፊ በወረዳው ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት አስተባባሪ /ፋሲሊቴተር/ይሆናል።

ም/ቤቱ አባላት ተዋጽኦና ስብጥር በእያንዳንዱ ወረዳ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ይወሰናል፤

ም/ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይሆናል ሆኖም አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊጠራ ይችላል።

## Article 18

### *Establishment of Zone HIV/AIDS Prevention and Control Council*

1. There is hereby established Anti-AIDS Coordinating Council at Zonal level which is accountable to the Council of the Region.
2. Chairman of the Zone Administration shall be a chairperson of the Coordinating Council.
3. The Secretary of the Zone shall be a focal person or coordination of the Zone HIV/AIDS Prevention and Control Office.
4. The number and combination of members of the Council shall be determined on the basis of objective condition of each zone. The Heads of the Coordinating Offices of Zone Administration and representatives of civil associations shall be the member of the Council; however; the institutions and individuals that can render high contribution in prevention and control of HIV/AIDS shall be given priority of membership.
5. Ordinary meeting of the Council shall be held once in a month; however, extraordinary meetings may be called as may be necessary.

## Article 19

### *Powers and Duties of HIV/AIDS Prevention and Control Council of Zone*

1. It shall devise a way and means to effectively implement its objectives in the Zone.
2. It shall call on individuals and organizations engaged in the activities of prevention and control of HIV/AIDS in the Zone to provide all necessary assistance for it.
3. It shall coordinate the efforts of governmental and non-governmental organizations; and facilitate conditions to create integrated activities between them.
4. The Council shall attend, and present the problems of the Zone at, conferences to be held on the prevention of HIV/AIDS at the Regional level; and it shall seek solutions for such problems in joint discussion.
5. It shall seek and allocate budget necessary for the Zone; and shall follow up and supervise that it has been properly used.
6. The Council shall facilitate conditions to cause the preparation of different conferences and workshops with a view to creating public awareness in Zone of HIV/AIDS and the disaster it causes.
7. The Council shall collect and analyze data relating to HIV/AIDS in the Zone; and forward them; as may be necessary, to the concerned sectors.
8. It shall provide necessary support for the sub-coordinating committees.
9. It shall follow up and supervise the activities of the Anti AIDS Coordinating Councils of the Woredas.
10. It shall submit periodic reports on its activities to the Council.
11. The Council shall discharge other duties related to its activities.

## Article 20

### *Establishment of Woreda HIV/AIDS Prevention and Control Council*

1. There is hereby established Anti-AIDS Coordinating Council at Woreda level which is accountable to the Council of its Zone.
2. The Chairman of the Council of Woreda shall be Chairperson of the Coordinating Council.
3. The Secretary of the Council of Woreda shall be a facilitator or co-ordination of the Woreda HIV/AIDS Prevention and Control Office.
4. The representation and combination of members shall be determined on the basis of the concrete condition of each Woreda.
5. An ordinary meeting shall be held once in a month; however, the Council may call extraordinary meetings.

## አንቀጽ ፳፩
## የወረዳው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር፤

የወረዳው አስተባባሪ ም/ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

፩. በወረዳው ውስጥ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎች ዕቅዶችን ያወጣል አፈፃፀማቸውን ይከታተልል።

፪. በወረዳው ውስጥ በኤች.አይቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችና ድርጅቶች አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋል፤

፫. የወረዳው ነዋሪ ሕዝብ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ስለጉዳቱ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ የተለያዩ ስብሰባዎች፣ አውደ ጥናቶችና ሲንፖዚየሞችን ያዘጋጃል፤

፬. ለለጋሽ ድርጅቶችና ለመንግሥት አካላት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ የፕሮጀክት ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ፕሮጀክቶችን ሠርቶ ያቀርባል፣ የበጀት ድጋፍ ሲገኝም በተግባር ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፭. በሥሩ የሚገኙ ቀበሌዎች ፀረ-ኤድስ ክበባት እንቅስቃሴን በቅርብ ይከታተላል፤

፮. የወረዳው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ገጽታ መረጃዎች ያሰባስባል ያጠናቅራል እንደ አስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሪፖርት ያደርጋል፤

፯. ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሕሙማንና ቤተሰቦች አስፈላጊው እንክብካቤ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፰. የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ ለሚመለከተው የዞን አስተባባሪ ምክር ቤት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል።

፱. ከሥራ ባህሪው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ ፳፪
## ስለ ቀበሌ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ መቋቋም

፩. ተጠሪነቱ ለታቀፈበት ወረዳ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት የሆነ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት በቀበሌ ደረጃ ተቋቁሟል፤

፪. የኮሚቴው ሰብሳቢ የቀበሌ መስተዳድር ሊቀመንበር ይሆናል፤

፫. የኮሚቴው ፀሀፊ በቀበሌው ሥራ አስፈፃሚ የሚሰየም አስተ ባባሪ ወይም ተወካይ ይሆናል፤

፬. የኮሚቴው አባላት ተዋፅኦና ስብጥር በእያንዳንዱ ቀበሌ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ ይወሰናል፤

፭. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይሆናል። ሆኖም አስቸኳይ ስብሰባዎችን ከማድረግ በዚህ አዋጅ አይታገድም፤

## አንቀጽ ፳፫
## የቀበሌ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የቀበሌ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

፩. በቀበሌው ውስጥ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ ለሚሠሩት ሥራዎች ዕቅዶችን ያወጣል ይተገበራል፤

፪. በቀበሌው ውስጥ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚደረገውን ሁለገብ እንቅስቃሴ ያስተባብራል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፫. የቀበሌውን ነዋሪ ኅብረተሰብ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስና በሚያስከትለው ጉዳት ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ ስብሰባዎች በማዘጋጀት ትምህርት ይሰጣል፤

፬. በበሽታው ለተያዙና ለተጎዱ ግለሰቦች አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤

## *Article 21*
## *Powers and Duties of the Woreda HIV/AIDS Prevention and Control Council*

The Woreda Coordinating Council shall:

1. draw up plans of the activities to be carried out around HIV/AIDS in the Woreda; and follow up their implementation;
2. Call on the individuals and organizations working around HIV/AIDS in the Woreda to provide all necessary assistance;
3. prepare different conferences, workshops and symposiums to make the people of the woreda aware of HIV/AIDS and its impacts;
4. initiate project proposals which will help donor organizations and government organs to prevent and control HIV/AIDS; prepare projects and submit them to such organizations and organs; and follow up their implementation when supporting budget is found;
5. closely follow up the activities of Anti-AIDS Clubs in the Kebeles of the Woreda;
6. collect and analyze data relating to HIV/AIDS situation in the Woreda; and report to the concerned sectors as may be necessary;
7. facilitate conditions so that the people infected with HIV/AIDS and their family members will get necessary care;
8. submit periodic reports on its activities to the Coordinating Council of Zone;
9. discharge other duties related to its activities.

## *Article 22*
## *Establishment of Kebele Anti-AIDS Coordinating Committee*

1. There is hereby established Anti-AIDS Coordinating Committee at Kebele level that is accountable to the Woreda HIV/AIDS Prevention and Control Council.
2. The Chairperson of the Kebele Administration shall be a chairperson of the Committee.
3. The Secretary of the Committee to be designated by the Executive shall be a coordinator or representative of the Committee.
4. The representation and combination of members of the Committee shall be determined on the basis of concrete conditions of each Kebele.
5. An ordinary meeting of the Committee shall be held once in a month extraordinary meetings shall, however, be called as may be necessary.

## *Article 23*
## *Powers and Duties of Kebele Anti-AIDS Coordinating Committee*

Kebele Anti-AIDS Coordinating Committee shall:

1. formulate and execute plans of the activities to be carried out around HIV/AIDS prevention in the Kebele;
2. coordinate, and give necessary support to, all-round activities carried out around HIV/AIDS prevention in the Kebele;
3. prepare different meetings and give education to the Kebele dwellers to raise their awareness of HIV/AIDS and the disaster it causes;
4. devise ways and means that enable to provide necessary assistance for the individuals infected with, and affected by the disease;

፭· የቀበሌውን የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ገጽታ መረጃዎች ያሰባስባል ያጠናቅራል እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋል፤

፮· ማኅበረሰቡ ለተለያዩ ዓላማዎች የሚያቋቁሟቸውን የዕድር፣ ማኅበርና የዕቁብ ተቋማት…ወዘተ በመጠቀም ኅብረተሰቡ በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ላይ ያለውን ግንዛቤ እንዲያሳድግ ይቀሰቅሳል፤

፯· ለሚመለከተው ወረዳ ፀረ–ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ ወቅታዊ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

፰· ከሥራ ባህሪው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፱· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የኤች· አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ መተግበር።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፳፬
### ስለምክር ቤቱ የገቢ ምንጭ

ሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፣

፩· ከብሔራዊ ሴክራታሪያት ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ዩኒት

፪· ከክልሉ መንግሥት የሚመደብ በጀት፣

፫· መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ ለጋሽ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች የሚገኝ የፋይናንስና የቁሳቁስ ድጋፍ፣

### አንቀጽ ፳፭
### ስለሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤት የበጀት ዓመት

— የሴክሬታሪያቱ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግሥት የሚሠራበት የበጀት ዓመት ይሆናል፤

### አንቀጽ ፳፮
### ስለበጀት አስተዳደርና ሂሣብ አያያዝ

፩· የሴክሬታሪያቱ የራሱ ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሣብ በስሙ ይከፍታል፤

፪· የሴክሬታሪያቱ የራሱ የሆነ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይኖረዋል።

### አንቀጽ ፳፯
### ስለማንኛውም መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ግዴታዎች

፩ በክልሉ ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ መንግሥታዊ መ/ቤቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመሳተፍ ፣ ድጋፍና ትብብር የማድረግ ግዴታ አለባቸው፣

፪ በክልሉ ኤች· አይ·ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የመሳተፍ ኃላፊነት አለባቸው፡—

### አንቀጽ ፳፰
### ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው አሠራሮች

— የኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት አስመልክቶ እስካሁን ድረስ በክልሉ ውስጥ ፀንቶ የሚሠራበት ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ ሆኖ ከተገኘ ይህንን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### አንቀጽ ፳፱
### ደንብ የማውጣት ሥልጣን

— የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

### አንቀጽ ፴
### አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

— ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ሰኔ........................፲፱፻፺፬ ዓ·ም

እስማኤል አሊሴሮ
የአፋር ብ/ክ/መንግሥት ርዕስ መስተዳድር

5. collect and analyze data relating to HIV/AIDS situatio in the Kebele; and submit such data to the concrene sector as may be necessary;
6. agitate the community at community-based institution such as Idir, Ikub, associations, etc to raise its wareness o HIV/AIDS;
7. Submit periodic reports on its activities to the wored Anti-AIDS Coordinating Committee;
8 discharge other duties related to its activities;
9. implement HIV/AIDS prevention and control policy o the country;

## SECTION FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### Article 24
### Source of Income of the Council

The Sources of income of the Office of the Secretariat shall be the following:

1 National Secretariat Project Coordination Unit;
2. Budget allocated by the Regional State;
3. Governmental and non-governmental institutions; donor organizations as well as individuals.

### Article 25
### Fiscal Year

The Secretariat's fiscal year shall be the fiscal year of the Regional State.

### Article 26
### Budget Administration and Accounting

1. A current account shall be opened in the name of the Secretariat.
2. The Secretariat shall have its own accounting system.

### Article 27
### Obligations of Governmental and Non-Governmental Institutions

1. Government organs and non-governmental organizations shall have obligations to participate and cooperate in, and give support to, the activities carried out by the Office of the Secretariat to prevent and control HIV/AIDS in the Region.
2. All the people living in the Region have responsibility to participate in the activities carried out to prevent and control HIV/AIDS in the Region.

### Article 28
### Inapplicability

Any law and practices inconsistent with this Proclamation shall not be applicable to matters provided for herein.

### Article 29
### Powers to Issue Regulations

The Council of Regional Government shall have the powers to issue regulations to implement this Proclamation.

### Article 30
### Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Afar Region Negarit Gazeta.

Done at Semera, this 7th day of July, 2002

Ismael Ali Sero
Head of the Afar National Regional State

QAFAR XOLETIH RAKAKAYA

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

## AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አይሳኢታ – ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 6
AYSAITA – 8th July, 1999

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ........................ ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 7/1999
Administration of Finance of the Afar National Regional State Proclamation ........................ Page 1

### አዋጅ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፩

### የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ

መንግሥት ኃላፊነቱን በትክክል መወጣት እንዲችል ዘመናዊ እና ቀልጣፋ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ያለበት በመሆኑ ፤

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋያናንስ አስተዳደር የሚመራበትን መሠረታዊ ፅንሰ ሃሣብ ፤ መርህ እና ዋና ዋና ጉዳዮች መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በአፋር ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፪·፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪· **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩· "በዓይነት የተሰጠ ዕርዳታ" ማለት የክልሉ መንግሥት ከገንዘብ ሌላ በዕቃ ወይም በአገልግሎት መልክ በሁለት ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነት ወይም ከሌሎች ምንጮች የሚቀበለው ማናቸውም ዕርዳታ ነው ፤

### PROCLAMATION NUMBER 7/1999
### PROCLAMAITON TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF FINANCE OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL State

WHEREAS it is necessary for the government to properly accomplish its responsibilities by implementing a modern and efficient system of administration of finance;

WHEREAS it is found necessary to define the basic concepts, priniciples and elements that guide the administration of finance of the Afar National Regional State.

NOW THEREFORE– In accordance with Article 47(2.2) of the Constitution of the Afar National Region, it is hereby proclaimed as follows.

### PART ONE
### GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Administration of Finance of the Afar National Regional State Proclamation No. 7/1999"

2. Definition

In this Proclamation:

1. "Aid Provided in Kind" means, an assistance excluding monetary once procured by the regional state in the form of goods or services through bilateral or multilateral agreements or other sources;

፪. "መፍቀድ" ማለት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ለመክፈል የሚያስችል በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጥ ማናቸውም ሥልጣን ነው ፤

፫. "የካፒታል ወጪ" ማለት ቋሚ ሀብት ለማፍራት ወይም ለማሻሻል ወጪ የሚደረግ ሂሣብ ሲሆን ፤ ለምክር አገልግሎት የሚደረገውን ወጪ ይጨምራል ፤

፬. "የተጠቃለለ ፈንድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በማናቸውም97106 ኛ3 የመንግሥት መ/ቤት ስም በክልሉ የፋይናንስ ቢሮ በተከፈተው የባንክ ሂሣብ ውስጥ ገቢ የተደረገ የክልሉ መንግሥት ገንዘብ ፤ የመንግሥት መ/ቤቶች ለክፍያ እንዲውል በጥሬ ገንዘብ የያዙት እንዲሁም በዓይነት የተገኘ እርዳታ ነው ።

፭. "ግዴታ" ማለት በውል ፤ በስምምነት ወይም በሕግ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ የሚፈጠር ኃላፊነት ነው ፤

፮. "ክፍያ" ማለት በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የተቀመጠውን የመንግሥት ገንዘብ ወጪ ማድረግ ነው ፤

፯. "የክልል መንግሥት" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው ፤

፰. "የበጀት ዓመት" ማለት ከሐምሌ ፩ እስከ ሰኔ ፴ ቀን ያለው ጊዜ ነው ፤

፱. "የችሮታ ጊዜ" ማለት ባለፈው የበጀት ዓመት ርክክቡ ለተፈፀመ ዕቃ እና ለተሰጠ አገልግሎት ባለፈው የበጀት ዓመት ውስጥ የቀረበው የክፍያ ጥያቄ ካለፈው ዓመት በጀት ላይ የሚከፈልበት ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ሃምሌ ፴ ቀን ድረስ ያለው ቀናት ነው ።

፲. "መቅረት" ማለት ወጪ ለማድረግ የተሰጠው ፈቃድ ማብቅያ ጊዜ ነው ።

፲፩. "የቢሮ ኃላፊ እና ቢሮ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ እና የፋይናንስ ቢሮ ነው ።

፲፪. "ሌሎች ተሰብሣቢ ሂሣቦች" ማለት ከግብር እና ከመቀጫ በስተቀር ለክልሉ መንግሥት ሊከፈል የሚገባ ማናቸውም ገንዘብ ነው ፤

፲፫. "የመንግሥት መ/ቤት" ማለት ማንኛውም በከፊል ወይም በሙሉ በክልል መንግሥት በጀት የሚተዳደር መሥሪያ ቤት ነው ።

፲፬. "የመንግሥት ገንዘብ" ማለት የቢሮው ኃላፊ ወይም ማናቸውም የክልሉ መንግሥት ቢሮ ባለሥልጣን ወይም ማናቸውም በክልሉ መንግሥት ስም ገንዘብ ለመቀበል ፤ ወይም ለመሰብሰብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው የተቀበለው ወይም የሰበሰበው (ወይም በተሰብሳቢነት የያዘው) ማናቸውም የክልሉ መንግሥት ገንዘብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል ፤
   ሀ. የክልል መንግሥት ልዩ ሂሣቦች እና ከእነዚህ የሚገኝ ገቢ፤
   ለ. የክልል መንግሥት ገቢዎች ፤
   ሐ. የክልል መንግሥት የዋስትና ሰነዶችን በማውጣትና በመሸጥ የሚሰበሰበው ገንዘብ ፤
   መ. የክልል መንግሥት ወይም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በባለሁለት ወገን ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነት ወይም ከሌሎች ምንጮች በብድር ወይም በእርዳታ የሚያገኘው ገንዘብ ፤
   ሠ. ከፌዴራል መንግሥት የሚላክ የበጀት ድጋፍ
   ረ. በዓይነት የሚገኝ እርዳታ ፤

፲፭. "የክልሉ መንግሥት ንብረት" ማለት ከመንግሥት ገንዘብ እና መሬት በስተቀር የክልል መንግሥት ሀብት የሆነ ማናቸውም ንብረት ነው ፤



2. "Appropriation" means any authorization given by the Regional Council to effect payment out of the general fund;

3. "Capital Expenditure" means an outlay for the acquisition of or improvements to fixed assets, and includes expenditures made for consultancy services;

4. "Consolidated Fund" means all public fund of the Regional Government that is deposited in a bank account opened by the Regional Office of Finance in the name of any pubic office, cash held bypublic offices for disbursement and aid that is obtained in kind;

5. "Commitment" means an obligation that exists when conditions provided in a contract, an agreement or by law mature;

6. "Disbursement" means the release of public fund that is held in the consolidated fund;

7. "Regional Government" means the National Regonal Government of Afar;

8. "Fiscal Year" means the period between 1st Hamle to 30th Sene;

9. "Period of Grace" means thirty (30) days that fall between 1st Hamle till 30th Hamle during which period payment is effected from the previous fiscal year's appropriation for deliveries of goods and services that were made in the previous fiscal year;

10. "Lapse" means termination of the period of spending approval;

11. "Head of Office" and "Office" means the Head of the Office of Finance and the Office of Finance;

12. "Other Receivables" means any revenue owing to the Regional government except tax and penalty;

13. "Public Office" means any organ that functions by budget allocated, wholly or partly, by the Regional Government;

14. "Public Fund" means all money received or collected (or receivable) by the Head of the Office or by any authority of the Regional Government who is entrusted with the power to receive or collect such money and includes;
   (a) special funds of the Regional Government and the revenue generated thereof;
   (b) revenues of the Regional Government;
   (c) money raised through issuance or sale of securities of the Regional Government;
   (d) money obtained by the Regional Government or other public office as loans or assistance through bilateral or multilateral agreements or other sources;
   (e) budgetary subsidy allocated by the Federal Government; and
   (f) aid provided in kind;

15. "Property of the Regional Government" means all money except public funds and land, which is the property of the Regional Government;

፲፮· "ምህረት" ማለት ግብርን ፣ መቀጫን ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሣቦችን መማር ወይም ነፃ ማድረግ ነው ፣

፲፯· "ዕዳ መሠረዝ" ማለት የክልል መንግሥት ተሰብሣቢ ሂሣቦችን ግዴታዎችን ፡ ወይም ሌላ የይገባኛል ጥያቄዎች ከሂሣብ መዝገብ መሠረዝ ነው ፣

፲፰· "የዋስትና ሰነድ" ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈፀም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ነገር ሲሆን ፡ የግምጃ ቤት ሰነድን የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል ፣

፲፱· "የጥሪት ፈንድ (ሲኒኪንግ) ፈንድ" ማለት በረጅም ጊዜ እንዲመለስ የተወሰደን ብድር ለመክፈል ፣ ቋሚ ንብረቶችን ለመተካት ወይም የክልሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣው ደንብ ለሚወሰነው ሌላ ማናቸውም ዓላማ እንዲውል ኢንቨስት የሚዳረግ ገንዘብ ነው ።

፳· "የበጀት ድጋፍ" ማለት የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥት የሚሰጠው ዓመታዊ የበጀት ድጋፍ ነው ።

፳፩· "ዝውውር" ማለት ከአንድ አርዕስት ፣ ንዑስ አርዕስት ፣ ፕሮጀክት ወይም የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሚደረግ የተፈቀደ የበጀት ዝውውር ነው ።

፳፪· "የተለዩ ዓላማ" ማለት በሕግ በተሰጠ ሥልጣን መሠረት ተለይቶ በሚያዝ የመንግሥት ገንዘብ የሚከናወን የክልል መንግሥት ተግባር ነው።

## ፫· የተፈፃሚነት ወሰን

፩· ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆነው በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ ነው ።

፪· የክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አዋጁ የሚመለከታቸውን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር በየጊዜው ያወጣል ።

## ፬· ኃላፊነት እና ተጠያቂነት

የእያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡት ደንቦችና ድንጋጌዎች በኃላፊነት በሚመራው መ/ቤት ውስጥ ሙሉ በሙሉና በተገቢው መንገድ ተግባራዊ መሆናቸውን በማረጋገጥ ረገድ ለክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠያቂነት አለበት ።

## ክፍል ሁለት
## የመንግሥት ገንዘብ ስለመሰብሰብና ገቢ ስለማድረግ

## ፭· የተጠቃለለ ፈንድ

፩· በተለየ ሁኔታ እንዲቀመጥ በሕግ ከተፈቀደለት በስተቀር የክልሉ መንግሥት ገንዘብ ሁሉ ገቢ የሚደረግበት አንድ የተጠቃለለ ፈንድ ይኖራል ።

፪· በዓይነት የተሰጠ እርዳታ ቢሮው ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር የሚያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ በሚወሰነው ዋጋ መሠረት በተጠቃለለ ፈንድ ውስጥ ይመዘገባል ።

፫· ቢሮው የተጠቃለለውን ፈንድ ይይዛል ፣ ያስተዳድራል።

፬· ቢሮው በማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ስም የመንግሥት ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሣብ ሊከፍት ይችላል ። የዚህ ዓይነቱም የባንክ ሂሣብ የተጠቃለለው ፈንድ አካል ይሆናል።

## ፮· የመንግሥት ገንዘብ አሰባሰብ

፩· በሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር ማናቸውም የመንግሥት ገንዘብ መሰብሰብ አይቻልም ።

፪· ማናቸውም የመንግሥት ገንዘብ ያለፋይናንስ ቢሮው ሕጋዊ ደረሰኝ ሊሰበሰብ አይችልም ።



16. ''Remission'' means the discharge or cancellation of taxes, penalties or other receivables due to the Regional State;
17. ''Write-Off'' means the cancellation from the books of accounts of receivables, obligations or claims that are due to the Regional State;
18. ''Security'' means something given or pledged to execute a financial promise or financial obligation and includes a treasury bill, promissory instrument and bond;
19. ''Sinking Fund'' means a fund invested to repay a debt that is acquired on a long-term basis, to replace fixed assets, or allocated for any other purpose to be determined by Regulations issued by the Regional Executive Committee;
20. ''Budget Subsidy'' means the annual budgetary subsidy provided by the Federal Government to the Regional State;
21. ''Transfer'' means the authorized transfer of an approved budget from one head, subhead, project or item to another;
22. ''Special Purpose'' means an activity of the Regional State undertaken by an earmarked public fund in accordance with power provided bylaw;

3. *Scope of application*
   1. This Proclamation is applicable to public offices.
   2. The Regional Executive Committee shall, from time to time, issue the list of public offices to be governed by this Proclamation.

4. *Responsibility and Accountability*

The executive head of every public office shall be accountable to the Regional Executive Committee with regard to ensuring the full and proper implementation of the provisions of this Proclamation and provisions of Regulations in the office in which he/she is responsible.

## PART TWO
## Collection and Deposit of Public Fund

5. *Consolidated Fund*
   1. Unless and otherwise a special procedure of deposite is provided by law, there shall be one Consolidated Fund into which all the funds of the Regional State is deposited.
   2. Aid in kind shall be registered in the Consolidated Fund by the office at a value determined by assessing the information obtained from concerned public offices.
   3. The office shall hold and administer the Consolidated Fund.
   4. The office may open a bank account in the name of a public office for the deposit of public funds. Such kind of bank account shall form part of the Consolidated Fund.

6. *Collection of Public Funds*
   1. No public fund shall be collected unless authorized by law.
   2. No public fund shall be collected without the exchange of receipts of the office.

፫· ማናቸውንም የመንግሥት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበሰብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ቢሮው በሚያ ወጣው መመሪያ መሠረት ገንዘብ የተቀበለበትን እና ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ መዝግቦ ይይዛል ።

፯· የመንግሥት ገንዘብ ስለማስቀመጥ

፩· በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ በመመዝገቡ በዚሁ እንደ ተቀመጠ ከሚቆጠር በዓይነት ከሚገኝ እርዳታ በስተቀር ማናቸውም የመንግሥት ገንዘብ በፋይናንስ ቢሮው ስም በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ይቀመጣል ።

፪· ለተለየ ዓላማ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ ለዚሁ ዓላማ እንዲውል በሚፈቅደው አዋጅ መሠረት ወጪ ሆኖ ሊከፈል ይችላል ።

፰· ወለድ

፩· ለተለየ ዓላማ እንዲውል በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የተቀመጠው ገንዘብ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ወለድ ሊከፈልበት ይችላል ።

፪· የወለዱ መጠን ቢሮው ከአስቀማጩ ጋር በመመካከር በሚያቀርበውና የክልሉ ምክር ቤት በሚያፀድቀው ልክ ይሆናል ።

፫· በቢሮው ወይም በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም በንግድ ባንኮች በተከፈቱ የባንክ ሂሣቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ ላይ ሁሉ ባንኮቹ ወለድ ይከፍላሉ ። የወለዱ መጠን በባንኩ እና በቢሮው መካከል በሚደረገው ስምምነት ይወሰናል ።

ክፍል ሦስት

ዕዳን ስለመማር ፣ ስለመሠረዝና ስለ ልዩልዩ ክፍያዎች

፱· የዕዳ ምህረት

፩· የክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት ከቢሮው በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ከማንኛውም ግብር ፣ በዚሁ ላይ ከሚከፈል ወይም ከተከፈለ ወለድ ጭምር ምህረት ሊያደርግ ይችላል ።

፪· ቢሮውን በበላይነት የሚመራው የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት በማንኛውም ግብር ላይ ከተጣለ መቀጫ በዚሁ ላይ የሚከፈልን ወይም የተከፈለን ወለድ ጭምር ምህረት ሊያደርግ ይችላል ።

፫· ቢሮውን በበላይነት የሚመራው የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲያፀድቅለት ማናቸውንም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሣቦችን እንዲሁም በዚሁ ላይ የተከፈለን ወይም የሚከፈለን ወለድ ጭምር ሊምር ይችላል ።

፲· ምህረት የሚደረግባቸው ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፱ በተደነገገው መሠረት የሚደረግ ምህረት በሙሉ ወይም በከፊል ፣ በገደብ ወይም ያለገደብ ሆኖ፤

ሀ· ታክስ ፣ መቀጫ ወይም ሌሎች ተሰብሣቢ ሂሣቦችን ለማስገባት ጉዳዩ ለክስ ከተመራ ፣ ክሱ ከተጀመረ ወይም ከመጀመሩ በፊት ፤

ለ· ታክስ ፣ መቀጫ ወይም ሌሎች ተሰብሣቢ ሂሣቦች በፍርድ አፈጻጸም ከመከፈላቸው በፊት ወይም ከተከፈሉ በኋላ ፤

ሐ· ታክስን ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሣቦችን የሚመለከት ማናቸውንም ጉዳይ ወይም ጉዳዮች ሲኖሩና የመክፈል ኃላፊነት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ከመድረሣቸው በፊት ሊሰጥ ይችላል ።

3. Every person who is authorized to receive or collect public funds shall keep a record of receipts and deposits of money in accordance to directives to be issued by the Office.

7. *Deposit of Public Funds*

1. All public funds shall be deposited in the Consolidated Fund to the credit of the Office except aid in kind which is registered in the Fund and deemed deposited thereof.
2. Money deposited in the Consolidated Fund for a special purpose may be paid out in accordance to the proclamation that determined it for that purpose.

8. *Interest*

1. Interest may be paid from the Consolidated Fund to the amount that is deposited in the Fund and which is earmarked for a special purpose.
2. Subject to the approval of the Regional Council, interest rate shall be fixed by the Office in consultation with the depositor.
3. The National Bank of Ethiopia or commercial banks shall pay interests on funds held in account opened in the name of the Office or other public offices. The interest rate shall be fixed by an agreement made between the bank and the Office.

## PART THREE

### Remissions, Write-Offs and Fees and Charges

9. *Remission*

1. The Regional Executive Committee may, when it believes the existence of good cause and upon the recommendation made by the Office, remit tax including any interest payable or paid thereof.
2. The member of the Regional Executive Committee who administers the Office as a superior may, when it believes the existence of good cause and in accordance with directives issued by the Regional Executive Committee, remit any penalties on taxes including interest payable or paid thereof.
3. The member of the Regional Executive Committee who administers the office as a superior may, upon approval by the Executive committee, remit any other receivables including interest paid or payable thereof.

10. *Conditions for Remission*

A remission made under the above mentioned Article 9 may be total or partial and with or witout condition and may be granted:

(a) pending, after or before the institution of a suit for the recovery of taxes, penalties on other receivables.

(b) before or after the payment of taxes, penalties on other receivables through the execution of judgments.

(c) with respect to the existence of any claim or claims related to taxes or other receivables whose conditions of liablity of payment has not yet matured.

፲፩· <u>የተከፈለ ገንዘብን ስለመማር</u>

በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ በማናቸውም አዋጅ መሠረት ምህረት የተደረገው በተከፈለ ገንዘብ ላይ ሲሆን ፤ ገንዘቡ ለዚሁ ዓላማ በተለይ ከተመደበው ሂሣብ ውስጥ ወጪ ተደርጎ ይከፈላል።

፲፪ <u>ምህረት የተደረገለት ዕዳ ሪፖርት ስለማድረግ</u>

በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ በማናቸውም አዋጅ መሠረት በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ምህረት የተደረገለት ዕዳ ቢሮው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በሚቀርበው የመንግሥት ሂሣብ ውስጥ ተጠቃሎ ሪፖርት ይደረጋል።

፲፫· <u>ዕዳን ስለመሠረዝ</u>

፩· ለክልል መንግሥት መግባት ያለበት ማንኛውም ተሰብሳቢ ሂሣብ ፤ መፈፀም ያለበት ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ በሙሉ ወይም በከፊል ስለሚሰረዝበት ሁኔታ የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ሊያወጣ ይችላል ። እንደዚህ ያሉት ደንቦች ፤

ሀ) ማንኛውም ተሰብሳቢ ሂሣብ ፤ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ የሚሠረዝባቸውን መመዘኛዎች፤

ለ) ማንኛውም ተሰብሳቢ ሂሣብ ፤ ግዴታ ወይም የክፍያ ጥያቄ ከመሠረዙ በፊት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችና መፈፀም ስለሚገባው ሥነ ሥርዓት እና

ሐ) የተሰረዙ ተሰብሳቢ ሂሣቦችን ግዴታዎችንና የይገባኛል ጥያቄዎችን በሚመለከት መያዝ ስለሚገባው መረጃዎችና መዝገቦች ፤ የሚያጠቃልሉ ሊሆኑ ይችላሉ ።

፪· የማናቸውም ተሰብሣቢ ሂሣብ ፤ ግዴታ ፤ ወይም የይገባኛል ጥያቄ መሠረዝ ከተፈቀደው በጀት ላይ የመቀነስ ውጤት የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ዕዳው ሊሠረዝ የሚችለው በበጀት አዋጅ ወይም በሌላ ማናቸውም አዋጅ በወጪ በጀት የተያዘ ሲሆን ብቻ ነው።

፫· የማንኛውም ተሰብሣቢ ሂሣብ ፤ ግዴታ ወይም ሌላ የይገባኛል ጥያቄ መሠረዝ የክልሉ መንግሥት ዕዳውን ለማስመለስ ወይም ለመሰብሰብ ያለውን መብት አይገድብም ።

፬· ማንኛውም በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ አዋጅ መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተሠረዘ ተሰብሣቢ ሂሣብ ፤ ግዴታ ወይም ሌላ የይገባኛል ጥያቄ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ የመንግሥት ሂሣብ ውስጥ ተጠቃሎ ሪፖርት መደረግ አለበት ።

፲፬· <u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

፩· የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የመንግሥት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት ዕቃ ፤ ለሚሰጡት አገልግሎት እና ለአገልግሎት መስጫዎች የሚያስከፍሉትን ዋጋ ልክ በሚመለከት ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በተመለከተ ሌላ አዋጅ ልዩ ሥልጣን የሰጠ ከሆነ በንዑስ አንቀፁ የተመለከተው ተፈፃሚ አይሆንም ።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>በጀት</u>

፲፭· <u>የአቀራረብ ሥርዓት እና ጣሪያ</u>

፩· ቢሮው እና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አግባብ ካለው የመንግሥት ባለሥልጣን ጋር በመመካከር ዓመታዊ በጀት ስለሚቀርብበትና ለእያንዳንዱ የበጀት ጥያቄ መሠረት ሊሆን ስለሚገባው ከፍተኛው የገንዘብ መጠን የበጀት አቀራረብ ሥርዓት ይቀርጻሉ ።

11. *Remission of Amounts Paid*

Where the remission made under this or any other proclamation is subject to amounts already paid, the money shall be paid back by withdrawing from funds specially appropriated for such purpose.

12. *Reporting of Remitted Debts*

Debts that are subjects of remission made in accordance with this or any other proclamation in one fiscal year shall be, pursuant to directives issued by the Office, included in the public accounts report prepared for the fiscal year.

13. *Write-Offs*

1. The Regional Executive Committee may issue Regulations relating to the whole or partial writing off of any receivable, executable obligations or claims that are due to the Regional Government. Such Regulations may include:
   (a) the criteria for writting-off of any receivable, obligations or claims;
   (b) the necessary prerequisites and the procedures to be followed before any receivable, obligation or request of payment is written off; and
   (c) the information and records to be kept with regard to written off receivables, obligations and claims.
2. Where the writing-off any receivable, obligation or claim results in a deduction from the approved budget, the debt shall be written off only if the Budget Proclamation or any other proclamation has set the amount aside as expenditure.
3. The writing-off of any receivable, obligation or other claims shall not prohibit the Regional Government of its right to recover or collect the debts due to it.
4. Any receivable, obligation or other claims that are subject of writ-off made in accordance with this or any other proclamation in one fiscal year shall be, persuant to directives issued by the Office, included in the public accounts report prepared for the same fiscal year.

14. *Fees and Charges*

1. The Regional Executive Committee may issue Regulations with regard to fees and charges due to goods, services and facilities provided or public bodies.
2. Sub-Article (1) of this Proclamation shall not apply where another proclamation has given special authorization with regard to matters listed therein.

PART FOUR

Budget

15. *Format and Ceilling*

1. The Office and the Office of Planning and Economic Development, in consultation with the appropriate government authority, shall draw a format procedure for annual budgetary submissions and the maximum amount on which each budget request is to be based.

፪· የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የተከታታይ ዓመታት የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራሞች የአቀራረብ ሥርዓት ይመሰርታል ፡፡

፲፮· በጀትን ስለማጽደቅና ስለማሣወቅ

ለዓመቱ የተፈቀደው በጀት እስከ ሰኔ ፴ ቀን በክልሉ ምክር ቤት ፀድቆ ፣ ሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች እስከ ሐምሌ 7 ቀን እንዲያውቁት ይደረጋል ፡፡

፲፯· የበጀት ዝውውር

፩· የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ከመደበኛ በጀት ወደ ካፒታል በጀት ማዛወር ይቻላል ፡፡

፪· ከካፒታል በጀት ወደ መደበኛ በጀት ማዘዋወር አይቻልም ፡፡

፲፰· በመንግሥት መ/ቤት ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር

፩· በመንግሥት መ/ቤት ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር መደበኛ በጀትን በሚመለከቱ በዋና ሂሣብ መደቦች ውስጥ የሚደረግ ዝውውር እስከሆነ ድረስ የቢሮው ኃላፊ በጀትን ለማዛወር ያለውን ሥልጣን በውክልና አግባብ ላለው የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪· የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ በጀትን ከአንድ የካፒታል ፕሮጀክት ወደ ሌላ የካፒታል ፕሮጀክት ለማዘዋወር ያለውን ሥልጣን በውክልና አግባብ ላለው የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሰጥ ይችላል ፡፡

፲፱· በመንግሥት መ/ቤቶች መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ምክንያቶች የአንድ የመንግሥት መ/ቤት የካፒታል በጀት ወደሌላ የመንግሥት መ/ቤት የካፒታል በጀት እንዲዘዋወር ሊፈቅድ ይችላል፡፡

ሀ) በመንግሥት መ/ቤት የፀደቀ የመዋቅር ለውጥ ወይም የሥራ ኃላፊነት ማሻሻያ በመደረጉ ምክንያት የበጀት ዝውውር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፣

ለ) በአንድ የመንግሥት መ/ቤት ውስጥ ያጋጠመን የካፒታል በጀት እጥረት ለማቃለል ለሌላ የመንግሥት መ/ቤት የተፈቀደ የካፒታል በጀት በማዘዋወር መጠቀም አስፈላጊ ሲሆንና ይህም ተጨማሪ በጀት ያስፈለገው ቀደም ሲል ለተፈቀደ የካፒታል በጀት መሆኑ ሲረጋገጥ ፣

፳· ለድንገተኛ ወጪ ስለሚደረግ የበጀት ዝውውር

በዓመቱ የበጀት አዋጅ የተቀመጠው ማናቸውም ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በሥራ ላይ ላለው በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ በጣም አስቸኳይ የሆነና የዓመቱ በጀት በሚዘጋጅበት ጊዜ ያልታሰበ ተጨማሪ ገንዘብ ሲጠየቅ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለድንገተኛ ወጪ ከተያዘው በጀት ውስጥ በተጨማሪ ለተጠየቀው ወጪ የሚሆን በጀት ማዛወር ይችላል ፡፡

፳፩· ተጨማሪ በጀት

የክልሉ ምክር ቤት የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚያቀርበውን የውሣኔ ሐሣብ መሠረት በማድረግ ተጨማሪ በጀት ሊፈቀድ ይችላል ፡፡

፳፪· የበጀት መፅደቅ መዘግየት

፩· የክልሉ ምክር ቤት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የዓመቱን በጀት ሣያፀድቀው ሲቀር ምክር ቤቱ የዓመቱን በጀት እስኪያፀድቀው ድረስ ባለፈው ዓመት የፀደቀው መደበኛ በጀት በየወሩ እየታየ ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል ፡፡

2. The Office of Planning and Economic Development shall establish the procedure ofpresentation of the consecutive years investment program of the government.

16. *Budget Approval and Notification*

The budget appropriated for the year shall be approved by the Regional Council until Sene 30th and all public offices shall have been notified until Hamle 7th.

17. *Budget Transfer*

1. Subject to Regulations issued by the Regional Executive Committee, recurrent budget may be transferred to capital budget.
2. Capital budget may not be transferred to recurrent budget.

18. *Budget Transfers within Public Offices*

1. Where budget transfers made in public offices are related to recurrent budget transfers made within major sections of account, the Head of the Office may delegate his power of transfering budget to the executive head of the appropriate public office.
2. The Head of the Office of Planning and Economic Development may delegate his power of transfering budget from one capital project to another capital project to the executive head of the appropriate public office.

19. *Budget Transfers between Public Office*

The Regional Executive Committee may authorize the transfer of the capital budget of one public office to the capital budget of another public office under the following reasons:

(a) where making transfer of budget is necessiated due to structural changes approved by a public office or shift of responsibility;

(b) Where it is necessary to transfer and use the capital budget approved for another public office to lessen a budget deficit which occurred in one public office and where it is established that such additional budget is necessitated for a previously approved capital budget.

20. *Budget Transfer Made for Emergency Expenditures*

Without prejudice to any prohibition set under the Annual Budget Proclamation, where a request for extra fund is made that is urgently needed for the operations of the current fiscal year and which was not foreseen at the time of preparation of the year's budget, the Regional executive Committee may transfer funds from the emergency expenditure Reserve Budget to that needed for the extra expenditure request.

21. *Supplementary Budget*

The Regional Council may, based on the recommendations presented by the Regional Executive Committee, approve supplementary budget.

22. *Delay of Budget Approved*

1. Where the Regional Council fails to approve the budget of the fiscal year at the beginning of the year, the regular budget which was approved the previous year shall be implemented on a monthly basis until the Council approves the budget of the year concerned.

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ቀደም ሲል ለተፈቀዱ የካፒታል ፕሮጀክቶች ክፍያ ሊፈጸም የሚችለው ከፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር ይሆናል ።

## ክፍል አምስት
## የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ

### ፳፫· ከተጠቃለለው ፈንድ ክፍያ ስለመፈፀም

አንቀጽ ፳፪ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤

፩· የክልሉ ምክር ቤት በበጀት ካልፈቀደ በስተቀር ከተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ክፍያ ለመፈፀም አይቻልም ።

፪· ቢሮው ካላፀደቀው በስተቀር ከተፈቀደው በጀት ላይ ክፍያ መፈፀም ወይም የክፍያ ግዴታ መግባት አይቻልም።

### ፳፬· የክፍያ ገደብ

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፲፮–፳፩ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከቱት የመንግሥት መ/ቤቶች እንዲከፈል ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈፀም አይቻልም ።

### ፳፭· ግዴታ ስለመግባት

፩· በመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ በሚወክለው ሰው በጽሑፍ ካልተጠየቀ በስተቀር ለመ/ቤቱ ከተፈቀደው በጀት ላይ ክፍያ ለመፈፀም ግዴታ መግባት አይቻልም ።

፪· ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሚደርስ ማናቸውንም ዕዳ ለመክፈል የሚያስችል በቂ በጀት ካልኖረው በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ ክፍያን የሚጠይቅ ስምምነት ወይም ሌላ ዓይነት ግዴታ ውስጥ መግባት አይችልም ።

፫· ቢሮው ለእያንዳንዱ የሂሣብ መደብ የተገባለትን የፋይናንስ ግዴታ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓትና የሚመዘገብበት ቅጽ ያወጣል ።

፬· የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ቢሮው በሚያወጣው ቅጽ መሠረት ለእያንዳንዱ የሂሣብ መደብ የተገባለትን የፊናንስ ግዴታ ለመቆጣጠር የሚያስችል መዝገብ ይይዛል ።

### ፳፮· ለዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚደረግ ክፍያ

፩· መቅረብ ካለበት የወጪ ዝርዝር ወይም የክፍያ ማረጋገጫ በተጨማሪ የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ካላረጋገጠ በስተቀር ክፍያ ሊፈፀም አይችልም ።

ሀ) የተከናወኑ ሥራዎች ፤ የዕቃዎችና አገልግሎት አቅርቦት ክፍያዎችን የሚመለከት ሲሆን ፤

i) ሥራው መጠናቀቁን ፤ ዕቃው መቅረቡን ወይም አገልግሎቱ መስጠቱንና ዋጋው በስምምነቱ መሠረት የተጠየቀ መሆኑን፤ ዋጋው በስምምነቱ ካልተገለፀም ተቀባይነት ያለው መሆኑን፤

ii) በስምምነቱ በተገባው ግዴታ መሠረት ክፍያ የሚፈጸመው ሥራው ከመጠናቀቁ ፤ ዕቃው ከመቅረቡና አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ሲሆን ክፍያው በስምምነቱ መሠረት የተጠየቀ መሆኑን ወይም ፤

iii) ቢሮው በሚያወጣው ሥርዓት መሠረት ማረጋገጫ ከመገኘቱ በፊት ክፍያ መፈጸም ያለበት ሲሆን ጥያቄው ተቀባይነት ያለው መሆኑን ወይም ፤



2. Notwithstanding sub-Article (a) of this Article, payments for previously approved capital projects shall be effected in consulation with the Office of Planning and Economic Development.

## PART FIVE
## *Public Disbursement*

### 23. *Disbursement from the Consolidated Fund*

Without prejudice to Article 22

1. No disbursement shall be effected from the Consolidated Fund unless and otherwise the Regional Council has permitted through appropriation.
2. Unless and otherwise approved by the Office, disbursement or entering commitments for disbursement shall be made from the approved budget.

### 24. *Limit of Disbursement*

Except as provided under Aticles 16-21 of this Proclamation, no disbursements shall be effected that is more than the money amount allowed for the public offices shown in the Budget Proclamation of one fiscal year.

### 25. *Commitments*

1. No commitment to the effect of disbursement out of the approved budget of the public office shall be entered unless the executive head of the public office or the person delegated by him has made a requisition in writing.
2. No contract or other kind of commitment to the effect of disbursement to be made in the fiscal year shall be entered unless any public office has sufficient budget which enables it to disburse all debts which mature within the fiscal year concerned.
3. The Office shall set the procedures and the registration form which enables to control the financial obligation entered with regard to each budgetary item.
4. The executive head of the public shall, based on the form established by the Office, keep a record which enables to control the financial obligation entered with regard to each budgetary item.

### 26. *Disbursement Made for Goods and Services*

No disbursement shall be effected, unless, in addition to list of expenditures or certificates of payments required, the executive head of the public office or person delegated by him has certified the following:–

(a) Where the payment relates to works performed, the goods delivered and the services rendered and the price is offered in accordance with the agreement or if the price is not stated in the agreement, that it is reasonable;

(i) that the work has been performed, the goods delivered and services rendered and the price is offered in accordance with the agreement or if the price is not stated in the agreement, that it is reasonable;

(ii) that the payment has been offered in accordance with the agreement where the payment in accordance to the obligation entered is to be effected before the completion of the work, the delivery of the goods and the rendering of the services;

(iii) that the request is reasonable where, in accordance to the procedures prescribed by the Office, payment shall be effected in advance of verification; or,